# አገር አቀፍ የጤና ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል

## የኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር

መጋቢት 2013 ዓ.ም.

# ማውጫ


መቅድም ..... 2

ምስጋና ..... 3

ክፍል አንድ፤ አጠቃላይ ምልከታ..... 5

1.1. ዳራ .....5

1.1.1 የ2006 ዓ.ም. የጤና ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል ማሻሻያ ያስፈለገበት ምክንያት..... 6

1.1.2 የማካተቻ ማንዋሉ ዓላማ .....

1.2 የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋሉ መግቢያ .....7

1.2.1 የሥርዓተ-ፆታ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ..... 7

1.2.2 የሥርዓተ-ፆታ ማካተት በጤና ፖሊሲዎችና ህግጋት ውስጥ ..... 9

1.3 ዓላማ ..... 9

1.4 ቁልፍ መርሆዎች .....10

1.5 ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀም .....10

ክፍል ሁለት፤ በጤናው ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና ስልታዊ ቅንጅት .....12

2.1. የሥርዓተ-ፆታ ማካተት መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች.....12

2.2. የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ቁልፍ ጉዳዮች .....13

2.3. የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና ወሳኝ ማህበራዊ የጤና ጉዳዮች.....19

2.4. የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና፤ በጤናው ዘርፍ ውስጥ አዲስ የአሰራር ሥርዓት .....20

2.5. በጤናው ዘርፍ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት .....21

2.6. አገር አቀፍ የጤና ዘርፍ የሁለተኛው የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሥርዓተ-ፆታ ከማካተት አንጻር .....22

2.7. ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ተግባራዊ እርምጃዎች .....28

ክፍል ሦስት፤ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት መለኪያዎች .....32

አባሪ ሰነዶች .....37

ዋቢ መጻሕፍትና ማጣቀሻ ሰነዶች .....49

## መቅድም

ኢትዮጵያ የ2030 አለማቀፉ የዘላቂ ልማት ግቦችን በመቀበል እ.ኤ.አ. ከ2015 ወዲህ በጤናው ዘርፍ ፕሮግራሞችና ተቋማት ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን በማካተት የሥራ እምርታን አሳይታለች። 17ቱንም የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) ለማሳካት የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ማረጋገጥና ሁሉን ሴቶችና ልጃገረዶችን ማብቃት ቁልፍ መሆናቸውን የጤና ሚኒስቴር ይገነዘባል። የዘላቂ ልማት ግቦችንና "ማንም ወደ ኃላ መቅረት የለበትም" የሚለውን ቃልኪዳን ለማሳካት ቅድሚያ ሴቶችና ልጃገረዶች በሃገሪቱ ዙሪያ የሚገጥማቸውን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦትና መድሎን መታገል ወሳኝ ነው።

ይህን ለማሳካት፣ ሁሉም የሁለተኛው የጤና ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የእኩልነትና የመድሎ አለመኖርን መርሆዎች ማካተት፤ የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት አገር አቀፍ ስልታዊ እቅድ ውስጥ ማካተት፤ የሴቶችና የወንዶች ንቁና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ፤ እና ሁሉንም ሴቶችና ልጃገረዶችን ማብቃት ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

እ.ኤ.አ በ2014 የተመረቀውና ሁለተኛው አገር አቀፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል በተለመደው ስልታዊ እቅድ ላይና በተቋሙ ባህል ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ትራንስፎርሜሽን ተግባራትን በማካተት ረገድ ተጨባጭ የመጀመሪያ ደረጃ እምርታን አሳይቷል። ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ የሥርዓተ-ፆታ ማካተትን ከግምት ውስጥ በማስገባት እኩልነትን እንደ መርህ ይዟል። ይህም ሥርዓተ-ፆታን ከወሳኝ የጤና መስፈርቶች ትንተና ውስጥ ማካተትን ይጨምራል። እንደዚሁም በአገልግሎት ሰጭዎችና በተገልጋዮች ደረጃ የአካታችነት መርህን የሚከተለውን የሰብአዊ መብት አሰራርን የተከተለ ነው። "ሰዎችን ማዕከል ያደረገ አቀራረብ" እና "ጤና በሁሉም ፓሊሲዎች ውስጥ" የሚሉት አቀራረቦች እንደ ቅደም ተከተላቸው በጤና ዘርፍና በሌሎች ፈርጀ ብዙ ዘርፎች እንደ ዋና አሰራር ተወስደዋል። በጤናው አገልግሎትና አቅርቦት ስትራቴጂ ልማትና ለውጥ ውስጥ  ለተሻለ የጤናው ዘርፍ ውጤትና የሃብት አስተዳደር የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል። ስለሆነም፤ የህብረተሰብ ጤና ቁሳቁሶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ካላቸው ከዓለማቀፋዊና ብሔራዊ ለውጦች ጋር ተጣጥሞ ለመንዝ ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ የብሔራዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋሉን ለመከለስና ለማሻሻል ተገዷል።

ክለሳው ለመረዳትና ለመተግበር ቀላል በሆነ መልኩ እንዲቀርብ በማድረግ ላደረጉት አስተዋፅዖ የሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ለየሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ዳይሬክቶሬትና ለቴክኒክ የሥራ ቡድኑ ምስጋናውን ያቀርባል።

ወ/ሮ ሳህሬላ አብዱላሂ

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ

# ምስጋና

የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋሉን የመጀመሪያ ደረጃ ክለሳ ስላደረጉ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለኢንጂንደር ሄልዝ-ኢትዮጵያ ላቅ ያለ ምስጋና ያቀርባል። ሁለተኛውን የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ማንዋሉ በሥርዓተ-ፆታ የቴክኒክ የስራ ቡድን ታይቷል። በመሆኑም ላሳዩት ቁርጠኝነትና ለማንዋሉ ስኬት ላበረከቱት ቴክኒካዊ ግብዓት የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ያመሰግናቸዋል።

ሰነዱ ከወቅታዊ ግኝቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የማንዋሉን የሁለተኛ ደረጃ ክለሳ ስላደረጉና ሰነዱ ላቅ ያለ ጥራት እንዲኖረው ለሠሩት የአርታኢነት ስራ ከሁሉም በላይ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ለአለም ጤና ድርጅት የተለየ ምስጋና ያቀርባል።

ከታች የተዘረዘሩት ግለሰቦች ላበረከቱት ላቅ ያለ አስተዋፅዎ በተለየ መልኩ ሊመሰገኑ ይገባል።

ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ - የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶች፣የሕጻናትና የወጣቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ወ/ሮ ሌንሳ ዘካርያስ - በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶች፣የሕጻናትና የወጣቶች ዳይሬክቶሬት

አቶ አቤል ሞሴ - በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶች፣የሕጻናትና የወጣቶች ዳይሬክቶሬት

ዶ/ር ፍቅር መለሰ - የአለም ጤና ድርጅት - ኢትዮጵያ

ወ/ሮ ሄራን አበበ - ዩኤስኤይድ ትራንስፎርም ፕራይመሪ ሄልዝ ፕሮጀክት፤

ዶ/ር ዙፋን ዳምጠው - ኢንጂንደር ሄልዝ - ኢትዮጵያ

ዶ/ር ንፅህት ወርቁ - የኢንጂንደር ሄልዝ - ኢትዮጵያ አማካሪ

በመጨረሻም፤ ሰነዱን ወደ አማርኛ ለማስተርጎም የዓለም ጤና ድርጅት፣ እንደዚሁም ሰነዱን ለማሳተም ኢንጂንደር ሄልዝ- ኢትዮጵያ ላደረጉት የገንዘብ ድጋፍ የጤና ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል።

# ክፍል አንድ፤ አጠቃላይ ምልከታ

የየትኛውም ሃገር ልማት በሁሉም ዘርፉ የማህበረሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶችን በእኩልነት ሳያሳትፍ እና ሴቶችን ሳያበቃ ሊሳካ ስለማይችል “የቤጂንግ ድክላሬሽን ኤንድ ፕላትፎርም ፎር አክሽን” (የቤጅንግ ማሳሰቢያና የተግባር መድረክ) በተሰኘውና እ.ኤ.አ. በ1995 በቤጂንግ በተደረገው በአለም የጤና ኮንፈረንስ (ስብሰባ) ላይ በመመስረት የተባበሩት መንግስታት፣ በ15ኛው ጠቅላላ ጉባኤው እ.ኤ.አ. በ1997 በሁሉም ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታ መካታት አለበት የሚል ውስኔ አስተላለፈ። የቤጂንጉ ዲክላሬሽን ደግሞ እ.ኤ.አ በ1985 በናይሮቢ በተደረገው የእኩልነት፣ የልማትና የሰላም የዓለም ኮንፈረንስ ላይ በተደረገው ውሳኔ ላይ የተመሰረተ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግስት ከአለማቀፋዊው ስምምነቶቹ ጋር በሚስማማ መልኩ በብሔራዊ ግቦቹና ዓላማዎቹ ላይ በመመርኮዝ የሥርዓተ-ፆታ ማካተትን በሚኒስቴር መስሪያቤቶቹ፣ በኤጀንሲዎቹ፣ በግል ተቋማትና በማህበረተሰቡ ውስጥ ለመተግበር መወሰን ችሏል።

ዘላቂ የልማት ግቦች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት በራሱ አንድ ግብ እንደሆነና ሌሎች ግቦችን በሙሉ ለማሳካት ደግሞ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ይረዳል። የዘላቂ የልማት ግቦችን ማሳካት የጤና ዘርፍን አቅም ለሰላምና ለብልጽግና ለመገንባት ያስችለዋል ፤ ስለዚህ ሴቶች ግቦቹን በማሳካት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው።

የጤና ሚኒስቴር የሴቶች፣ የሕጻናትና ወጣቶችን ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ሥርዓተ-ፆታን በጤናው ዘርፍ በማካተት ሃላፊነቱን ተወጥቷል።

የሥርዓተ-ፆታን አስፈላጊነት የጤና ሚኒስቴር ራዕይ ውስጥ “ጤናማ፣ ምርታማና የበለፀገን ማህበረሰብ ማየት” በሚል ሐረግ ያመላከተ ሲሆን ይኸውም ሁሉን አካታችና ተጋላጭ የሆኑ ወገኖችን የማገልገል እሳቤን ያነገበ መሆኑን ያስተውላል። በመሆኑም በኢትዮጵያ የሚኖሩ ህዝቦች ጤናማና ምርታማ ዜጋ ሆነው ወደ ብልጽግና እንዲገሰግሱ ይሰራል ማለት። ይህ ራዕይ ሊሳካ የሚችለው የማህበረሰቡ 50 በመቶ የሆኑ ሴቶች በጤና ስልታዊ እቅድ ትግበራ ውስጥ ሲሳተፉና ተጠቃሚ ሲሆኑ ብቻ ነው። እንደዚሁም፤ “ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ፓኬጆችን በከፍተኛ ጥራትና ፍትሃዊነት በማቅረብ የህብረተሰቡን ጤና እና ደህንነትን ማረጋገጥ” የሚለው ተልዕኮውም የሚያንጸባርቀው የጤና አገልግሎት ክፍሉ ሁሉም ፕሮግራሞች እና አሠራሮች በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን በማስረገጥ በፍትሃዊነት ትንተና ያደረገ መሆኑን ያሳያል። የሴቶችና የወንዶች የተለዩ ፍላጎቶች (specific needs) በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት ፓኬጆች ውስጥ የተካተቱ ናቸው።

ስለዚህ የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ዳይሬክቶሬት በፖሊሲዎች፣ በፕሮግራሞች እና በአሠራሮች ውስጥ በአራቱም የሁለተኛው የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (እ.ኤ.አ 2020-2025) ምሶሶዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ኃላፊነት ተሰጥቶታል። እነዚህም ምሶሶዎች የታሳለጠ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን መስጠት፣ ሰዎችን ከድንገተኛ የጤና እክሎች መጠበቅ፣

የወረዳ ትራንስፎርሜሽንና የጤና አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና አካላት የምላሽ አሰጣጥን ማሻሻል ናቸው።

ሁለተኛው ብሔራዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል እ.ኤ.አ በ2014 ስራ ላይ ከዋለ ጊዜ ወዲህ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ጽንሰ ሃሳቡ እንዲተዋወቅ ተደርጎ በመላው የጤና ዘርፍም ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል። ይሁን እንጂ በፕሮግራምና እቅድ ሳይክል ውስጥ ተቋም አቀፍ የሆነ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና አቅም አለመገንባቱ ወይም ውስንነት (ማለትም እስካአሁን የመነሻ ትንተና አለመዘጋጀቱ)፤ የአመራሩን ቁርጠኝነት የሚያመላክት በጤና ሚኒስቴር አመራር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ አለመካተቱ፤ ፆታን መሰረት ያደረገ መረጃ ለማደራጀትና እና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና እንዲኖር አለመበረታታቱ፣ እንዲሁም በሁሉም ዘርፎች ዘንድ ወሳኝ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ መስፈርቶችን በማስቀመጥ ተጠያቅነትን በማረጋገጥ ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ።

### 1.1.1. የ2006 ዓ.ም. የጤና ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል ማሻሻያ ያስፈለገበት ምክንያት

ከ2006 ዓ.ም ወዲህ የጤናው ዘርፍ አገልግሎት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ለውጦች በሃገሪቱ ተከስተዋል። እነዚህ ለውጦች የጤና የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል እዲከለስ ምክንያቶች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ከታች የተዘረዘሩት ወሳኝ ለውጦች ለክለሳው መሰረታዊ ምክንያቶች ናቸው።

- ከጤና ዘርፍ ልማት ዕቅድ ወደ የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስልታዊ ሽግግር መደረጉ። ይህም የአገልግሎት አሰጣጥ ፍትሃዊነት እና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ አካላትን - ማለትም ሴቶችን፣ ሕጻናትን፣ ወጣቶችንና የአካል ጉዳተኞችን ያማከለ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ትኩረት ያደረገ ነው።
- የዘላቂ ልማት ግቦች መቀረጽ፣ እንደዚሁም አዳዲስ ብሔራዊ ህግጋት ለምሳሌ እንደ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ (ቁ 970-2016) ፤ የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ (1064-2017) ፤ እና የሥርዓተ-ፆታን አካታችነት የሚጠይቅ የሰራተኛና አሰሪ አዋጅ (ቁ. 1156-2019) ያሉ አዋጆች መውጣታቸው
- ፕሮግራሞችን/ኦፕሬሽኖችን እና ፖሊሲዎችን ለመገምገም ወሳኝ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስኮር ካርድ እና የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ አሰጣጥ የግምገማ መስፈርት መዘጋጀታቸው።

### 1.1.2. የማንዋሉ ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዓለማ የጤና ሚኒስቴር ፈፃሚዎች በሁሉም የስራቸው ዘርፍ በስትራጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ በስታንዳርድን ዝግጅት ሂደት፣ በክልል ደረጃ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን ቀይሰው በመተግበር እና የፕሮጀክት ዑደት (ምህዋረ-ሕይወት) በማስፈጸም ሂደት የሥርዓተ-ፆታን በብቃት እንዲያካትቱ ማገዝ ነው። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ በየደረጃው ያለው ሁሉም ሰራተኛ ለመተግበር ሊተጋ የሚገባው የጋራ፣ ተቋማዊና ከፕሮግራሞች ጋር የተቀናጀ ሊሆን የሚገባው ጥረት ነው። ብዙ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ተግባሮች አሁንም ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ብዙም ትኩረት አይሰጡም፤ በአንዳንዶቹ ዘንድ ደግሞ ጭራሹንም ቦታ የለውም። በጤና ሚኒስቴር ሥራ

ውስጥ በማንኛውም ተግባር ሥርዓተ-ፆታን ለማካተት የሥርዓተ-ፆታ ገጽታዎችን መረዳት ይጠይቃል። ይኽውም ሥርዓተ-ፆታን ማካተት መረጃ ማግኘትን፣ ትንተናንና ከሴቶች እና ከወንዶች ጋር መመካከርን ይፈልጋል። በመጨረሻም፤ የሥርዓተ-ፆታ አካታችነት አመለካከትን ማዳበር ሚዛኑን ወደ ጠበቀና ሁሉንም ወደሚወክል አቀራረብ ያመራል። በመሆኑም በሁሉም የጤና ሚኒስቴር የስራ ዘርፎች ውጤታማ የጤና ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

### 1.1.3. የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል ተጠቃሚዎች

ይህ ለሶስተኛ ጊዜ የተከለሰው ማንዋል የተለያዩ በሃገሪቱ በጤናው ዘርፍ ውስጥ የሚያገለግሉ ማለትም ውሳኔ ሰጪዎች፤ እቅድ አዘጋጆች፤ የፕሮግራም አመራሮች፣ ጤና አገልግሎት ሰጪዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች፣ የክትትልና ግምገማ ባለሙያዎች እና የኦፕሬሽን (የአስተዳደር) ሰራተኞች ሥርዓተፆታን በጤናው ሥርዓት ውስጥ አካትተው እንዲተገብሩ ለማገዝ ነው። በተጨማሪም በየደረጃው በሚገኙ በጤናው ዘርፍ ተቋማዊ አሰራር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታን የማካተት የጋራ ማዕቀፍ ተፈጥሮ መልካም የተቋም ባህልን ለማዳበር አስተዋፅጾ በማድረግ ረገድ እንዲያግዛቸው ነው።

በተጨማሪም የሥርዓተ-ፆታ ተጠሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ተግባራትን፣ እንደዚሁም የጤና አገልግሎት አጋሮች ተግባራትን በተቀናጀና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማስተባበርና ለመከታተል ይረዳቸዋል።

## 1.2. የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋሉ መግቢያ

### 1.2.1 የሥርዓተ-ፆታ መሰረታዊ ጽንሰ ሐሳብ

'ሥርዓተ-ፆታ' በሚለው ሐረግ ትርጉም እና 'ፆታ' ከሚለው ቃል ጋር እንዴት በትርጉም እንደሚለያዩ በተመለከተ ሰፋ ያለ ግርታ አለ። ይሁን እንጂ ፆታና ሥርዓተ-ፆታ አንድ አይደሉም። ፆታን በተመለከተ ሰዎች "ወንድ" እና "ሴት" በመባል የሚከፍሉ ሲሆኑ ከሥነ-ተፈጥሮ (biology) እና ስነ-ልቦና ልዩነቶች የተነሳ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታዩትን ልዩነቶችን ያብራራል። ሥርዓተ-ፆታ ላይ በመመስረት የሚደረጉ ክፍፍሎች "ወንድ" እና "ሴት" የሚባሉ ሲሆኑ ሚናዎች፣ ባህሪያት፣ ተግባራትና በማህበረሰቡ የተገነቡና በዘልማድ በማህበረሰቡ ለወንድ እና ለሴት የሚሰጡ እሴቶች ናቸው።

ሴቶችና ወንዶችን፣ ወንዶች ልጆችና ልጃገረዶችን በተመለከተ የሚስተዋሉ እምነቶች/ግንዛቤዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ በማህበራዊ ሂደት የሚተላለፉ ናቸው። እነዚህ ግንዛቤዎች ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ ስለ ሥርዓተ-ፆታ ተቀባይነት ያገኙ አመለካከቶች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ምን ምን ተገቢ የሆኑ የወንዶችና የሴቶች ባህሪያት ሊሆኑ እንደሚገቡ ይወስናሉ።

በህብረተሰቡ ዘንድ ስለ ሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች (Gender norms) የትኞቹ ተግባራት፣ ስራዎች፣ እና ኃላፊነቶች የወንዶችና የሴቶች ተብለው እንደሚመደቡም ይወስናሉ። በሌላ መልኩ

የሥርዓተ-ፆታ ሚና በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶችና ወንዶች ምን ምን ማከናወን እንዳለባቸው በተለይም በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በሥራ ቦታ የሚያንጸባርቁት የስራ ክፍፍሎች ላይ ተጽህኖ ያሳድራል። ይህ ደግሞ በመደበኛው የስራ ገበያ መሳተፍን ወይም የቤት ውስጥ ስራንና የአስተናጋጅ አገልግሎት ኃላፊነቶችንም ያካትታል። በአጠቃላይ እነዚህ ሚናዎች የምርታማነት፣ የሥኑ-ተዋልዶ እና የማህበረሰብ ስራ ሚናዎች በመባል ይከፈላሉ።

**ምርታማ ሥራ** ማለት ለግል ፍጆታ ወይም ለንግድ ተብለው የሚመረቱ ምርቶች እና/ወይም አገልግሎቶች ናቸው። ለምሳሌ፦ እርሻ፣ የዓሣ እርባታ፣ የፋብሪካ ስራ፣ ወይም በግንባታ ስራ ላይ መስራት ሲሆኑ በመቀጠር ወይም ስራን በመፍጠር የሚሰሩ ናቸው። ስራቸው ምን እንደሆነ ሲጠየቁ ምርታማ ስራቸውን በተለይም ክፍያ የሚያገኙበትን ስራ ይጠቅሳሉ።

**የሥኑ-ተዋልዶ ሥራ** ማለት ቤተሰብን መንከባከብ እና የቤት ውስጥ ስራን ማከናወን ሲሆን ልጆችን መውለድና ማሳደግን እንደዚሁም የቤተሰቡን ጤና ኃላፊነት መውሰድን ያካትታል። በተጨማሪም ምግብ በማብሰል፣ ዉሃ በመቅዳት፣ ማገዶ በመልቀም፣ ከእጅ ወደ አፍ የማብርና ስራ ላይ በመሰማራት፣ እና ሎሌችም የቤት ውስጥ ስራዎችን በመስራት የቤተሰቡን የምግብ ፍላጎት ማሟላትን ያካትታል።

**የማህበረተሰብ ሥራ** ማለት የማህበረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል የታቀዱ አጠቃላይ ማህበራዊ ኩነቶች፣ አገልግሎቶችና ተግባራት ላይ መሳተፍ ሲሆን በተጨማሪም በዓላት፣ ሥርዓቶች፣ የፖለትካ ተሳትፎዎች እና ሌሎች የማህበረተሰብ አደረጃጀቶች ውስጥ መሳተፍ ማለት ነው። እነዚህ ተግባራት ለቤተሰቡ ኑሮና ደህንነት ወሳኝ ሲሆኑ በአብዛኛው ጊዜ የሚወስዱና ከፍተኛ የጉልበት ስራን የሚጠይቁ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ ስራዎች ክፍያ የማይገኝባቸውና በዘልማድም የሚሰጣቸው ዋጋ አነስተኛ ነው። በመሆኑም ተሳታፊውን ከፍተኛ አንጻራዊ ጥቅም የሚያሳጡ ናቸው። ይልቁንም በአብዛኛው በቤተሰብ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ የህብረተሰብ ሚና ተደርገው ይወሰዳሉ።

በሌላ ጎኑ፣ የማህበረሰብ ስራ የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ የመሰረተ ልማት ማሻሻያዎች እና ማህበረሰቡን በጋራ የሚጠቅሙ የተለያዩ ስራዎችን ያካትታል። እንደዚሁም መደበኛም ሆነ ኢመደበኛ በሆነ መልኩ የሚሰሩ የማህበረሰቡ ፖለቲካ ስራዎችን ይጨምራል። በብዙ ማህበረሰብ ውስጥ የፖለቲካ ስራን የሚሰሩት ወንዶች ናቸው። በምላሹ የገንዘብ ጥቅም ወይም የተሻለ ተቀባይነትና ስልጣን ያገኙበታል። ሴቶች ግን "በትርፍ" ጊዜያቸው የሚሰሩት የማህበረሰብ ስራዎች ላይ ይሳተፋሉ። ይህም እንደ ሥኑ-ተዋልዶ ሥራቸው አካል ይወሰዳል። ሥራውም ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት (ያለ ክፍያ) የሚሰራ ነው። ለምሳሌ የማህበረሰቡን ሃብት መጠበቅ፣ በፈቃደኝነት፣ በማህበረሰቡ መማክርት ጉባኤ ውስጥ መሳተፍ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ስራዎች ውስጥ መሳተፍ ናቸው።

የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች ከማህበረተሰብ ወደ ማህበረሰብ የሚለያዩ መሆናቸውን ልብ ይለዋል። ይህ ልዩነት በአጎራባች ማህበረሰቦችም መካከል ሊታይ ይችላል። በአጠቃላይ በአብዛኛው ሴቶች ተጎጂዎች ናቸው። ከወንዶች ይልቅ ከባድ ስራዎችን የሚሰሩ ሲሆኑ የተለያዩ ሃብቶችን የማግኘት እድላቸው ግን ጠባብ ነው።

በክፍያ በሚሰሩ ስራዎችም ዙሪያ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦችና ሚናዎች ወንዶችና ሴቶች በሚሰሩት የስራ አይነቶች ላይም ጭምር ተፅህኖ አላቸው። በብዙ አገሮች ሴቶች የሚሰማሩባቸው ሙያዎችና የስራ ዘርፎች ማህበረሰቡ የሴቶች ሥራ ናቸው ብሎ የሚወስዳቸው ሥራዎች ናቸው። ለምሳሌ የመንከባከብ ሥራዎች፣ የቤት ውስጥ ሥራዎችና የአልባሳት ኢንዱስትሪዎች ናቸው። ሴቶች እነዚህን ሥራዎች በቤታቸው ሲሰሩ ስለማይከፈላቸው በቅጥር ቢሰሩም በቂ ክፍያ አይከፈላቸውም።

በተጨማሪም፣ በብዛት በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ - ኢትዮጵያን ጨምሮ - ወንዶች የቤተሰቡ መተዳደሪያ የገቢ ምንጭ ተደርገው ስለሚወሰዱ ሴቶቹ የሚያስገኙት ገቢ እንደ ድጎማ ብቻ ነው የሚታየዉ።

“ያለ ክፍያ የሚሰሩ የእንክብካቤ ስራዎች” ከታች በተዘረዘሩት ሶስት ወሳኝ ባህሪያት አንፃር ይተረጎማሉ፡-

- “ያለ ክፍያ” የሚለው ሐረግ ሥራው የገንዘብ ጥቅም እንደማያስገኝ ያመላክታል።
- “እንክብካቤ” ማለት ሥራው ለሌሎች ሰዎች ደህንነት የሚሰራ የአገልግሎት ሥራ መሆኑን ያሳያል።
- “ሥራ” ማለት ደግሞ ተግባሩ ጊዜና ሃይልን የሚጠይቅ ሲሆን ከማህበረሰብ ወይም ከቤተሰብ ግንኙነት የተነሳ በሰሪው ላይ የተጣለ ሃላፊነት መሆኑን ያሳያል።

የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎችና በማህበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች (gender norms) በጥንድነት “የሥርዓተ-ፆታ ግንኙነቶች” ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ። ግንኙነቶቹ በተናጠል በሴቶችና በወንዶች አልያም በቡድን ደረጃ እና በአንድ ሥነ-ፆታ መካከል ያሉ ግንኙነቶች ናቸው። ይህም በወንዶችና በሴቶች እንደዚሁም በሥነ-ፆታዎቻቸው መካከል በግለሰብ ደረጃ ወይም በቡድን በህብረተሰብ ደረጃ የሚደረጉ መስተጋብሮች ናቸው። እነዚህ ግንኙነቶች በባህል፣ በሃይማኖታዊ እምነቶችና የአመለካከት ስሪቶች የሚደገፉ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንአልባትም በተቋማትና በድንጋጌዎችም የተደገፉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ስለዚህ፣ ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ አራት ምሶሶዎች ያሉት ሲሆን (እነዚህም ምሶሶዎች የተሳለጠ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን መስጠት፣ ሰዎችን ከድንገተኛ የጤና እክሎች መጠበቅ፣ የወረዳ ትራንስፎርሜሽንና የጤና አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና አካላት የምላሽ አሰጣጥን ማሻሻል ናቸው) አላማውም በሁሉም ተግባራቱ ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተትና የሥርዓተ-ፆታን የእኩልነት ክፍተቶችን እያጠበበ የጤናን አገልግሎት ጥራት ማሻሻል ነው።

### 1.2.3 በጤና ፖሊሲዎችና ድንጋጌዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት

የኢትዮጵያ መንግስት ሴቶችን ለማብቃት የታለሙና የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት የሚደግፉ በርካታ አለማቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶችንና ዲክላሬሽኖችን (ውሳኔዎችን) ፈርማለች። ከእነዚህም

መካከል የእ.ኤ.አ 1979 በሴቶች ላይ የሚደረጉ ማናቸውም አይነት መድሎዎችን የማስወገድ ስምምነት (Convention on the Elimination of All Forms Of Discrimination Against Women (CEDAW)) የእ.ኤ.አ 1993ቱ የቪዬናው ዲክላሬሽን እና ፕሮግራም ፎር አክሽን፣ የእ.ኤ.አ የ1994ቱ የፖፑሌሽንና ልማት አለማቀፍ ኮንፈረንስ፤ የአ.ኤ.አ 1995ቱ የቤጂንግ ዲክላሬሽንና ኮል ቱ አክሽን ጉባኤ፣ የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች፣ የእ.ኤ.አ 2013ቱ ዘኮሚሽን ኦን ዘ ስታተስ ኦፍ ውሜን፣ ዘላቂ የልማት ግቦች፣ እ.ኤ.አ በ2010 የተቋቋመው የዩኤን ውሜን፤ የተባበሩት መንግስታት አዲሱ የሥርዓተ-ፆታ የእኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ተቋም ስምምነቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የአፍሪካ አህጉር ዲክላሬሽኖችና ስምምነቶች እ.ኤ.አ የ2003ቱ የአቡጃ ስምምነት፣ እ.ኤ.አ የ2006ቱ የማፑቶ ዲክላሬሽን፣ እንደዚሁም 2063 የአፍሪካ ዘላቂ የልማት ግቦች በጥቂቱ ይጠቀሳሉ።

አገራዊ ህጎችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ህገመንግስት በማያሻማ መልኩ በአንቀጽ 35 ላይ **ሴቶች የአገሪቱ እኩል ዜጎች** የመሆናቸውን መብት ያረጋግጣል። ሌሎች ፖሊሲዎችም (ቢሔራዊ የህዝብ ፖሊሲን ጨምሮ) እ.ኤ.አ በ1993 የተላለፈው የኢትዮጵያ ሴቶች ፖሊሲና የጤና ፖሊሲ (በአሁኑ ወቅት ክለሳ ላይ ይገኛል) ይህንኑን አመለካከት የሚደግፉ ሲሆን ፍትሃዊ ተደራሽነትን፣ የተገለሉ ማሕብረሰብን፣ ኮረዳ ሴት ልጆችን እና የገጠር ነዋሪዎችን አፅንያት ይሰጣል።

በተጨማሪም በቅርቡ የተደነገጉ የተለያዩ ህጎች ለሴቶች ከቀድሞው የበለጠ የተሻለ መብትና ጥበቃ የሚያረጋግጡ ናቸው። እነዚህም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ (ቁ 970-2016) ፤ የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ (1064-2017) ፤ <u>የሴቶች፣የሕጻናትና የወጣቶች ሚኒስቴርን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ (የአዋጅ ቁጥር 1097/2018)</u> ፣ እና የሰራተኛና አሰሪ አዋጅ (ቁ. 1156-2019) ናቸው።

## 1.3. ዓላማ

በሁሉም የጤናው ዘርፍ እርከኖች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና አሠራሮች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ውጤታማ በሆነ መልኩ በማካተት ጥራት ያለውና ፍትሃዊ የሆነ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ሆኖ እንዲሰጥ ማድረግ ነው።

ሥርዓተ-ፆታን ማካተት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡-

- በሁሉም የሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (HSTP II) የትግበራ ፕሮግራሞች፣ አሠራሮች፣ አመራርና ፖሊሲዎች ውስጥ የጤና ሚኒስቴርን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና አቅም መገንባት
- በጤና ትግበራ እቅድ ዑደት (ምሕዋረ-ሕይወት) እና በሪፓርት ሥርዓት ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት
- በፆታ ተከፋፍለው የተደራጁ መረጃዎችን መጠቀምና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መስራትን ማበረታታት
- በሁሉም ደረጃ ተጠያቂነት እንዲኖር ማስቻል

## 1.4. ቁልፍ መርሆዎች

የጤና ባለሙያዎች ማንዋሉን ሲተገብሩ ከታች የተዘረዘሩ መሠተታዊ መርሆዎችን መከተል ይጠበቅባቸዋል።

***ፍርሃዊነትና ጥራት*** - የጤና አገልግሎቱ የጥራት ደረጃን የጠበቀ ሆኖ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በፍትሃዊነትና በጥራት ደህንነትን በጠበቀ መልኩ መሰጠት አለበት።

***አካታችነት*** - ሁሉም የጤና ፕሮግራሞችና ኦፕሬሽኖች (አሠራሮች) ሥርዓተ-ፆታን ያካተቱና ፍትሃዊ ሆነው ጤና እና ደህንነትን የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው።

***ተሳታፊነት*** - በአመራር፣ በውሳኔ አሰጣጥ፣ በመካሪነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በክትትልና ግምገማ ሂደት የሴቶች ተሳትፎ መረጋገጥ አለበት።

***ሰብአዊ መብት*** - የጤና አገልግሎት የሴቶችን፣ የወጣት ልጃገረዶችንና የወንዶች ልጆችን እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ሰብአዊ መብትን ማዕከል ባደረገ አቀራረብ መቃኘት አለበት።

***ተጠያቂነት*** - ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ሥራዎችን የመተግበር፣የመከታተልና የመገምገም ተገቢ የአሠራር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል።

***ደረጃውን መጠበቅ*** - በሥርዓተ-ፆታ ማካተት ስልታዊ እቅድ ውስጥ የተገለፁትን መመዘኛዎች ማጠናከርና ዘላቂነታቸውን መከታተል ያስፈልጋል።

***ቀጣይነት*** - የጤና ሚኒስቴርን ራዕይ በተከተለ መልኩ በጤና ትምህርት፣ በማዳን፣ በመከላከል እና በማገገሚያ የጤና አገልግሎቶች ውስጥና በተቋማዊ ኦፕሬሽኖች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን የማቆራኘት ሥራ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል።

## 1.5 ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀም

***ሥነ-ፆታ ሥርዓተ-ፆታ አይደለም!***

ፆታ ማለት አንድን ሰው ወንድ ወይም ሴት መሆኑን የሚለዩ እንደ ውስጣዊና ውጭአዊ የሥነ-ተዋልዶ ብልቶች እንዲሁም ሆርሞኖችና ዘረመሎች (ክሮሞዞሞች) የመሳሰሉ የሥነ-ህይወትና የሥነ-ልቦና ባህሪያት ማለት ነው።

***ሥርዓተ-ፆታ*** - ማለት ማህበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች የተገቡ ናቸው በማለት የሰየማቸው ባህሪያት ናቸው። በወንዶችና በሴቶች መካከል እንዲሁም በሴቶችና በሴቶች እና በወንዶችና በወንዶች መካከል የተቀመጡ ተገቢ ተብለው የተወሰዱ ባህሪያት፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የእነዚህ ባህሪያት ምሳሌዎች ናቸው። አብዛኛው ሰው በግልፅ የተለየ ፆታ ይዞ ይወለዳል። ነግር ግን በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን እሴቶች እና ባህሪያትን ከሕብረተሰቡ ይማራል። ይህም ከተመሳሳይና ከተቃራኒ ፆታ ጋር፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር፣ በስራ ቦታ እና በማሕበረሰባቸው መካከል ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባቸው አቀራረቦችን ያካትታል። ሥርዓተ-ፆታ ከማህበረሰብ ወደ ማሕበረሰብ ሊለያይ የሚችልና በጊዜ ሂደትም ሊለወጥ የሚችል ነው።

***የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት*** - የሚያመላክተው በወንዶችና ሴቶች (በተናጠል ሆነ በቡድን) ማሕበራዊ እቅፍ ውስጥ፣ የኢኮኖሚ (ምጣኔ ሃብት) እና የፖለቲካዊ ሃብቶችን የማግኘትና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እኩል እድሎችና የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲኖሯቸው ማድረግ ነዉ። ይህ ደግሞ የህግ ጥበቃ ማግኘትን (ለምሳሌ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርትና የመምረጥ/ድምጽ የመስጠት መብቶችን) ያጠቃልላል። በሌላ አጠራር መደበኛ እኩልነት ይባላል።

***የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት*** - የሚያመላክተው የሴቶችና የወንዶች የተለያዩ ፍላጎቶችና ምርጫዎችን ነው። ይህም ዕድሎችን በእኩልነት ለማስፈን የተለያዩ አግባብነት ያላቸው አያያዞች ሊያስፈልጉ ይችላሉ ማለት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህ መሰረታዊ እኩልነት (substantive equality) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የወንዶችንና የሴቶችን ነባራዊ ሁኔታ ማገናዘብን ይጠይቃል።

***የጤና ፍትሃዊነት*** - በማህበራዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ህዝባዊ (demographically) ወይም መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች የተለያዩ ቡድኖች ወይም ህዝቦች መካከል ፍትሃዊ ያልሆኑ፣ ማስወገድ ወይም መከላከል የሚቻሉ የጤና ልዩነቶች አለመኖር ማለት ነው።

# ክፍል ሁለት፤ በጤናው ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና ስልታዊ ቅንጅት

## 2.1. የሥርዓተ-ፆታ መሰረታዊ ጽንሰ ሐሳቦች

ሥርዓተ-ፆታን ማካተት የሚል ጽንሰ ሃሳብና ጥቅሞቹ በቂ መረዳት አላገኙም። የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ሥርዓተ-ፆታ በሰዎች እድሎች፣ በማህበራዊ ሚናዎቻቸውና በመስተጋብሮቻቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽህኖ ያጤናል። የብሔራዊና ክልላዊ የጤና ተቋማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ግቦች በተሳካ መልኩ መተግበራቸው ላይ ሥርዓተ-ፆታ በቀጥታ ተፅህኖ ያሳድራል። በተዘዋዋሪ ደግሞ የማህበራዊ ልማት ሂደት ላይ ተፅህኖ ያሳድራል። ሥርዓተ-ፆታ የግለሰቦችና የህብረተሰቦች የምጣኔ ሃብታዊ፣ የማህበራዊና የዕለታዊ ህይወት አካል ነው። እንደዚሁም ለወንዶችና ለሴቶች በማህበረሰቡ የተሰጡ የተለያዩ ሚናዎችና ኃላፊነቶች አካል ነው።

ፆታ ቋሚና የማይቀያየሩ ሁሉም ማህበረሰቦችና ባህሎች የሚጋሯቸው በሥነ-ሕይወታዊ ባህሪዎች የሚገለጥ ሲሆን ሥርዓተ-ፆታ ግን በማህበራዊ ግንኙነት የታሪክ ሂደት ውስጥ ተፈጥሮ በማህበራዊ ተቋማት የሚጠናከር ነው። ሥርዓተ-ፆታ መነሻው ከሥነ-ሕይወት (biological) ልዩነቶች የሚመነጭ ቢሆንም ሁለቱ ፆታዎች መጫወት የሚገባቸውን ሚና በተመለከተ ግን ከሥነ-ልቦናዊና ከሥነ-ህይወት መለያዎች ያለፈ ነው። ምንም እንኳን የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶች በማሕበረተሰቡ የሚገነቡና አንድ ማሕበረተሰብ በአካላዊ ልዩነቶች እና ዝንባሌዎች፣ ፍላጎቶችና ችሎታዎቻቸው ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጠው ሚና ነው። የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶች እንደማይለዋወጡ የፆታ ባህሪያት ሳይሆኑ በታሪካዊና አንጻራዊ ማህበራዊ ትንታኔዎች ውስጥ የሚቀረጹና በጊዜ ሂደትና ከአንድ ባህል ወደ ሌላ የሚቀያየሩ እና የሚሻሻሉ ናቸው። እነዚህ ልዩነቶች የሚጸኑት በህብረተሰቡ ውስጥ ባሉ እሴቶችና ልማዶች ሲሆን እንደ ሃይማኖት፣ ትምህርት፣ ቤተሰብ፣ ፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ባሉ ተቋማት ተፈጻሚነት ያገኛሉ።

የሚፈጠሩት የተሳሳቱ አረዳዶች በሥርዓተ-ፆታ ማካተትና የሥርዓተ-ፆታን ሚዛን መጠበቅ መካከል የሚነሱ ግራ መጋባቶች፣ ወንዶችንና ሴቶችን አንድ ለማድረግ የሚደረግ ሙከራ ተደርጎ መወሰዱ፣ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ተጠቃሚ ይሆናሉ የሚል ስጋት፣ ወይም በአካባቢ ባህልና መዋቅር ውስጥ ጣልቃ ይገባል የሚሉ ናቸው። እነዚህ የተሳሳቱ አረዳዶች የሚያመላክቱት አሁንም የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ስራ ሁሉን አቀፍ እንዳይሆን አድርጎ የሚያስቀጥል መሆኑ ነው።

### ሥርዓተ-ፆታን ማካተት ምንድነው?

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት በቀላሉ ሲታይ ማንኛውም ተግባር በሰዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽህኖ፣ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች እና በአንጻሩ ተግባሩ የሚያሳድረው የተጽዕኖ በመለያየት በማስመር ተግባሩ ወንዶችንም ሴቶችንም እኩል በሚጠቅም መልኩ መቅረጽ ማለት ነው። የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚጠቅም ስትራቴጂ ነው። የሥርዓተ-ፆታ ትያዌን የተለየ ጥያቄ አድርጎ አይመለከተውም፤ ይልቁንስ የሥርዓተ-ፆታ ገጽታዎችን በሁሉም ተግባራት ውስጥ ግልጽ በሆነ መልኩ ማቀናጀት ነው።

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ሁሉም ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚኖራቸውን ፋይዳ በሁሉም የፕሮግራም ዑደት - ከዕቅድ እስከ ትግበራና ግምገማ ድረስ - ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል።

***ሥርዓተ-ፆታን ማካተት*** ማለት ማንኛውም የታቀደ የድርጊት መረሃ ግብሮች - ድንጋጌዎችን፣ ፖሊሲዎችን ወይም ፕሮግራሞችን ሁሉ ጨምሮ - በሁሉም ስፍራና በሁሉም ደረጃዎች ድርጊቱ በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅህኖ የመገምገም ሂደት ማለት ነው። የሴቶችንና የወንዶችን ስጋቶችና ልምዶች በሁሉም የፖሎቲካና የምጣኔ ሃብት እንደዚሁም የህብረተሰባዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዕቅድ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ምዘና ውስጥ የማይነጠል ገጽታ አድርጎ የማስገባት ስልት ነው። ይህም ወንዶችና ሴቶች እኩል ተጠቃሚዎች እንዲሆኑና የእኩልነት አለመኖር እንዳይቀጥል ማድረግ ነው። የመጨረሻ ግቡ የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ማረጋገጥ ነው።

## 2.2. የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ይዘቶች

1. ***የሥርዓተ-ፆታ ትንተና:*** የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ለጤና እቅድና ለፕሮግራም ንድፍ የሚያስፈልጉ ሂደቶችንና መረጃዎችን የሚያመነጭ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ቁልፍ ክህሎት ነው። በቀላሉ የማይገኙ መረጃዎችን ማግኘት የሚጠይቅ ወሳኝ ጥያቄዎችን ማንሳት ያካትታል (አባሪ ሰነድ 1ን ይመልከቱ) ።

የሥርዓተ-ፆታ ትንተና በማህበረተሰቡ ተቀባይነት ካገኙ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች (gender norms)፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሚመነጩ የእኩልነት እጦት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራትን ለመለየት፣ ለመገምገምና አቅጣጫ ለማሳየት ይጠቅማል። እንደዚሁም በወንዶችና በሴቶች፣ አልፎም በሴቶችና በሴቶች እና በወንዶችና በወንዶች መካከል የሃይል አለመመጣጠን ግንኙነቶችን፤ እንደ ጎሳ፣ ትምህርት ወይም የቅጥር ሁኔታን የመሳሰሉ የአውዳዊ ጉዳዮች መስተጋብር ችግሮችን ለመፍታት ይጠቅማል።

***የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች (gender norms) በጤና ላይ የሚያሳድሩ ተጽህኖዎች:*** ለምሳሌ የሴቶች በዝቅተኛ ማህበራዊ ደረጃ ላይ መገኘት ለአይነ ስውርነት የበለጠ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። የተጠኑ ጥናቶች በተመሳሳይነት ይሄንኑን ያመላክታሉ። በሁሉም የአለም አከባቢዎችና የዕድሜ ክልሎች ሲታይ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለአይነ ስውርነት በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ናቸው። ይሁን እንጂ ብዙ ሴቶች የአይን ቀዶ ጥገና ህክምና ለማግኘት ከወንዶች ጋር እኩል እድል የላቸውም። ምክንያቱም ብቻቸውን ወደ ህክምና ማዕከሉ መሄድ አለመቻላቸው፣ ሴቶች የቀዶ ህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን በተመለከተ ዋጋ አለመሰጠቱና ወይም የጤና መረጃ ማግኘት አለመቻላቸው ነው።

ወንዶች ልጆችን ጎጂ በሆኑ አመለካከቶች እይታ እና የሽግግር ሂደቶች በማሳለፍ ወንዶች እንዲሆኑ ማስተማር ሕይወታቸውንና የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ለአደጋ እንዲያጋልጡ ያደፋፍራቸዋል። ለምሳሌ በማህበራዊ ሂደት ውስጥ ወንዶች ልጆች ማልቀስ እንደማይገባቸው (ሴታሴት እንዳይባሉ) ይነገራቸዋል። እንደዚሁም ድብድብ ችግርን ለመፍታት ተቀባይነት ያለው የችግር አፈታት ዘዴ ነው ተብለው ይነገራሉ። ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት የመሸጋገር አንዳንድ ሥርዓቶች ሲጋራ ማጨስን፣ አልኮል መጠጣትን ወይም ከብዙ የወሲብ አጋሮች ጋር ጥንቃቄ የጎደለው ፆታዊ ግንኙነቶችን ማድረግን ያካትታሉ። እንዲህ ያሉት ማህበራዊ መስተጋብሮች የጤና አገልግሎት ከማግኘት መዘግየትን፣ አደንዛዥ ዕጾች፣ አልኮሆልና ሲጋራ መጠቀምን ያስከትላሉ። ይህ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ለሚቆዩ በሽታዎች እና ለሞትም ጭምር ያጋልጣል። እንዲሁም ኤች አይ ቪን ጨምሮ ለአባለዘር በሽታዎች ተጋላጭነት ይጨምራል።

**የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች በጤና ላይ ያላቸው ተፅህኖ**፡ የቤት ውስጥ ስራዎች የሴቶች ሥራ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ሥራዎቹ ጤናቸውን ለአደጋ ሊያጋልጡ ይችላሉ፡፡ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሃገሮች የሚኖሩ ሴቶች በምግብ ዝግጅት ወቅት ለከፍተኛ ጭስ ይጋለጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ለሚቆይ የሳንባ በሽታ የመጋለጥ ዕድላቸውን ከፍ ያደርጋል፡፡ ይህ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለበሽታ ተጋላጭ እንደሚያደርጓቸው የሚያሳይ ሌላ ምሳሌ ነው፡፡

የወንዶች ሥራ በሥራ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶች ከሥራ ጋር ተያያዥነት ላላቸው አደጋዎች ከሌሎች ሰዎች በበለጠ መልኩ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡ በሥርዓተ-ፆታ ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የሥራ ክፍፍል የወንዶች ሥራ እንደ ከባድ መኪና ሹፌርነት (ለበለጠ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ያጋልጣቸዋል) እና የግንባታ ሰራተኝነት (ከባባድ ማሽኖችን ሲያንቀሳቅሱ ለሚፈጠሩ አደጋዎች፣ ለድንገተኛ አደጋዎችና ከከፍታ ቦታ የመውደቅ አደጋዎች ያጋልጣቸዋል) ይመድባል፡፡ እነዚህ የወንዶች የሥራ ሚና በአደጋ ለሚፈጠር ቁስለት ትልቁን ድርሻ እንዲይዙ ያደርጋቸዋል፡፡

***የሥርዓተ-ፆታ ግንኙነቶች የጤና ተጽህኖ***፡ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚፈጠሩ ያልተመጣጠነ የሃይል ግንኙነቶች ለሥርዓተ-ፆታ ግጭቶች አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ሴቶች በቤታቸው አካላዊ፣ ፆታዊ እና አእምሮአዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ከቅርብ አጋሮቻቸው፣ በጠብ መካከልና በማህበረተሰብ መካከል ይገጥማቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከጥቃቱ የተነሳ ይሞታሉ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ደህንነቱ ባልተረጋገጠ (ሥጋት በተሞላበት) ሁኔታ ውስጥ ለመቆየት ይገደዳሉ፡፡

ያለ እድሜአቸውና ወይም ተገደው የሚዳሩ ወጣት ልጃገረዶች ያለእድሜ እርግዝና እና ጥንቃቄ ለጎደለው የድፍረት ወሲብ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ያለእድሜ ጋብቻ ወይም ተገዶ መደፈር ያለጊዜ እርግዝናና፣ ጥንቃቄ ለጎደለውና በጉልበት ለሚደረግ ወሲብ በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ከማድረጉም ባሻገር ለኤች. አይ. ቪ እና ለሌሎች የአባላዘር በሽታዎች መዛመት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ያለእድሜ ጋብቻ ልጃገረዶችን ከትምህርት ገበታ ያስወጣቸዋል (ይህ ደግሞ ትምህርት ካለመማር ጋር የሚያያዙ የጤና ጉዳቶችን ይጨምራል) ፤ በቤተሰብ ውስጥ ውሳኔ የመወሰን አቅማቸውን ይቀንሳል፤ በመረጃ ላይ የተመሰረተና ወቅቱን የጠበቀ የህክምና እርዳታ ለመፈለግ ወሳኝ የሆነውን የማህበራዊ ድጋፍ ማግኛ መንገዶችን ጭምር ሊገድብ ይችላል፡፡

እነዚህ እንግዲህ የወንዶች/የወንድ ልጆች እና የሴቶች/የልጃገረዶች ጤና ከሥርዓተ-ፆታ አኳያ ሲታይ እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ለማሳየት የተቀመጡ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

***ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ***፡- ሲባል ማንኛውም ዓይነት መድሎ፣ መለየት እና መገደብ (ለምሳሌ - ኢፍትሃዊ ወይም እኩልነት የሌለበት መስተንግዶ) በሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች ላይ የተመሰረተና በተለያየ ደረጃም ሆነ የእድሜ ክልል ያሉ ሴቶችንና ወንዶችን ሰብአዊ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ የሚገድባቸው ሲሆን ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በተሳሰተ መንገድ በሴቶችና በወንዶች ላይ፣ በማናቸውም የዕድሜ ክልልና በሃይማኖት፣ በመደብ፣ በማህበራዊና ምጣኔ ሃብት ደረጃ፣ በጎሳ፣ በፆታ፣ በቋንቋና ወ.ዘ.ተ. ላይ ለሚሰነዘሩ ጉዳጣዎች እውቅናን በመስጠት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

የሚከተሉት ወሳኝ ነጥቦች ሊታወሱ ይገባል፡-

- በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ አብዛኛውን ጊዜ ስለሴቶች እና ስለወንዶች በሚኖሩ ልማዳዊ ቅቡልነቶች ላይ የተመሰረተ ነው።
- በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ሊሆን ይችላል፤ ማለትም የሚታይ መድሎ (ቀጥተኛ መድሎ) ወይም ሚዛናዊ በሚመስሉ ህጎችና ፖሊሲዎች ላይ በመደገፍ በቡድኖች መካከል የሚፈጸሙ ማበላለጦች ሊሆን ይችላል (ቀጥተኛ ያልሆነ መድሎ) ።
- በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ ሁልጊዜ ሆን ተብሎ የሚደረግ ላይሆን ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ከተለመዱ ስሪቶችና (ቅቡልነት ያላቸው) ድርጊቶች የመነጨ ነው።
- ተቀባይነት ያገኙ አውዶችና ልማዶች እውነተኝነታቸው ወይም ፍትሃዊነታቸው ሳይጠየቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ ይችላሉ።
- ሴቶችን የሚገጥማቸው የሃብት ተደራሽነት ማጣትና መቆጣጠር አለመቻል አብዛኛውን ጊዜ ምንጩ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ ነው።
- በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ መድሎዎች በማንኛውም የእድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ጤና ላይ ጉዳት የሚያመጡበት ሁኔታዎች ሲከሰቱ የጤና ፕሮግራሞችና ፖሊስዎች ምላሽ መስጠት አለባቸው
- ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የማንበረሰብ ጤና ሰራተኞች በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ እንዴት በጤና ላይ ተጽህኖ ማሳደር እንደሚችል መረዳት አለባቸው። እንደዚሁም መድሎን ለመታገል የሚያስችሏቸውን በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ የተካተቱትን አንዳንድ ስልቶች ማወቅ አለባቸው።

የሴቶች ብልት ትልተላ (FGM) በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ ምሳሌ ነው። የሴቶች ብልት ትልተላ - ለህክምና ምክንያት ሳይሆን የሴቶችን ብልት አካል በከፊልም ሆነ በሙሉ ማስወገድ - ስለ ድንግልና እና ስለ ትዳር ታማኝነት ካለው ባህላዊ አመለካከት የተነሳ የሴቶችን ፆታዊ ፍላጎት የመቆጣጠሪያ ዘዴ ነው። በአንዳንድ አውዶች (ባህሎች) ልጃገረዶችን ለጎልማሳነት ህይወትና ለትዳር ለማዘጋጀት የሚደረግ ሥርዓት ነው። ይህን በማድረግ የሴቶች ወሲባዊነትን በተመለከተ ያሉ አመለካከቶችና እምነቶች፣ እንደዚሁም የሴቶች ዝቅተኛ ማህበራዊ ኑሮ የበለጠ እንዲጠናከር ያደርጋል። በዚህ ተጎጂ የሚሆነው ማን ነው? በአንዳንድ የአገራቱ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ናቸው። ይህ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎ በጤና ላይ የሚያሳድረው ተፅህኖ ምንድነው? ወዲያው የሚከሰቱ ውስብስብ የጤና ጉዳቶች ከፍተኛ ህመም እና የደም መፍሰስ፣ ሽንት ለመሽናት መቸገር እና የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ናቸው። ከጊዜ በኃላ የሚመጡ ጉዳቶች ውሃ የቋጠሩ እብጠቶች፣ እባጮች፣ ጠባሳ፣ ከሽንት ቧንቧ መሽንቆር የተነሳ ሽንት መቆጣጠር አለመቻል፣ በወሲብ ወቅት የህመም ስሜት፣ መካንነት፣ በወሊድ ላይ መቸገር፣ እና የተወለዱ ጨቅላዎች ሞትም ጭምር ናቸው።

በጤናው ዘርፍ የሚደረግ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦት በጤና እና በደህንት ላይ የሚያስከትለውን ችግር ይገመግማል። እንደዚሁም በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ በወንዶችና በሴቶች ቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ የጤና ነክ ልዩነቶችንና መበላለጦችን ለመረዳት አስተዋፅዖ ያደርጋል።

- ስጋቶችና እና ተጋላጭነት
- የበሽታ ሁኔታዎች፣ ህመሞችና ሥነ-ምግባር

- ፖሊሲዎች፣ ድንጋጌዎች እና ፕሮግራሞች በጤና ላይ የሚያሳድሩት ተጽህኖዎች

የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን ለመቆጣጠር ወሳኝ ሥራ ቢሆንም የጤና ስጋቶችንና ተጋላጭነትን መረዳትና ማጤን መቻል ደግሞ መረጃ ላይ የተመሰረተ የጤና ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ነው። ለጤና ስጋት የሚሆኑ ጉዳዮች ሲባል ከበሽታ አነሳስና ህመም ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች ወይም የበሽታና የመታመም መነሻ ምክንያቶች ማለት ነው። ለጤና ስጋት የሚባሉት ጉዳዮች - ለምሳሌ እንደ ትንባሆ መጠቀም - ከብዙ በሽታዎች ጋር ይያያዛሉ። እንደዚሁም አንዳንድ በሽታዎች - ለምሳሌ የልብና የደም ቧንቧ ህመም - ከብዙ ለበሽታ ከሚያጋልጡ ስጋቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። እነርሱን መረዳት የተጋላጭነትን ጉዳት ለመቀነስ ወይም ተጋላጭነትን ለማስቀረት እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችላል። ስለዚህ ለእንደዚህ ዓይነት የበሽታ ስጋቶች ተጋላጭነት አብዛኛውን ጊዜ ከሥርዓተ-ፆታ አመለካከቶች፣ ሚናዎች፣ እና ግንኙነቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። በመሆኑም በወንዶችና ሴቶች መካከል የተለያዩ ናቸው።

| *የጤና ስጋት መክንያቶች ምሳሌ* |
| --- |
| የማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ መደብ ወይም የማህበራዊ መደብ ምክንያቶች - እነዚህም ድህነት፣ ዕድሜ፣ ብሔር እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦት ናቸው። |
| መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ወይም የመገናኛ የቦታ ምክንያቶች (ለምሳሌ ከተማ ወይም ገጠር) - እነዚህ የመኖሪያ ቤት ሁኔታን ጨምሮ እና/ወይም የስራ ሁኔታ እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ተደራሽነት መኖር አለመኖር ናቸው። |
| የስነ-ልቦና ምክንያቶች ወይም የአኗኗር ዘይቤ ወይም የግል ምክንያቶች - ለምሳሌ ትንባሆን ወይም አልኮሆልን መጠቀም፣ አመጋገብ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴ |
| አካላዊ ምክንያቶች - ለምሳሌ ፆታ፣ የአካል አይነት፣ ዘረመል፣ የደም ግፊት እና በደም ውስጥ የሚገኝ የኮለስተሮል የስብ መጠን |

***ተጋላጭነት*** :- የሚያመላክተው ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች እና ሲስተሞች (አደረጃጀቶች) ለጉዳት የተመቻቹ ሲሆኑና ለስጋት ምክንያቶች ሲጋለጡ የመቋቋም ወይም ያለመቋቋም የአቅም ማነስ ማለት ነው።

የተደራሽነትና በሐብት በሃብት ላይ የመወሰን አቅም ልዩነቶች ለህመምና ለበሽታ የበለጠ ተጋላጭ ሊያደርግ ይችላል። የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘት እና ለበሽታ አጋላጭ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ ሴቶችን ለተላላፊ በሽታዎች እና በወሊድ ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ ያደርጉታል። ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦት የሚመነጩ በልጃገረዶችና በወንዶች ልጆች መካከል የሚደረጉ የአመጋገብ ልዩነቶች ልጃገረዶችና ሴቶች ላይ እንደ ደም ማነስ ላሉት በሽታዎች የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ ያደርጋል (አባሪ ሰነድ 2 ይመልከቱ)።

በጤና ላይ የሚደረግ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የተደራሽነት ልዩነቶችን በሚከተለው መልኩ አጉልቶ ያሳያል፦

- የጤና አገልግሎቶችና ሌሎች እንደ ትምህርት፣ የትራንስፖት እና የመረጃ አቅርቦት የመሳሰሉትን በሽታን ለመከላከልና ጤናን ለማጎልበት የሚያግዙ አስፈላጊ ሃብቶችን የማግኘት ልዩነቶችን
- ጤና-ነክ የሆኑ የውሳኔ ሰጪነት ሂደትን እና የጤና አሰራር ልዩነቶችን ያሳያል።

**ተደራሽነት-**

ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት የማግኘት እድል መኖሩና መጠቀም መቻል አዎንታዊ የጤና ውጤቶችን ለማግኘት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ የስራ ድረሻዎች እና ግንኙነቶች - የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦትን ጨምሮ - እንዲሁም የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና መጠቀም መቻል አለመቻል ሲፈተሽ ተደራሽነት ሲባል የአቅርቦት መኖር አለመኖርን (availability)፣ የመክፈል አቅምን ያገናዘበ መሆን አለመሆንን (affordability,)፣ አገልግሎቱ ለተጠቃሚው ተደራሽ መሆን (accessibility)፣ ሁሉን አቃፊ መሆን አለመሆኑን (accommodation) እና ጥራት ያላቸው የጤና አገልግሎቶችን መጠቀም መቻልን የሚያካትት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

***የህክምና አገልግሎት ማግኘት የመፈለግ ባህሪይ***፦ የሚያመላክተው አንድን የጤና ችግር ለመፍታት አንድ ግለሰብ የጤና አገልግሎት ለማግኘት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ማለት ነው። ይህ መደበኛ/ሞደርን እና አማራጭ የጤና አገልግሎቶችን ያጠቃልላል።

የሚከተሉት እውነታዎች የጤና አገልግሎት የመፈለግ ባህሪይ ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው ያመላክታል፦ የማህበራዊና ምጣኔ ሃብት፣ የቤተሰብ ድህነትን ጨምሮ የትምህርት ደረጃ፤ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ርቀት፤ የህመሙ አይነት፣ ጊዜው እና ጉዳቱ፤ ረጅም የወረፋ መጠበቂያ ጊዜ፤ አጥጋቢ ያልሆኑ ወይም አሉታዊ የሆኑ የአገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች አመለካከት፤ እና በቂ የሆነ የጤና ትምህርት ማግኘት አለማግኘት ሲሆኑ እነዚህ ከፆታና ከሥርዓተ-ፆታ ተጨማሪ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው።

***ተደራሽነት የሚያካትታቸው ነጥቦች***

***አቅርቦት***፦ አስፈላጊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶች መኖር አለመኖርና በበቂ ሁኔታ መገኘት አለመገኘት።

***የመክፈል አቅምን ያገናዘበ መሆን***፦ በሽተኛው ላገኘው አገልግሎት የመክፈል አቅምን የሚመለከት ሲሆን የነጻ አገልግሎትና ሌሎች ወጭን የመሸፈን ጉዳዮችንም ይጨምራል።

***ተደራሽነት*** ፦ የህዝብና የአገልግሎት መገኛ ቦታ፣ የመንገገርና ተዛማጅ ወጭዎች እና ሌሎችም ተገልጋዮች የጤና አገልግሎት ጋር ለመድረስና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያወጡት ወጭዎችን ያካትታል።

***አቃፊነት***፦ የጤና አገልግሎቶቹ ከተጠቃሚዎቹ የጊዜና የተግባቦት ፍላጎቶች ጋር የመጣጣም አለመጣጣም ሲሆን ለአገልግሎቱ ጥራት አስተዋፅዖ አለው።

***ተቀባይነት***፦ በአካባቢው ባህል አረዳድ ላይ በመመርኮዝ የአገልግሎቱና የማህበረሰቡ ወይም የግለሰቡ መጣጣም ወይም አለመጣጣም

***የህክምና አማራጮች***፦ የተለያዩ የጤና እክሎች የተለያዩ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና የማገገም ዘዴዎችን ይፈልጋሉ። ያሉት አማራጮች ራስን ከመንከባከብ ጀምሮ እስከ አማራጭ ህክምናዎች (ለምሳሌ የአካባቢ ባህላዊ ፈዋሾች) እስከ ጤና ተቋሞች፣ በማህበረሰብ ወይም በቤት የሚሰጡ መደበኛ ህክምናዎች ድረስ ሊለያዩ ይችላሉ።

የጤና አገልግሎት ሰጭዎች የህክምና አማራጮችን በተመለከተ የሚለግሱት ምክር ያታንና ሥርዓተ-ያታን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ይህም ከተለያየ ህብረተሰብ የሚመጡ ወንዶችና ሴቶች ላላቸው የጤና ፍላጎቶችና እውነታዎች አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

> ***ስለ ህክምና አማራጮች አስፈላጊ ነጥቦች***
>
> - በብዙ አውዶች በሽታን የመከላከል ፕሮግራሞች ማህበረተሰብን ያማከሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በማህበራዊና ባህላዊ ልማዳዊ ደንቦች ተጽህኖ ስር ናቸው፡፡
> - የህክምና እና የማገገሚያ አማራጮች አብዛኛውን ጊዜ ተቋማዊ ናቸው፡፡ ማለትም በሃብት አቅርቦት የሚወሰኑ ናቸው፡፡

***በጤና አገልግሎት መስጫ ውስጥ*** ሰዎች ከዚህ ቀደም ያላቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ***ልምምድ*** የወደፊት የህክምና አገልግሎት የማግኘት ፍላጎት ባህሪያቸው ላይ ተፅህኖ ያሳድራል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ልምምድ ከግለሰቦች ወይም ከቤተሰቡ አባል ወይም ከማህበረሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ አባወራ ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ የጤና አገልግሎት ገጥሞት ከሆነ የቤተሰቡ አባል ወደ ጤና ተቋሙ እንዳይሄድ ሊያበረታታ ወይም ሊከለክል ይችላል፡፡ በተለይም አገልግሎቱ ክፍያ ጋር የተያያዘ ከሆነ፡፡ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ በተለይ ሴቶች ውስን የውሳኔ መስጠት አቅም ያላቸው ከሆነ በራሳቸው ያልደረሰባቸውን ነገር ወደ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ላለመሄድና አገልግሎት ላለማግኘት ይህን እንደምክንያት ሊጠቅሱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አውድ የህክምና አገልግሎት የመሻት ባህሪይ ላይ፣ ህክምናን ሳያቋርጡ የመከታተል እና አጠቃላይ የአገልግሎት ጥራት አረዳድ ላይ ተጽህኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ መድሎ በሚታይበት መልኩ፣ ጉዳት በሚያስከትልበት መንገድ ወይም ውጤታማ ባልሆነ ሁኔታ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ወንዶችና ሴቶች ህክምናን ከመፈለግ ራሳቸውን እንዲቆጥቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የሥርዓተ-ያታ ልማዳዊ ደንቦችን፣ የስራ ድርሻዎችንና ግንኙነቶችን ከግምት ውስጥ የማያስገባ እና ባህልንና አግባብነትን ያላገናዘበ የጤና አሰጣጥ አውድ እኩልነት እንዳይኖር ምክንያት በመሆን የበለጠ የጤና አገልግሎት የመሻት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ሳይደርስ ሊቀር ይችላል፡፡

***የጤና መታወክ ማህበራዊ ውጤቶችና መዘዞቹ***- ይህ የሚገልጸው ጤናው የተቃወሰ ሰው ምን ሊገጥመው እንደሚችል ያመላክታል፡፡ ይኸውም ያ ወንድ ወይም ያቺ ሴት ሊያገግም/ልታገግም፣ ወይም የአካል ጉዳት ሊደርስበት/ሊደርስባት አለዚያም ሊሞት/ልትሞት ይችላል/ትችላለች፡፡ የጤና ችግር መዘዞች በጥቅል ሲታይ ለታማሚውም ሆነ በማሕበራዊ ትስስር ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች (ማለትም የቤተሰብ አባሉት፣ ጓደኞች ወይም ሰፊው የማህበረሰቡ አባላት) በሽታው የሚያስከትለው የምጣኔ ሃብታትና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያመጣው ጫና ማለት ነው፡፡ የጤና መታወክ ውጤቶች የምንላቸው የበሽታ ወይም የህመም መገለጫዎች እና ማገገምን፣ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ማለት ነው፡፡ የሥርዓተ-ያታ አመለካከት አብዛኛውን ጊዜ እንዴት እነዚህ የጤና መታወክ ውጤቶች በግለሰብና በቤተሰብ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽህኖ ሊቀይር ይችላል፡፡ የጤና ችግሮች ወይም ሁኔታዎች በማህበራዊ የትስስር ውስጥ በሚገኙ ሰዎች ሁሉ ላይ የምጣኔ ሃብታት፣ ማህበራዊ እና የአመለካከት መዘዞችን ያመጣሉ፡፡ በአንዳንዶች ላይ ከሌሎች በበለጠ መልኩ ጫና ያሳድራሉ፡፡

የጤና መታወክ ማህበራዊ ውጤቶችና መዘዞቹ ላይ ተጽህኖ የሚያሳድሩ ነገሮች የሚከተሉት ነጥቦችን ያካትታሉ፡-

- የገንዘብ ወጭዎች
- የጤና ችግሩ መጥናት/ቆይታና እና የጥልቀቱ መጠን
- የሚያስፈልገው የእንክብካቤ አይነት፣ አቅርቦቱና ተደራሽነቱ
- ማህበራዊ ትስስሮች
- መድሎ

***የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ለሚከተሉት ሥራዎች ሊውል ይችላል፡-***

- የጤና ፖሊሲዎች፣ ድንጋጌዎች፣ ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶችና ጥናቶች
- የተለዩ በሽታዎችና የጤና ችግሮች
- የሰው ሃብት እቅድ ዝግጅት፣ የበጀት ዝግጅት እና የአስተዳደር/የኦፕሬሽን እቅድ ዝግጅት ላይ

***የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የጤናውን ዘርፍ ውጤታማነትን በሚከተሉት መንገዶች ሊያሳድግ ይችላል፡-***

- የተለያዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድኖች በጤንነት የመኖር ያላቸውን መብት በማረጋገጥ
- በጤናው ዘርፍ የሚታዩትን ተጨባጭና ስልታዊ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ፍላጎቶችን በመለየት
- ሴቶችና ልጃገረዶች ጤናቸውን ለመጠበቅና ለማጎልበት ሲጥሩ የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች በማወቅና በመቀነስ
- የወንድ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች፣ የስራ ሚናዎች እና ግንኙነቶች የወንዶችንና የወንድ ልጆችን ጤና ሊጎዱ እንደሚችሉ በመረዳትና መፍትሔ በመስጠት
- የወንዶችንና የሴቶችን ተጨባጭ የጤና ፍላጎቶችና የህይወት ሁኔታዎችን ችላ የሚሉ አግባብነት የሌላቸው፣ ውጤታማ ያልሆኑ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም ፖሊሲዎችን በመቀነስ
- በጤናው ዘርፍ ውስጥ የሚታዩ የሥርዓተ-ፆታ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በመለየትና በመቀነስ
- ለየሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ አገልግሎቶችን (የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ደረጃ) እና ፕሮግራሞችን በመቅረጽና በመተግበር
- የጤና መረጃን፣አያያዝና አጠቃቀምን በማሻሻል

2. **የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት**፡- የማህበራዊ ፕሮግራም ኦዲት አካል ሲሆን እስካሁን የተገኙትን ውጤታማ ተግባራትን እና የበለጠ ሥራ የሚፈልጉትን ክፍተቶችን የሚያስስ ነው፡፡ ምንም እንኳን በሥራ ላይ ለማዋል በተለያዩ ጉዳዮች እንደ ፋይናንስ አቅም የሚወሰን ቢሆንም የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት የአንድ ተቋም አሁናዊ አቋም (ስራዎች እንዴት እንደሚሰሩ፣ በማን እንደሚሰሩ፣ ማን እንደሚወስን) የሚፈተሽበት ሁለንተናዊ አቀራረብ ነው፡፡ ድርጅቱ ተልዕኮውን (ማለትም ፕሮግራሞቹንና ፕሮጀክቶቹን) እንዴት እንደሚፈጽም ያጤናል፡፡

በመሆኑም የፕሮግራሞችንና የኦፕሬሽኖችን የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭነት አቅምን ያጎለብታል። የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት የጤና ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ እና ኦፕሬሽኖች ፍትሃዊነትና እኩልነት በሴቶችና በወንዶች መካከል እንዲሰፍን የሥርዓተ-ፆታ አካታችነትን ተቋማዊ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማወቅ የተለያዩ መሳሪያዎችን ይጠቀማል። የጤና ፕሮግራሞች ስኬታማነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወሰነው የተለያዩ ስልቶችና እርምጃዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበራቸው ላይ ነው። የኦዲት ዋናው አርዕስት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ለቀጥተኛ ተጠቃሚዎች አገልግሎቱ መድረሱን ማረጋገጥ ነው።

3. **ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ**፡- ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ በበጀት ዝግጅት ሂደት ውስጥ ሥርዓተ-ፆታ አካታችነትን ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው። ይህም ማለት ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ የበጀት ግምገማ፣ በእያንዳንዱ የበጀት ዝግጅት እርከን የሥርዓተ-ፆታዊ እይታዎችን ማካተት፣ የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማጎልበት ገቢዎችንና ወጭዎችን እንደገና ማዋቀር ማለት ነው። የሥርዓተ-ፆታ ማካተትን ለማረጋገጥ የሚደረግ የበጀት አመዳደብ በዋናነት የሚጠቅመው የበጀት አመዳደብ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ለመገምገም ነው። ይህም ለምሳሌ ከብዜር፣ ከመደብ፣ ከመልክዓ ምድራው አቀማመጥ፣ ከእድሜ ወይም ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን ለማስቀረት ያግዛል። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደቡ ቴክኒክ ወይም የበጀት ውሳኔው የሚወሰድበት የአስተዳደር እርከን (በብሔራዊ፣ ክልላዊ ወይም አካባቢያዊ ደረጃ ሊሆን ይችላል) ላይ በመመርኮዝ አቀራረቡ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ግብ ሊለያይ ይችላል። ነገር ግን ዓላማዎቹ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ የመረጃ አደረጃጀትን፣ ፖሊሲዎች በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅህኖዎች ግምት ውስጥ ማስገባትን፣ እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ጥረትን ያካትታሉ።

ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ አንድ ወጥ ዘዴ የለውም። የተለያዩ አውዶችን፣ ፖለቲካው አሰራሮችን፣ የፖሊሲው ትግበራ የሚከናወንበትን የአስተዳደር እርከኖችን እና የምጣኔ ሃብታዊ እድገት ደረጃዎችን ከግምት በማስገባት የተለያዩ አቀራረቦችን መጠቀም ይቻላል። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ቁልፍ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው። የአሰራር ሂደቶችና ወሳኔ አሰጣጥ ግለጸኝነት፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፣ ቀጣይነትን እና የረጅም ጊዜ አቅጣጫን ከግምት ውስጥ ማስገባትን ያጠቃልላል። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ለየት ያለ የፖሊሲ ጉዳይ ላይ ወይም አጠቃላይ የበጀት አሰራር ሂደቱ ላይ ወይም በሁለቱም ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል። ቁልፉ ነጥብ ግን የበጀት አመዳደቡና በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚያሳድረው ተጽህኖ ግልጽ መሆኑ ነው። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ሂደት ውስጥ የተለያዩ የአሰራር ቴክኒኮች ሥራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እነርሱም፡- ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ የፖሊሲ ሂደቶች፣ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የጥቅምና የተጠቃሚዎች ትንተና፣ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የመረጃ አደረጃጀት፣ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለማጤን የወጭዎችና የገቢዎች የሥርዓተ-ፆታ አዲትን ማካሄድ፣ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚያሳድረውን ተፅህኖ መገምገም፣ እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ግቦችን መጠቀም ናቸው።

ለምሳሌ በቀበሌ ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ለመጠቀም (የአካበቢ የጤና አገልግሎት እቅድ ውስጥ)፣ አንድ አዲስ ሆስፒታል ለወንዶችና ለሴቶች ሊሰጥ ያዘጋጀውን የአገልግሎት እቅድ መገምገም ይቻላል። ግምገማውም የህዝቡን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ብቻ ሳይሆን የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዳይጠቀሙ እንቅፋት የሚሆኑ ምክንያቶችን ነቅሶ ማውጣትን ይጨምራል። እንደዚሁም አዳዲሶቹ አገልግሎቶች እንቅፋቶቹን ለማስወገድ እንዴት እንደሚረዱ ጭምር መታየት አለበት። እንዲህ አይነቱ ትንተና ሁሉን አገልግሎቶች የሚነካ ነው። ማለትም የህዝብ የትራንስፓርት አገልግሎት መኖር አለመኖርን፣ በአካባቢው የሚገኙ የስራ እድሎችን፣ የትምህርትና የሕጻናት ጤና እንክብካቤ (የሌሎችም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንክብካቤ) ተቋማት መኖር አለመኖርን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

## 2.3. የሥርዓተ-ፆታ ማካተትና ማህባራዊ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የጤና ወሳኝ ጉዳዮች የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅህኖ ለመቀነስ የሚረዱ ዘዴዎችን ለመጠቀም ያስችላል። ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖር ችግሮችን ለመፍታት ለየት ያሉ ስትራቴጂዎች ያስፈልጋሉ። የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት በሁሉም ዘርፎች ተቋማዊ እንዲሆን ያለመ አለማቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘ ስትራቴጂ ነው። ሥርዓተ-ፆታ በወንዶችና በሴቶች ጤና ላይ የሚያሳድረውን ከፍተኛ ተጽህኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖርን ለማስወገድ በጤናው ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችና ፖሊሲዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት ግድ ይላል።

ሥርዓተ-ፆታ ከእነዚህ መጠነ-ሰፊ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው። በወንዶችና በሴቶች መካከል የተለያዩ የጤና ውጤቶችን በሚፈጥር መልኩ ሥርዓተ-ፆታ ከሌሎችም ወሳኝ የጤና ጉዳዮች ጋር ይያያዛል። ወንድ ወይም ሴት መሆን በጤና ባህሪይ ላይ፣ በጤና ሁኔታ ላይ፣ በጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ተጽህኖ ያሳድራል። ከኃይል አንጻር፣ ከኑሮ ሁኔታ አንጻር፣ ከሥነ-ህይወታዊ አወቃቀር፣ ከማህበራዊ መስተጋብር እና በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚኖራቸው ሚና አንጻር ወንዶችና ሴቶች ይለያያሉ። እነዚህ ልዩነቶች መኖራቸውን መቀበል፣ መተንተንና ስልታዊ በሆነ መልኩ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።

በጤናው ዘርፍ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት በአጠቃላይ ሶስት ዋና የትግበራ ዘዴዎችን በሚከተሉት ደረጃዎች ይጠቀማል፦

1. በተቋም፣ በፕሮግራም እና በአፕሬሽን ደረጃ
2. በቤተሰብ እና በግለሰብ ደረጃ
3. በዘርፈ ብዙ ዘርፎች ደረጃ - ይህም ከሰው ልጅ ጤና ወሳኝ ማህበራዊ ጉዳዮች (ጤና እና ደህንነት፣ የውሃና የንጽህና አገልግሎቶች አቅርቦት፣ አካባቢ፣ ትምህርት፣ ሃብት፣ ጥበቃ፣ አመጋገብ፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ዕድሜ፣ ወ.ዘ.ተ.) አንጻር ሊታይ ይገባል

## 2.4. የሥርዓተ-ፆታ ማካተት፡ በጤናው ዘርፍ አዲስ የአሰራር ዘዴ

“ጤና ለሁሉም” እንደሚባለው ዓይነት የጤና ፍትሃዊነት ግብን ለማሳካት የሚደረገው እርምጃ መጀመር ያለበት “ሁሉም” የሚለው ቃል አንድ አለመሆኑን ወይም አንድ ዓይነት አይደሉም የሚለውን መሰረታዊ ሐሳብ በመቀበል መሆን አለበት፡፡ በአገራት እና በክልሎች መካከል የጤና ሁኔታ መለያየትና መበላለጥ በስፋት እውቅና አግኝቶ በጤና መረጃ አደረጃትና ሥነታሪኮች ውስጥ ይመዘገባሉ፡፡ በማንኛውም እርከን የሚሰሩ የጤና ሰራቶኞች በሃገራቸው ህዝቦች መካከል ላሉት ልዩነቶች እውቅና መስጠትና መለየት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህንም ልዩነቶች በዜዴና በአግባብ ምላሽ ሊሰጡበት ይገባል፡፡ በመሆኑም በአንድ ህዝብ ውስጥ በሚገኙ ቡድኖች መካከል በተቻለ መጠን ጥሩ የጤና ሁኔታ እንዲኖር ለማስቻል የተለያዩ ስራዎችን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም የተለመዱ አሰራሮች ይህን ለማሳካት የተሻሉና ውጤታማ አሰራሮች እንዳልሆኑ መረዳትም ያስፈልጋል፡፡ አለማቀፍ የጤና እኩልነት እጦትን እና ወንዶችንና ሴቶችን የሚገጥሙ የተለያዩ የጤና ፍላጎቶችና ግድድሮሾችን ለመፍታት ከትርክት በዘለለ መልኩ አዳዲስ አስተሳሰቦችና አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎች ያስፈልጋሉ፡፡

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ልዩነቶችንና መበላለጦችን ለመለየት ይረዳል፡፡ የጤና ዘርፉም ዓላማዎቹን ለማሳካት አሰራሩን እንዴት መለወጥ እንዳለበት ያመላክታል፡፡ ይህን የሚያደረገው በሁለት ተቀራራቢ ዘዴዎች ነው፡- በጤና ፕሮግራሞች ትግበራ ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት እና በተቋም ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት ናቸው፡፡

### *1. በጤና ፕሮግራሞች የትግበራ ዕቅድ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት*

መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎች - ማለትም እኩልነት፣ ተሳታፊነት፣ መድሎ ያለመኖር - ላይ በመመርኮዝ የጤና ፕሮግራም አቀራረቦች የጤና ችግሮችን ለመፍታት በዘዴ የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ይጠቀማሉ፡፡ ይህም በሴቶችና በወንዶች ጤና ላይ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሚያሳድሩትን ተፅህኖ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡

በጤና ፕሮግራሞች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፡-

- የጤና ችግሮች እንዴት በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ወንዶችና ሴቶች እንደዚሁም ቡድኖች ላይ በተለየ መልኩ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይቃኛል፡፡
- ሴቶችን በማብቃትና ትኩረት የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ እየተፈፀመ ያለውንና ለረጅም ጊዜ የቆየውን መድሎ ለመፍታት ይጥራል፡፡
- የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች እንዴት በወንድ ባህሪ እና የጤና ውጤቶች ላይ ተጽህኖ እንደሚያሳድሩና ይሄ ደግሞ ወንዶች የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና እንዴት እንደሚቀርፅ ያጤናል፡፡
- የእድሜን፣ የማሕበራዊና የምጣኔ ሃብት፣ የብሔር ስብጥር፣ የራስን በራስ ማስተዳደር፣ የማብቃት፣ የወሲባዊነትና ወ.ዘ.ተ. ጉዳዮችን ለማጤን ሰፋ ያሉ የፍትሃዊነት አቀራረቦችን ይጠቀማል፡፡
- አግባብነት ያለው፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ የጤና ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ፖሊሲ ቀረፃና አገልግሎት አሰጣጥን ለማስፈን አስፈላጊ መረጃዎችን ያቀርባል፡፡

### *2. በተቋም ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት*

ይህ ደግሞ የድርጅቶችን የአሰራር ስርዓት ያጤናል። የፖሊሲ አቀራረፅና አስተዳደር፣ የአጀንዳ አቀራረጽ፣ አስተዳደራዊ ሥራዎች እና አጠቃላይ ተያያዥ ጉዳዮችን ያጠናል። ተቋማዊ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት አንድን ተቋም ለጤና ፕሮግራሞቹ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማስታጠቅ ማለት ነው። እንደዚሁም የተቋሙ የአሰራር ዘዴና ሂደቱ በሰው ሃይል አመዳደብ፣ በስራ ድርሻና አስተዳደር የሥርዓተ-ፆታ አለመመጣጠንን እንዳያስፋፋ ያደርጋል። ተቋማዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የመዋቅር ለውጥና የማህበረሰቡ የጤና አጀንዳ ለውጥን በማምጣት ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሴቶችንና የወንዶችን ተሳትፎ በማረጋገጥ በማህበረሰቡ ጤና ተቀዳሚ ጉዳዮችና ተግባራት ላይ እንዲወስኑ እና እንዲተገብሩ ማስቻል ነው።

ተቋማዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የሰው ሐብት፣ ፋይናንስና የድርጅቱ ፖሊሲዎችን (የቅጥር ምልመላና የሰራተኛ ጥቅማ ጥቅም ፖሊሲዎችን ጨምሮ) በማቀናጀት የሚከተሉትን ያረጋግጣል፡-

- የሥራና የህይወትን ሚዛን መጠበቅ፤
- በሰራተኛ አመዳደብ የፆታና የሥርዓተ-ፆታ ሚዛንን መጠበቅ፤
- የሥራ ዕድገት ሲኖር እኩል እድል መስጠት፣ እና
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ወንዶችና ሴቶች ሰራተኞችን እኩል ተሳታፊ የሚያደርግ ስርዓት መዘርጋት ናቸው።

ተቋማዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት የሥርዓተ-ፆታን በስትራቴጂያዊ አጀንዳዎችና ፖሊሲዎች፣ እንደዚሁም በድርጅቱ የሥራ ክትትልና ምዘና ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በሚከተሉት መንገዶች ሊያረጋግጥ ይጥራል፡-

- በእቅድ ስራ ውስጥ (በተቋማዊና ፕሮግራማዊ እቅዶች ውስጥም ጭምር) ሥርዓተ-ፆታን ከግምት ውስጥ ለማስገባት የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችንና ሂደቶችን መዘርጋት፣
- በአማካሪ አካላት፣ በአንቀሳቃሽ ኮሚቴዎችና ተመሳሳይ አካላት በኩል የሥርዓተ-ፆታና የጤና ተጠያቂነት ዘዴዎችን መዘርጋት
- በፕሮግራማዊ አሰራር ውስጥ የሚያስፈልጉ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያስችል የሰራተኛውን አቅም መገንባት

ስለዚህ፣በጤና አሰራር ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት ሲባል ተቋማዊም ሆነ ፕሮግራማዊ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ስራ ላይ ያተኩራል። ይህን የሚያደርገው አለማቀፋዊና ብሔራዊ የጤና ፓሊሲዎች በሁሉም የአሰራር ገጽታዎቻቸው ሥርዓተ-ፆታን አቀናጅተው በመስራት በአገር-አቀፍ ደረጃ አቅምን ገንብቶ ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጤና አለመመጣጠን ችግሮችን በመፍታት ነው።

## 2.5. በጤና ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ዘዴ

- ***የቁጥጥር ዘዴ (Regulatory approach)*** ፦ በአገር-አቀፍ ደረጃ የበሽተኞችን መብቶች ማስጠበቅ ወይም የማህበረሰብ ዘርፍ ተቋማት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እንዲያረጋግጡ ሃላፊነት መስጠት ይችላል። እንዲህ አይነቱ ሃላፊነት የጤና ሚኒስቴር የእኩልነት

አለመኖርን የሚያበረታቱ ክፍተቶችን በመለየት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማጎልበት እንዲሰሩ ያስገድዳቸዋል።

- ***ድርጅታዊ ዘዴ*** *(Organizational approach)* ፦ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን ለይቶ መፍትሔዎቹንም መጠቆም ላይ የሚያነጣጥር በጤና አሰራር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የታለመ ዘዴ ነው። ለምሳሌ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ በመንግስት ወጭዎች ላይ በማተኮር የበጀት ውሳኔዎች በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚያሳድረውን ተጽህኖ ግልፅ ማድረግ አንዱ የድርጅታዊ አሰራር ዘዴ ነው።
- ***መረጃዊ ዘዴ*** *(Informational approach)* ፦ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦትን ሰዎች እንዲያውቁ በማድረግ ረገድ የመረጃ ሚና ምን መሆን እንዳለበት ላይ ያተኩራል። ለምሳሌ፣ ሥርዓተ-ፆታን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ የጤና መረጃዎች በጤና ጉዳዮችና ጤናን በሚመለከቱ ወሳኝ ማህበራዊ ጉዳዩች ላይ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታዩትን ቁልፍ ልዩነቶችን ለይቶ በእነዚያ ዙሪያ የፖሊስ ለውጦች እንዲደረጉ ይጥራል።

## 2.6. ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት

ከጤና ሚኒስቴር ራእይና ተልዕኮ አኳያ፣ የሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዋና አላማው በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ሕዝቦች የጤና ደረጃና ደህና መሆንን በማሻሻል አራቱን ምሶሶዎች በመጠቀም ማንም ወደኃላ አለመቅረቱን ማረጋገጥ ነው።

### *1. ሁሉ አቀፍ የጤና ሽፋን እንዲረጋገጥ የተሳለጠ እምርታ ማሳየት*

ይህ ስትራቴጅያዊ አላማ በፊት ያለምንም የፋይናንስ ጫና የተገኙትን ጥራት ያላቸውና ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦት ስኬቶችን የሚያዳብር ነው። ይህ በሶስት ስትራቴጂያዊ የአሰራር መንገዶች ሊሳካ ይችላል።

1. ወሳኝ የጤና አገልግሎቶች በተለይም ጥራታቸውን የጠበቁ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎቶች በህዝቡ አቅራቢያ እንዲገኙ ማስቻል ነው
2. ግለሰቦችና ማህበረተሰቡ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ወሳኝ የጤና አገልግሎቶች ሽፋን መኖሩን ማረጋገጥ ነው። ይህ በአንጻሩ ሶስት በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውሉ ክፍሎች፣ የፍላጎት ትንተና፣ እና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ያካትታል። እነዚህም ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን እንዲረጋገጥ እየተወሰዱ ያሉ እምርታዎችን የሚከታተል ተግባራዊ አሰራር ነው።
3. ሰዎች በፋይናንስ እጥረት እንዳይጎዱ ይከላከላል። በሌላ አባባል፣ ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረታዊ የጤና ፓኬጅ አገልግሎቶች በተጠቃሚዎች ላይ የፋይናንስ ጫና ሳያሳድሩ ተደራሽና ማህበረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ይጥራል።

ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት እንዴት ይቻላል የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ ነው።

ከሥነ-ህይወት አንጻር ወንዶችና ሴቶች የተለያዩ የጤና ፍላጎቶች አሏቸው። ይሁን እንጂ ከተጨባጭ የማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች የሚመነጩ የአኗኗር ዘይቤዎችና በማህበረሰቡ

የተመደቡ ሚናዎች በጤና ላይ የራሳቸው ተፅህኖ አላቸው። ስለዚህ ስትራቴጅያዊ የጤና ፕሮግራሞችና ተቋማዊ እቅዶችን ለመቅረጽ የሚያስችል የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴን ለመተግበር በፆታ የተደራጀ የጤና መረጃን ማግኘት የመጀመሪያ እርምጃ ነው። የጤና ፍትሃዊነት ትንተና በተለምዶ በማህበራዊና በምጣኔ ሃብታዊ ልዩነቶችና ምላሾቻቸው ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፣ በማህበራዊ የጤና ፕሮግራሞች፣ ምርምሮችና ፖሊሲዎች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችን መጠቀም አላስፈላጊ፣ መከላከል የሚቻሉና ፍትሃዊ ያልሆኑ የጤና ደረጃ ልዩነቶችን ለማስወገድ ያስችላል። ይህ ደግሞ ፆታና ሥርዓተ-ፆታን እንደ ቁልፍ የጤና እኩልነት እጦት መለያ ነጥቦች አቀናጅቶ ከመጠቀም ይጀምራል። ማለትም በሴቶችና በወንዶች ቡድኖች (የእድሜ፣ የብሔር፣ የማህበራዊና ምጣኔ ሃብት፣ የመኖሪያ ክልሎችና በፆታ ቡድኖች) መካከልና በእርስ በእርሳቸው ውስጥ የሚታዩ ልዩነቶችን ስልታዊ በሆነ መልኩ በሥርዓተ-ፆታ ትንተና ውስጥ ማካተት ማለት ነው። በዚህም የጤና እኩልነት በሁሉም አሰራር ውስጥ ይሰርፃል።

ለምሳሌ፣ ወንዶች ሥራ-ነክ ለሆኑ በሽታዎች፣በሥራ ላይ ለሚያጋጥሙ ድንገተኛ አደጋዎች/ጉዳቶች፣ ሲጃራ ለማጨስ፣ አልኮሆል ለመጠጣት እና ሌሎች ለደባል ሱስ አስያዥ አመሎች የተጋለጡ ናቸው። ወንዶች ለልብና የደም ስር በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው (ወንዶችን በመግደል ቅድሚያ ስፍራ የያዘ በሽታ ነው)። ከወሊድ ጋር የሚያያዙ የሴቶች የጤና ስጋቶች በእርግዝና ወቅት ለደም ማነስ በሽታ፣ ለምግብ እጥረት፣ ለጉበት እንፌክሽን፣ ለወባ፣ ለስኳር በሽታና ለሌሎችም ህመሞች የበለጠ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ፣ የመሰረታዊ የጤና ፓኬጅ ተጠቃሚዎች ሥርዓተ-ፆታ-ነክ የጤና አገልግሎትና መረጃ ሲያገኙ ከጤና አገልግሎት አቅርቦትና ሽፋን ያለገንዘብ ወጪ ጫና ተጠቃሚና ትኩረት የሚሰጣቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

### 2. ሰዎችን ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች መከላከል

ይህ ስልታዊ ዓላማ የጤና ዋስትናን በማሻሻል ማህበረሰቡን ሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ከሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች፣ ግጭቶች፣ በተደጋጋሚ እና ሳይታሰብ ከሚከሰቱ በሽታዎችና ወረርሽኞች፣ አደጋዎች፣ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑት የጤና ችግሮች ከሚከሰቱ አዳዲስ የጤና ስጋቶች እንዳይጠቁ መከላከል ነው። በተጨማሪም ህብረተሰቡን ከድንበር-ዘለል በሽታዎች በመከላከል የዜጎችን የጤና ዋስትና ማረጋገጥ ላይ ያለመ ነው።

የማህበረሰብ የድንገተኛ የጤና አገልግሎቶች በዋናነት የሚያተኩሩት ሁሉንም ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና ችግሮችን በተመለከተ ዝግጁነት፣ መከላከል፣ ቀድሞ መለየት፣ መቆጣጠርና ከበሽታው ተፅህኖ ማህበረሰቡ እንዲያገግም መርዳት ናቸው። እነዚህም የወረርሽኝ መከሰት፣ የሥነ-ምግብ-ነክ ድንገተኛ ሁኔታዎች፣ እና በተፈጥሮ የሚከሰቱና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚያስከትሏቸው የጤና ችግሮችን ያጠቃልላሉ። ድንገተኛ የጤና ችግሮች የሚባሉት በፍጥነት ህክምና ካላገኙ ሞት ወይም ቋሚ ጉዳትን የሚያስከትሉ ማናቸውም የጤና ችግሮች ናቸው።

እንደዚሁም ወንዶችና ሴቶች የአካባቢ መበከል የሚያሳድረውን ተፅህኖ በተመለከተ ተጋላጭነታቸው ይለያያል። ለምሳሌ፣ ድርቅ ሲከሰት ለመጠጥ፣ ለማብሰል፣ ንፅህናን ለመጠበቅ የሚያስፈለገውን ውሃ የማግኘት እድል ይቀንሳል። በተጨማሪም የምግብ ዋስትና እጦትን እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ታዳጊ አገራት ላይ ያስከትላል። ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ የጤና አደጋን ያስከትላል።

ከምግብ ዋስትና አለመረጋገጥና የምግብ እጥረት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የጤና ችግሮች ከወንዶችና ከወንድ ልጆች ይልቅ ሴቶችንና ልጃገረዶችን የበለጠ ይጎዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሴቶችና ልጃገረዶች አብዛኛውን ጊዜ ለቤተሰቡ ውሃ የመቅዳት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በድርቅ ወቅት ውሃ ለመቅዳት ረጅም መንገድ መጓዝ ስለሚጠበቅባቸው ድርቁ የበለጠ ጫና ያሳድርባቸዋል፡፡ እንደ ድርቅና ዝቅተኛ የዝናብ መጠን የመሳሰሉ የአካባቢ የአየር ለውጥ ሲከሰት የሴቶች የሥራ ጫና ይጨምራል፡፡ ውሃን ለመቅዳት ከሚደረግ ተጨማሪ ጫና ባሻገር ማገዶንም መልቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም፣ የእለት ኑሮን ለማሸነፍ ከሚሰሩት ተባራሪ ስራዎች በተጨማሪ ነው፡፡

የአካባቢ የአየር ሁኔታ መቀየር አንዳንድ በተዋህሳን የሚተላለፉ በሽታዎች የሚያዳርሱት መልክዓ ምድራዊ ስፋትና የሚከሰቱባቸው የወቅቶች ዑደት እንዲፋጠኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን አንዳንድ ቡድኖች ከሌሎች በበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡

ሴቶች ለታመሙ የቤተሰብ አባላት እንክብካቤ የማድረግ ሚናቸው ለበሽታ የመጋለጥ እድላቸውን ያሰፋል፡፡ ስለዚህ ከበቂ ትንተና በኋላ ሥርዓተ-ፆታን ከበሽታ መከላከልና ከድንገተኛ የጤና አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት ግዴታ ይሆናል፡፡

### 3. የወረዳ ትራንስፎርሜሽን

ፆታና ሥርዓተ-ፆታ አስፈላጊ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሁለቱም በወንዶችና በሴቶች ለበሽታ ስጋቶች መጋለጥ ላይ፣ በጤና መረጃና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ፣ የጤና አገልግሎት ማግኘት የመፈለግ ባህሪ ላይ፣ የህክምና አማራጮች፣ እና በጤና አገልግሎት መስጫዎች ውስጥ በሚገጥሟቸው ልምምዶች ላይ ተፅህኖን ያሳድራሉ፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ በሴቶችና በወንዶች ጤና ውጤቶች ላይ ልዩነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችንና የጤና ሁኔታ አለመመጣጠንን የማጤን ስልታዊ ሂደት በመምራት ውስጥ ፕሮግራማዊና ተቋማዊ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ካደረጉ ልዩነቶች ጀርባ ያሉትን ምክንያቶች ለማወቅ ዘልማዳዊ የጤና ትንተና ዘዴዎች ብቁ አይደሉም፡፡ በብዙ መልኩ፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የጓሮ አትክልትን ተንከባክቦ ከማሳደግ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከመሬት በላይ የሚታየው አካል ስሮች በአፈር ውስጥ እንዴት ተጠላልፈው እንዳሉ አይናገርም፤ ወይም ስሮቹ በአፈር ውስጥ አጥብቀው ያያዙት ነገር ምን እንደሆነ አይገልጽም፡፡ እያንዳንዱ የጤና ፕሮግራም አተገባበር ከታች ወደ ላይ ሊፈተሽ ስለሚገባ፣ ወደ ክልላዊና ብሔራዊ ደረጃ ከመሄድ በፊት የአካባቢውን ሕዝብ እውነታዎች መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም እንዴትና ለምን ኃይል፣ መብትና ተደራሽነት አስፈላጊ በሆኑ የጤና-ነክ ሃብቶች ዙሪያ በህዝቡ መካከል እኩል ባልሆነ መልኩ ሊከፋፈሉ እንደቻሉ የሚያሳዩ መሰረታዊ ምክንያቶችን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ስለዚህ በወረዳ ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ የጤና አሰራሮች ትግበራ ሥርዓተ-ፆታን ካላገናዘበ አሰራር ወደ አቃፊ አሰራር ከማሸጋገሩም በላይ፤ ቤተሰቦችና ግለሰቦች የለውጥ ወኪሎች ስለሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ እንዲሳካ ያደርጋል፡፡

### 4. የጤና ሥርዓቱን ምላሽ ሰጭነት ማሻሻል

ሥርዓተ-ፆታ በሁሉም የጤና አሰራር ክፍሎች ውስጥ መካተት አለበት፡፡

*አመራርና አስተዳደር፡-* እ.ኤ.አ በ2019 50 በመቶ የሚኒስቶሮች ካቢኔን፣ እንደዚሁም 38.8 በመቶው የህዝብ መወሰኛ ምክር ቤት መቀመጫዎችን በሴቶች በማስያዝ ሃገሪቱ ሴቶችን በማብቃት ረገድ ተጨባጭ እምርታዎችን አሳይታለች፡፡ የጤና ሚኒስቴር በሴት ከሚመሩ የሚኒስቴር መስሪያቤቶች አንዱ ነው፡፡ ሴቶች የውሳኔ ሰጭነት ቦታዎችን ለመያዝና በራስ መተማመንን ለማጎልበት በሥርዓተ-ፆታ ውስጥ የሚታዩትን ልዩነቶች ለማስወገድ ትምህርት ወሳኝ ሃይል ነው፡፡ ሴቶች በተለይ በእርግዝናና ልጅ በማሳደግ ወቅት በሙያቸው እንዲቀጥሉ የሕይወትና/የኑሮና የሥራ መመጣጠን ወሳኝነት አለው፡፡ እያንዳንዱ ተቋም የህጻናት እንክብካቤ ማዕከል እንዲያቋቁም የሚያስገድደው ድንጋጌ ሴቶች እና ያለትዳር አጋር ልጅ የሚያሳድጉ ወንዶች በሙያቸው እንዲያድጉ ያስችላቸዋል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ለማካሄድና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በተለያዩ ከፍተኛ የቴክኒክ አመራር ደረጃዎችና የፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ደረጃዎች እንዲሰፍን ለማድረግ የጤና ዘርፉ የሥራ ሁኔታ መመቻቸት ብዙ እድሎችን ፈጥሯል፡፡ በክልል ጤና ቢሮዎችና በፌዴራል ጤና ኤጀንሲዎች ደረጃ የጤና ፖለቲካዊ አመራር ውስጥ የሚታየው ለወንዶች ያደላው የመጀመሪያው ዕደት የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሊፈተሽ ይገባል፡፡

ስለዚህ የድርጅት ባህሉ ሥርዓተ-ፆታ-ነክ የሆኑ ጉዳዮችና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በተመለከተ ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን ሊያመጣ ይገባል፡፡ ይህም ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሥራ ቦታ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ፣ መድሎን ማስቀረት፣ የግል ደህንነትን ማረጋገጥ እና ቢያንስ የስራ እና የህይወት ሚዛንን መስጠበቅ አለበት፡፡ በተጨማሪም የሥርዓተ-ፆታ አወቃቀርና አቅም (gender architecture and capacities) - በጤናው ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታን የማቀናጀት ዘዴና የሥርዓተ-ፆታ አቅምን መዘርጋት ማለት ሲሆን - በጤና ፕሮግራሞች/ትግበራዎች እና ተቋማት የሥርዓተ-ፆታን ለማካተት ይጠናከራል፡፡ ይህም በትብብርና በአጋርነት የሥርዓተ-ፆታ አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

*ፋይናንስና በጀት፡-* የማህበረሰብ የውጤቶች/ሽቀጦች በተለያየ ደረጃ ለሴቶችና ለወንዶች ፍጆታ ይውላሉ፡፡ ማለትም “ወንዶችና ሴቶች ከማህበራዊ ግብይቶች እኩል ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡” ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ እነዚህ ልዩነቶች እንዳሉ ለመቀበልና ልዩነቶቹን ለማጥበብ የሚደረግ ሙከራ ነው፡፡ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ወይም ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭ የሆነ የበጀት አመዳደብ የመንግስት የወጭ ምደባ ላይ ያተኮሩ የተለያዩ አቀራረቦችን ያቀፈ ነው፡፡ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ለየት ባለ መልኩ ለአንዱ ፆታ የሚመደብ (ለምሳሌ የሴቶች ፕሮግራም በጀት) ሃብት ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የበጀትና የገንዘብ ውሳኔዎች በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚያመጡት ተጽህኖ ከሥርዓተ-ፆታ አንፃር እንዲተነተኑ ይጠይቃል፡፡ የአንድ አገር ዓመታዊ በጀት በሚቀጥለው ዓመት መንግስት ለምን ለምን ስራዎች ቅድሚያ መስጠት እንደፈለገ የሚናገር ሰነድ ነው፡፡ ይህም ከተፎካካሪ/ተገዳዳሪ ጉዳዮች መካከል ተቀዳሚ ለሆነው የገንዘብ ሃብት መመደብን ያካትታል፡፡ እንደዚሁም ገቢ እንዴት እንደሚሰበሰብ ያወሳል፡፡ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ሲኖር ከፍላጎቶች እና ከልምምዶች አንፃር የሚታዩ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን የማህበረሰብ ዘርፍ የወጭ በጀት በሂደቱ

ውስጥ በግልጽ ትኩረት እንዲሰጣቸው ያደርጋል። ስለዚህ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ የሚከተሉት ጉዳዮችን ይወስናል፦ የወንዶችና የሴቶች ልዩ የሆኑ ፍላጎቶች፣ በወቅቱ ያሉት እርምጃዎችና ፖሊሲዎች የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶች ምን ያክል እንደሚያሟሉ፤ እና የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶች አለመመለስን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል። በተጨማሪም፣ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ዓላመው ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችን አስመልክቶ የመንግስት የወጭና የገቢ ፖሊሲዎች በህብረተሰብ ጤና ላይ ከሚያስከትለው ተጽህኖ አንጻር የመንግስትን ተጠያቂነትን ለማሳደግ ነው። ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ የበጀት አመዳደብ ብዙ ጊዜ ከጤና ፖሊሲ ጋር ግልጽ በሆነ መልኩ ሲያያዝ አይስተዋልም። ነገር ግን የበጀት አሰራሩ እንደ በሥርዓተ-ፆታ የተከፋፈለ መረጃ እና ሌሎች የሥርዓተ-ፆታ ቁልፍ መረጃ ጠቋሚዎችን የሚጠቀም እና እነርሱም ከጤና ፖሊሲ ጥያቄዎች ጋር የሚያያዙ ቢሆኑም ማለት ነው።

***ለጤና አገልግሎት የሚያስፈልግ የሰው ሃብት፦*** የጤና ሚኒስቴር የሠራተኛ ምደባ ፖሊሲዎቹንና የምልመላ አሰራሮቹን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ሲከታተል ቆይቷል። ይኸውም በፕሮግራሞቹና በተቋሞች ሁሉ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በሁሉም እርከን ለማስፈን ነው። የሥርዓተ-ፆታ ሚዛንን ለማስጠበቅና በተለይ በከፍተኛ የስልጣን እርከኖች የሚታዩትን ክፍተቶችን ለመሙላት ከሚወስዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች በተጨማሪ በሰራተኛ አመዳደብ ፖሊሲ ዙሪያ አሁንም ማሻሻያ እንደሚያስፈልግ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት-ነክ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህ ማለት ደህንነቱ የተጠበቀና በአክብሮት የተሞላ የሥራ አካባቢን ማመቻቸት፣ ለወሲባዊ ጥቃትና እንግልት ምንም ትዕግስት አለማሳየት፣ የስራና የህይወት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣ የወሊድ እረፍት ማመቻቸት (ለአባትም ለእናትም)፣ የሕጻናት ማቆያ ማዕከሎችን ማመቻቸት፣ የትዳር አጋር ቅጥርና ሌሎችም ተመሳሳይ እርምጃዎችን ከግምት ማስገባት አለበት። የእድሜ ወሰን ገደብን የሚያስቀምጥ የሰራተኛ እድገት ፖሊሲ መስፈርት በሥርዓተ-ፆታ አድቮከሲ ጥረት ከሁለተኛው የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ እንዲወጣ ተደርጓል። በአንጻሩ በህገመንግስቱ የተረጋገጡ ለሴቶች ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ የሚሰጥ ፖሊሲ (affirmative actions) በግልፅ እንዲጠናከር ተደርጓል።

***የመድኃኒትና መድኃኒት-ነክ አቅርቦቶችና ቴክኖሎጂዎች፦*** የመድኃኒትና መድኃኒት-ነክ አቅርቦቶችና ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ ምርትን መሰረት ካደረገ ትኩረት ሕመምተኛውን መሰረት ወዳደረገ ትኩረት የተደረገው ስትራቴጂያዊ ሽግግር ትልቅ ልዩነት ያመጣል። ይኸውም በግዥ፣ በክምችት ሂደት፣ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች ተጠቃሚዎች ጊዜውን ጠብቆ በማከፋፈል ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ይህ የአሰራር ለውጥ በሎጅስቲክና አቅርቦት ሰንሰለት አስተዳደር ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ለማካተት የተወሰደ እርምጃ ነው። የመድኃኒትና መድኃኒት-ነክ አቅርቦቶች፣ የምርመራና ህክምና መሳሪያዎች ቴክኖሎጂዎች ለሴቶችና ለወንዶች፣ ለልጃገረዶችና ለወንዶች ልጆች የተለያዩ ናቸው። ስለዚህ ሥርዓተ-ፆታንና እድሜን ያገናዘቡ ፊላጎቶች በፕሮግራሙ ውስጥ መካተት አለባቸው። የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ በአፍሪካ ምላሽ ሰጭና ቀልጣፋ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለት አስተዳደር ኤጀንሲ ለመሆን አንጊ ራዕይ አስቀምጧል። ይህ ራዕይ ሊሳካ የሚችለው ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተጋመደ የምላሽ ሰጭነት እቅድ፣ ትግበራና ቁጥጥር አሰራር ከዘረጋ ብቻ ነው።

በቤተ-ሙከራ የማይመረትና የወንዶችንም ሆነ የሴቶችን ህይወት የሚያድን መተኪያ የሌለው የሰው ልጅ ስጦታ ደምና የደም ውጤቶች ናቸው። **የደም ባንክ አገልግሎት** ደምን ፈቃደኛ ከሆኑ ለጋሾች ሰብስቦ ለሰዎች ይለግሳል። በዚህ ሂደት ደም የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ

ደምና የደም ውጤቶችን እንደየአስፈላጊነቱ ይወስዳሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ አሰራር ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት አይቀሬ ነው፡፡ የአቅርቦቱንም (የለጋሾችም) ሆነ የፍላጎቱን (ሥርዓተ-ፆታን መሰረተ ያደረጉ ፍላጎቶች) የአሰራር ጎን ለማሻሻል ፍትሃዊ የሆኑና ደህንነታቸውን የጠበቁ የደም አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑ በፍትሃዊነት ትንተና ውስጥ ሥርዓተ-ፆታ ተቀዳሚ ወሳኝነት አለው፡፡

ከመደበኛው ዘመናዊ ህክምና በተጨማሪ የባህል መድኃኒቶች ለአካል፣ ለአዕምሮ፣ ለማህበራዊ እና ለመንፈሳዊ ጤና በወንዶችም በሴቶችም ይወሰዳሉ፡፡ እንደዚሁም በሁለቱም ለአገልግሎት ይቀርባሉ፡፡ የባህላዊ መድኃኒቶችን ደህንነትና ፈዋሽነት በጥናት ማረጋገጥ ሁለተኛው የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን እቅድ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ፕሮግራሞች አንዱ ነው፡፡ ለተሻሉ የጤና ውጤቶችና በተጠቃሚዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ሥርዓተ-ፆታ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት ጥራቱን የጠበቀ የባህል መድኃኒት ዝግጅት ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ትንተና ያስፈልገዋል፡፡

***ምርምሮችን ያካተተ የጤና መረጃ ሲስተም*** ፡- የጤና ተግባቦት፣ መልዕክቶችና የተለያዩ የብዙሃን መገናኛዎች በማህበረሰብ ጤና ስራ ውስጥ በጤና-ነክ ጉዳዮችና የመከላከያ እርምጃዎች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠርና የጤናማ ባህሪ አመለካከትን (ከጤና አገልግሎት አሰጣጥና አድቮከሲ ዘመቻዎች ጋር ተያይዞ) ለማስፋፋት ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ እንደዚሁም የጤና ግቦችን ለማሳካት ቆራጥነትን ለማሳየት ወሳኝ ናቸው (በፖሊሲዎችና ንግግሮች ሊሆን ይችላል)፡፡ ሁለቱም አይነት ተግባቦቶች የተዛባን የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ከማጠናከር፣ ጎጂ የሆኑ ሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶችን ከማደፋፈር መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ በአንጻሩ ጤናን የሚጎዱ ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የተዛቡ አመለካከቶችን የሚቃወሙና የጤናን መልዕክት የሚያስተላልፉ ንግግሮች፣ ምስሎችና የብዙሃን መገናኛዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ እንዳንድ የተግባቦት መልዕክቶች ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ካደረጉ ማግለሎችና ከማናናቅ ንግግሮች የሚመነጭ መድሎን ሊያደፋፍሩ ይችላሉ፡፡

እነዚህም፡- ወንዶችን እንደ ቁጡ፣ ልቅ የወሲብ ባህሪ ያለቸውና ስሜታቸውን የሚደብቁ አድርጎ ማቅረብን ያካትታል፡፡ ሴቶችን ደግሞ በእናትነት አውድ ውስጥ ብቻ ማውሳት፣ በቤትና በማህበረሰብ ጉዳዮች ውስጥ ሴትን የበይ ተመልካች አድርጎ ማሳየት ናቸው፡፡ ስለዚህ ሥርዓተ-ፆታን በማስመልከት የተዛቡ አመለካከቶችን የሚያደፋፍሩ መልዕክቶችና ምስሎች የታቀደውን የግንዛቤ ማሻሻያ ስራንና ስለ አንድ የጤና አርዕስት እውቀት ለማጎልበት የሚደረገውን ጥረት ሊጸረሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የማሳካት ሂደት ውስጥ በሁሉም የተግባቦት እርከኖች ሥርዓተ-ፆታን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡

እቅድ ለማውጣትና ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ ***በፆታ የተከፋፈለ መረጃና ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ አመልካች መረጃዎች*** መሰረታዊ መስፈርቶች ናቸው፡፡ የሥርዓተ-ፆታ እና የጤና መረጃዎች ሰፋ ያሉ ቢሆኑም የሚከተሉት ቁልፍ ነጥቦች ግን ከግምት መግባት አለባቸው፡-

- የጤና መረጃን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የሚያመቻቹ አመልካች ነጥቦችን ለመምረጥ የትንተና ማዕቀፉ የሚያመች መሆን አለበት፡፡
- በፆታ የተከፋፈለ የጤና መረጃን ማደራጀትና መተንተን ለሥርዓተ-ፆታ ትንተና ቁልፍ መስፈርት ነው፡፡ ሁኔታዎች ሲፈቅዱ እንደ ጎሳ፣ የትምህርት ደረጃ የመሳሰሉ የተለያዩ የመረጃ አደረጃጀቶችም በከፍተኛ ሁኔታ ይበረታታሉ፡፡

- የጤና አመልካች መረጃዎች ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። ተገቢ የሆነ ክፍፍል ሊኖራቸው ይገባል። የተለዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድኖችን የሚመለከቱ ቁልፍ የሥርዓተ-ፆታና ጤና-ነክ ጉዳዮችን ያካተቱ መሆን አለባቸው።
- የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ለማካሄድ የጤና መረጃ ማግኘት ብቻውን በቂ አይደለም። ሥርዓተ-ፆታን በጤና እቅድ ዝግጅትና ፕሮግራም ቀረጻ ውስጥ ለማቀናጀት የሥርዓተ-ፆታ መረጃ ያስፈልጋል።

በጤና እቅድ ዝግጅትና ፕሮግራም ቀረጻ ውስጥ፣ በተለይም ለተጨባጭ ሁኔታ ትንተና፣ ለተግባር ዝግጅት፣ ለቁጥጥርና ምዘና የምዘና ማዕቀፎች ወሳኝ ናቸው። የተለያዩ ማዕቀፎችን መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን ሁሉም ወደ አንድ ድምዳሜ ይጠቁማሉ። ይሄም፣ የጤና መረጃ በበሽታ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮረ አለመሆኑ ላይ ነው። ይልቁንም፣ ለምሳሌ፣ እንደ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች፣ የጤና ሁኔታ እና ውጤቶችን ያካትታል። ስለዚህ የጤና መረጃ የመመዝገቢያ ስርዓት ወይም በሽታዎችን ከመቁጠር የዘለለና እንደ ሥርዓተ-ፆታ ያሉ ሰፋ ያሉ የማህበረተሰብ ጤና ጉዳዮችን የሚዳስስ ነው።

የሥርዓተ-ፆታ ምርምር ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ አስፈላጊ ነው፡ (1) በአብዛኛው የመድሎ አሰራሮችን ይገልጣል - በወንዶች ወይም በሴቶች ላይ የሚደረጉ መድሎዎችን፤ (2) በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታዩ የእኩልነት እጦቶችን በመለየት ላይ ያነጣጥራል፤ (3) በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ሰፋ ያሉ ልምዶችን የማንጸባረቅ እድሉ ሰፊ ነው። በመሆኑም የህብረተሰቡን ፍላጎቶችና ክፍተቶችን ጠቅለል ባለ መልኩ ለመዳሰስ አቅም ይኖረዋል። (4) በአለማቀፍ ጉባኤዎችና ስምምነቶች ውስጥ ፈቃድ ተሰጥቷል (CEDAW, Beijing Platform for Action)።

ስለዚህ የሥርዓተ-ፆታ እይታን ከሁሉም ምርምሮችና ፈጠራዎች ጋር ማቆረኙቱ አስፈላጊ ነው። ይህም ሥርዓተ-ፆታ እንደ ሁሉአቀፍ ጉዳይ በሁሉም የጥናቱ ሂደቶች ውስጥ እንዲካተት ያስፈልጋል። በጤና ዘርፍ ስር ለሚደረጉ የምርምርና በኢኖቬሽን ቡድንና በአመራር መዋቅር ውስጥ ለወንዶችና ለሴቶች በተመጣጠነ መልኩ እንዲሳተፉና እል እድል እንዲኖራቸው ሆኖ የምርምር ይዘቱ የሥርዓተ-ፆታን ምልከታ/ገጽታን ማካተት ይኖርበታል። እንደዚሁም ጥናቱ የሥርዓተ-ፆታ ገጽታንም ያካተተ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ፣ ህጋዊ ኃላፊነቶች የተቀመጡ ቢሆኑም፣ ሃሳቦችም ቢሰጡም፣ በሁሉም የእውቀት መስክ በሚደረጉ የምርምርና የቴክኖሎጂ ልማት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ መዛባት ይታያል። በወንዶች አመለካከት ላይ ያመዘነ እና የማህበራዊ እኩልነት እጦትን የሚያስፋፋ በመድሎ የተሞላ የሃይል አወቃቀር ይታያል። ሁሉም ምርምሮችና ጥናቶች በጥናቱ ሃሳብ ዝግጅት፣ የጥናቱ ዘዴ ቀረጻ፣ በጥናቱ ሂደት እና የጥናት ውጤቱን አሳትሞ ማሰራጨት ሂደት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ገጽታን ሊያካትቱ ይገባል። የትምህርትና ጥናት ተቋማት - አካደሚያን ጨምሮ - ለሥርዓተ-ፆታ ምርምር የተሻለ እድል መስጠትና በትምህርታቸው ውስጥ የሥርዓተ-ፆታን ማካተት እንደሚገባ ማስተማር አለባቸው። ለምሳሌ ለምርምር የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች ሲሰጡ የሥርዓተ-ፆታ ገጽታ በጥናቱ የሃሳብ ሰነዶች (proposals) ውስጥ መካተቱን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ አለባቸው።

***የጤና መሰረተ-ልማት፡*** የጤና አገልግሎቶች ለተጠቃሚዎች የመልክዓ ምድራዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸው የጤና መሰረተ-ልማት ወሳኝ ነው። የአንዳንድ የጤና መሰረተ-ልማቶች የመዋቅር ዝርጋታዎች ከሚጠበቀው ጥራት ባታች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለጤና ሰራተኞችም ሆነ ለወንዶችና ለሴቶች ተጠቃሚዎች ምቹ አይደሉም። እንደ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት፣ የመጸዳጃ

ቤቶች፣ ተግባቦት እና የውሃ አቅርቦቶች ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። የህክምና ተቋማት እንደ መሆናቸው መጠን የወንዶችና የሴቶችን፣ የልጃገረዶችና የወንዶች ልጆችን ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ያሰገቡ መሆን አለባቸው።

## 2.6 የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ተጨባጭ እርምጃዎች

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ሰዎች የጤና አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ለማሳካት ወሳኝ ነው። ሰዎችን የማህበረሰብ ጤና ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ማዕከል ያደርጋቸዋል።

ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችና የእኩልነት እጦቶች በወንዶችና በሴቶች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽህኖ ያሳድራል። እነዚህ በአጠቃላይ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎች ይባላሉ። በአብዛኛው በጥያቄ መልክ የሚዘጋጁ ሲሆኑ፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎች ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችና የእኩልነት እጦቶች በጤና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽህኖ ስልታዊ በሆነ መንገድ ለማጥናት ያስችላሉ። ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ካደረጉ የጤና ልዩነቶች በስተጀርባ ያሉትን ምክንያቶች ለማወቅ የተለመዱ የጤና ትንተና ዘዴዎች ብዙ ጊዜ በቂ አይደሉም። ዘዴዎቹ (የአሰራር መሣሪያዎቹ) የሥርዓተ-ፆታ የእኩልነት አለመኖር እንዴት፣ ዬትና ለምን በጤና ላይ ጎጂ ተጽኖ እንደሚያሳድሩ በመለየት በቂና ተገቢ ምላሾችን ለመስጠት ያግዛሉ። ስለዚህ ከታች ወደ ላይ በመፈተሽ፣ ወደ ብሔራዊ ደረጃ ከመሄድ በፊት የአካባቢውን ህዝብ እውነታዎች መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህም እንዴትና ለምን ሃይል፣ መብትና ተደራሽነት አስፈላጊ በሆኑ የጤና-ነክ ሃብቶች ዙሪያ በህዝቡ መካከል እኩል ባልሆነ መልኩ ሊከፋፈሉ እንደቻሉ የሚያሳዩ መሰረታዊ ምክንያቶችን ለማወቅ ያስችላል።

**በጤና ፕሮግራሞች ላይ የተመሰረተ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ትንተና** ሥነ-ህይወታዊ ጉዳዮች እንዴት ተቀባይነት ካላቸው የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች (ወይም ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች) ጋር መስተጋብር በመፍጠር በሴቶች፣ በወንዶችና በማህበረተሰባቸው ጤና ላይ ተፅህኖ እንደሚያሳድሩ ለማወቅ ተጨባጭ አሰራሮችን ያመላክታል። በሌላ መልኩ በተቋማዊ ጉዳዮችም ላይ - በተለይም በእቅድ ዝግጅትና የጤና ፕሮግራም ቀረጻ ላይ - ተጽህኖ አለው። የጤና ፍትሃዊነት ትንተና በተለምዶ በማህበራዊና በምጣኔ ሃብታዊ ልዩነቶችና ምላሾቻቸው ላይ የሚያተኩር ቢሆንም፣ የማህበረሰብ ጤና ፕሮግራሞች፣ ምርምሮችና ፖሊሲዎች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችን መጠቀም አላስፈላጊ፣ መከላከል የሚቻሉና ፍትሃዊ ያልሆኑ የጤና ደረጃ ልዩነቶችን ለማስወገድ ያስችላል። ይህ ደግሞ ፆታና ሥርዓተ-ፆታን እንደ ቁልፍ የጤና እኩልነት እጦት መለያ ነጥቦች አቀናጅቶ ከመጠቀም ይጀምራል። ማለትም በሴቶችና በወንዶች ቡድኖች (የእድሜ፣ የብሔር፣ የማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ፣ የመኖሪያ አካባቢ ቡድኖች) መካከልና በእርስ በእርሳቸው ውስጥ የሚታዩ ልዩነቶችን ስልታዊ በሆነ መልኩ በሥርዓተ-ፆታ ትንተና ውስጥ ማካተት ማለት ነው። በዚህም የጤና እኩልነት በሁሉም አሰራር ውስጥ ይሰርፃል።

## ሥርዓተ-ፆታን የማካተት እርምጃዎች

### *እርምጃ 1፡ የሥርዓተ-ፆታ ማህበራዊ አፈጣጠር*

የፆታ፣ የሥርዓተ-ፆታ፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ የፍትሃዊነት እና የመድሎን ትርጉም ማወቅ የሥርዓተ-ፆታ ሃሳብ እንዴት እንደሚፈጠር፣ ተጠብቆ እንደሚቆይና እንደሚጠናከር ለመረዳት ይጠቅማል።

### *የስርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ የስርዓተ ፆታ ፍትሃዊነት እና የጤና እኩልነት*

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት በጤና ጉዳዮች ላይ ሲተገበሩ የሚከተሉትን ልዩነቶች ማወቅ አስፈላጊ ነው፡-

- የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ማለት የበሽታ ስርጭት በወንዶችና በሴቶች መካከል እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ማለት አይደለም
- የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ማለት ወንዶችና ሴቶች ሙሉ መብታቸውን ለመጠቀምና ጤናማ ኑሮ የመኖር፣ ለጤና ልማት የማበርከት እና ከውጤቶቹም ተጠቃሚ የመሆን መብታቸውን ለማወቅ እኩል እድል ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው።
- የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ለአገልግሎቶችና ለሃብት የተገደበ ተደራሽነት ላላቸው የሴቶችና የወንዶች ቡድኖች ማገዝ የሚያስችሉ የተለዩ እርምጃዎችን መቅረጽ ያስፈልጋል።
- የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት ማለት በወንዶችና በሴቶች መካከል ፍትሃዊ ያልሆኑ እና ማስቀረት የሚቻሉ የእኩልነት አለመኖርን በጤና ደረጃ፣ በጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት እና በጤናው ስራ ግብረ-ሃይል አበርክቶአቸው ማዳላት እንዳይኖር የማድረግ ሂደት ነው።

### *እርምጃ 2፡ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎቹ/መሣሪያዎቹ እና ጽንሰ-ሃሳብና ዘዴዎቹ*

የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ለመተርጎም እና ለሥርዓተ-ፆታ ትንተና የሚረዱ የተለያዩ ምክንያቶች፣ ዘዴዎች/መሳሪያዎችና ጽንሰ ሃሳቦችን ለማስቀመጥ ይረዳል። ከሚከተሉ ጉዳዮች የሚመነጩ የእኩልነት አለመኖር ችግሮችን ለመፍታት ተግባሮችን ይለያል፣ ይመዘናል፣ እንደዚሁም አቅጣጫን ያሳያል፡-

- የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች
- በወንዶችና በሴቶች መካከል ወይም በእርስ በርሳቸው ውስጥ የሚታዩ የኃይል ግንኙነት አለመመጣጠን፤ እና
- ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ከሥርዓተ-ፆታ ጋር ያላቸው መስተጋብር (ለምሳሌ ብሔር፣ የትምህርት ደረጃ ወይም የስራ ቅጥር ሁኔታ) ።

የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ለጤና እቅድ ዝግጅትና የፕሮግራም ቀረጻ መረጃን ለማደራጀት፣ ለማቀናጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆነ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ቁልፍ ክህሎት ነው። መረጃን በቀላሉ ከማይገኝባቸው ቦታዎች ቆፍሮ የማግኘት ቁልፍ ጥያቄዎችንም ያካትታል። ከታች የተዘረዘሩ አይነት መርሆዎችንም ይከተላል፡-

i. ፆታ ሥርዓተ-ፆታ አይደለም
ii. ሴቶችና ወንዶች የተለያዩ ናቸው

iii. ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በወንዶችና በሴቶች ላይ በተመሳሳይ መንገድ ተፅህኖ አያሳድሩም
iv. ሥርዓተ-ፆታ እንዴት የጤና ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ለመረዳት የተለያዩ ማስረጃዎች ያስፈልጋሉ፡፡
v. ቀጣይነት ያላቸው የሥርዓተ-ፆታ ቆራጥነቶች ወሳኝ ናቸው፡፡

***ሴቶችን ማብቃት የሥርዓተ-ፆታ ትንተና አካል ነው፡-*** ይህ ማለት ትኩረት ያልተሰጣቸው ቡድኖች የጤና መብታቸውን እንዲጠቀሙበትና እንዲያሳኩ አቅማቸውን የማጠናከር ሂደት ነው፡፡ ሴቶችን በማብቃት እንዴት በጤና ችግር የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎችን መሰባጠር እንደሚቻል ከአባሪ መረጃ 2 ይመልከቱ፡፡ እንደዚሁም ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የማብቃት እርምጃዎችን እና የሴቶች መብቃት ግምገማ አመላካች ነጥቦችን በተመለከተ የአለም ጤና ድርጅት እንደ ሃሳብ ያቀረባቸውን ነጥቦች ከአባሪ መረጃ 2 ይመልከቱ፡፡

### *እርምጃ 3፡ ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የእኩልነት አለመኖር ማስረጃዎች*

የሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ የእኩልነት አለመኖር ከሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎችና የሥርዓተ-ፆታ ሚና እሴቶች ጋር በሥራ ጫና፣ ትምህርት ለመማር እኩል እድል ባለማግኘት፣የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሃብቶችን በማግኘትና በመቆጣጠር እንደዚሁም ስልጣን በማግኘት እድል ዙሪያ እንዴት እንደሚያያዙ ያብራራል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን ከሚያስረዱ አለማቀፋዊና ብሔራዊ መረጃዎች ጋር ያስተዋውቃል፡፡ ማስረጃዎቹ የሚገኙት እየተተነተነ ያሌለውን የጤና ጉዳይ በበለጠ ለመረዳት ከሚጠቅሙ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ከተዘዋዋሪ የመረጃ ምንጭ፣ ከህትመት፣ አሐዛዊና (quantitative) እና ዝርዝር (qualitative) መረጃዎችን በመጠቀም ከሚደረጉ ጥናቶች ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም፣ የጤና አገልግሎት መሰረት ያደረጉ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ከዋና ዋና የባለድርሻ አካላት ጋር ቃለ-መጠየቅ ማድረግ፣ የእውቀት፣ የአመለካከትና የድርጊቶች ጥናት ከማካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

### *እርምጃ 4፡ በተቋም የሥርዓተ-ፆታ ማካተት*

ይህ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ጽንሰ ሃሳብን እና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችን/መሳሪያዎችን ያስተዋውቃል፡፡ እንደዚሁም ሥርዓተ-ፆታን ለማካተት የሚረዱ የተለያዩ ተግባሮችንና ስትራቴጂዎችን ያስተዋውቃል፡፡

### *እርምጃ 5፡ ሥርዓተ-ፆታን እና ጤናን ማቆራኘት*

ሥርዓተ-ፆታ በጤና ሁኔታና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽህኖ ለመረዳት በተወሰኑ በሽታዎች (የጤና ሁኔታዎች) ላይ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎችን (አባሪ ሰነድ 2) በመጠቀም በጥያቄ ሂደት ይጀምሩና ከአግድም ዛቢያ ጉዳዮች (ሥርዓተ-ፆታ-ነክ ምልከታዎች) ጋር

መስተጋብር ያለውን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥን ይጠቀሙ፡፡ የአግድምና የቁልቁል ዛቢያዎቹ መቋረጫ (መገናኛ) በጤናው ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ለማካሄድ ማዕቀፍ ያበጃል፡፡ እንደዚሁም ማን እንደሚታመም፣ መቼ፣ ዬትና ለምን እንደሚታመም በተመለከተ የሚታዩ ልዩነቶችና መበላለጦችን ለመለየት ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ስለመረጃው ለሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎቹ የተሰጡትን መልሶች በመጠቀም የጤና ዘርፉ ምን እያደረገ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና፡-

### ዓላማ አለው

የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ማድረግ ለፖለቲካ ፍጆታ የሆነ ሐረግ በሪፖርት ለማቅረብ አይደለም፡፡ እንዲሁም የልማድ ወይም የባህል ወይም የእምነት ተቋማትን ሥራ ለማፋለስ/ለመለወጥ የታሰበ አይደለም፡፡

የማኅበረተሰብ ጤና ተዋናዮች የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን ሲያካሂዱ የሚከተሉትን ለመፈጸም ነው፡-

- ለወንዶች ወይም ለሴቶች የጤና ስጋቶችን የሚጨምሩ ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለማስተናገድ
- ተቋማዊ አሰራሮችን በመለወጥ የማህበረተሰብ ጤና ተግባሮች በሚጎለብቱበት፣ በሚተገበሩበትና ክትትል በሚደረግባቸው መልክ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማስፋፋት

### አሳታፊ ነው

ጎጂ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶችን ለመታገል ለምን አንዳንድ ድርጊቶችና እምነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ምላሾችና መፍትሔዎችን ለመስጠት በማህበረተሰቡ ውስጥ ከሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ጋር በትብብር መስራት ይጠይቃል፡፡

በጤና ፕሮግራሞች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተሻሉ ዘዴዎችን ለመለየት ከተለያዩ መስኮች ከመጡ ከሙያ ቡድኖችና ባለሙያዎች የተወጣጡ ሴቶችና ወንዶችን ማማከርና ማሳተፍ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ደግሞ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሠንጠረዥን መሙላትን ይመለከታል፡፡ እንደዚሁም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን የሚያስችሉ ለምሳሌ የሰው ሃብት ፖሊሲዎች ማጎልበቻ ዘዴዎችን ይመለከታል፡፡

### በአጋርነት ላይ የተመሰረተ ነው

ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈንና ለሴቶችና ለወንዶች የጤና ውጤቶችን ለማሻሻል ከሌሎች የሙያ ዘርፍ አጋሮች ጋር መስራት ወሳኝ ነው፡፡ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሠንጠረዦን መረጃ ሲያደራጁ በስራዎት ውስጥ መሪ ሆነው ጤናን እንደመድረክና የመግቢያ በር በመጠቀም የማህበራዊ እኩልነት እጦትን ይታገሉ፡፡ ከተቋማዊ አሰራር ረገድ፣ ማንኛውም የጤና ሚኒስቴር የስራ ክፍል ወይም ቢሮ ውጤታማ በሆነ መልኩ ብቻውን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖር ችግርን ሊፈታ አይችልም፡፡ ሁሉንም የስራ ክፍሎች፣ ቢሮዎችና ዘርፎችን ማሳተፍ ቀጣይነት ያለው ስኬት ለማረጋገጥ ብቸኛው መንገድ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት፡ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ እርምጃዎች

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ጥረቶች መጎልበትን የሚያስረዱ መረጃዎች እና ያሳደሩትን ተጽህኖ ጠቅለል ባለ መልኩ ለመገምገም የሚያስችሉ ዘዴዎች እጥረት አለ። በጤና ፕሮግራሞችና ትግበራዎች የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙቶችን መለካት በተመለከተ ከሚነሱ ግድድሮሾች በተጨማሪ በቂ የሆኑ በፆታና በእድሜ የተከፋፈሉ መረጃዎችን ማግኘት አሁንም አስቸጋሪ ነው። እነዚህ የመረጃ እጥረቶች ቢኖሩም ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖሮች ትኩረት ሊያገኙና ሊፈቱ ይችላሉ፣ ሊፈቱም ይገባል። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖር አንዱ አስፈላጊ የጤና ወሳኝ ሁኔታ እንደሆነ ለማሳየት ያሉ ማስረጃዎች በቂ ናቸው። ይህን እንጂ፣ የጤና መረጃዎችና ዘዴዎች እስኪጠናከሩ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆች ከጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙቶች በሚነሱ የጤና ችግሮች ሊሰቃዩ አይገባም።

የሥርዓተ-ፆታ ሰፋፊ ከሚባሉ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች አንዱ ነው። የሥርዓተ-ፆታ ከሌሎች ወሳኝ ጉዳዮች ጋር በመቀናጀት በወንዶችና በሴቶች የጤና ውጤቶች ላይ ልዩነት ያመጣሉ። ወንድ ወይም ሴት መሆን በጤና ባህሪ ላይ፣ በጤና ሁኔታ ላይ፣ በጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ተጽህኖ ያሳድራል። ከሃይል አንጻር፣ ከኑሮ ሁኔታ አንጻር፣ ከስነ-ህይወታዊ አወቃቀር፣ ከማህበራዊ መስተጋብር እና በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚኖራቸው ሚና አንጻር ወንዶችና ሴቶች ይለያያሉ። እነዚህ ልዩነቶች መኖራቸውን መቀበል፣ መተንተንና ስልታዊ በሆነ መልኩ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።

የአለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ መመዘኛ ስኬል፣ በሌሎች ማዕቀፎች ላይ በመመርኮዝ አምስት እርከኖችን ይዟል። ከአምስቱ ሁለቱ፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትንና የጤና እኩልነትን ለማረጋገጥ እንቅፋት ናቸው። ሶስተኛው እርከን - ይኸውም ሥርዓተ-ፆታን ማገናዘብ የሚለው እርከን ለውጥ የታየበት እርከን ነው። ይህ እርከን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙቶች በጤና ላይ ለሚያሳድሩት ወሳኝ ተጽህኖ እውቅና የሰጡበት እርከን ነው (አባሪ ሰነድ 3 ይመልከቱ)። አንድ ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ሊሆን የሚችለው (እርከን 4) ወይም በሥርዓተ-ፆታ ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው (እርከን 5) ሥርዓተ-ፆታን የሚያገናዝብ ሲሆን ብቻ ነው።



የሥርዓተ-ፆታ ግምገማ ዘዴ የአንድ ፕሮግራም በከፍተኛ ደረጃ የሚሰሩ ተግቦሮች የሥርዓተ-ፆታን ምላሽ ሰጭነት ሁኔታ (ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ሥርዓተ-ፆታ ተኮር ወይም የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ የሚያመጣ) በፍጥነት ለመገምገም ይረዳል። የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭነት ዬት ዬት ጋር መሻሻል እንዳለበት ይጠቁማል።

***የፖሊሲ አቀራረብ ለሴቶች ጤና:*** የሥርዓተ-ፆታ ግምገማ ዘዴ ውስጥ በሁለት አሰራር ሊቃኝ ይችላል።

1. *የሴቶች የጤና ፍላጎቶች:* ይህ ዘዴ በሴቶች እና በልጃገረዶች የተለዩ የጤና ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ለማድረግ በበሽታ ስርጭት ልዩነቶች ላይ ያተኩራል። ፆታዊና ሥነ-ተዋልዶ የጤና ጉዳዮችን ያጠቃልላል። ይሁን እንጂ ሁሉን አቀፍ የህይወት ጉዳዮችን መረዳት ላይ ይሰራል። ስትራቴጂያዊ የሥርዓተ-ፆታ እና የጤና ፍላጎቶች ከሴቶች ጤና ፍላጎቶች አሰራር ጋር የተቆራኘ ነው። ይህ አሰራር ብዙ ሴቶች-ተኮር እንቅስቃሴዎችን እያራመደ ከጤና ምርጫዎችና እድሎች አኳያ የሴቶች ሰብአዊ መብቶች ላይ ያተኩራል። እንደዚህ አይነቶቹ ስትራቴጂካዊ አሰራሮች ሴቶች ሰብአዊ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ አስችሏቸዋል። ይህ አሰራር በሴቶች ተጨባጭ የሥርዓተ-ፆታ እና የጤና ፍላጎቶች ላይ በማተኮር በሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች አውድ በሴቶች ጤና ላይ ይሰራል። ነገር ግን በቀጥታ የእኩልነት አለመኖር ላይ አይሰራም።

   ስለዚህ የሴቶች የጤና ፍላጎቶች አሰራርን መከተል በዋናነት *ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር* ስትራቴጂን መጠቀም ማለት ነው። ምክንያቱም አሰራሩ ሃብትን የማግኘትና የመቆጣጠር ልዩነቶች መኖራቸውን በመቀበል የተለዩ የሴቶች የጤና ፍላጎቶች ላይ አነጣጥሮ ይሰራል።

2. *የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን መሰረት ያደረገ አሰራር:-* ይህ አሰራር የትንተና አድማሱን ሰፋ ያደረገ ነው። ከበሽታ ስርጭት ጥናት ወደ ጎጂና በእኩልነት ላይ ያልተመሰረቱ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች በሴቶች ጤና ላይ የሚያሳድሩት ተጽህኖን አድማሱን በማስፋት ይተነትናል። እነዚህ ጉዳዮች በሴቶች ጤና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽህኖ ለመረዳት እና ለምን በሽታዎች፣ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች የወንዶችንና የሴቶችን ጤና በተለያየ መልኩ እንደሚጎዱ ለመረዳት ይጥራል። በመሆኑም የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን መሰረት ያደረገ አሰራር የጤናን ወሳኝ ጉዳዮች ያጠናል። እንደዚሁም የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች በወንዶችና በወንዶች ልጆች ጤና ላይ የሚያሳድሩት ተፅህኖ እንዲተነተን ያስችላል።

   የሴቶችን የጤና ችግሮች ለመፍታት የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን መሰረት ያደረገ አሰራርን መከተል ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ ስትራቴጂ ነው። በአንዱ ወይም በሌላኛው ፆታ ላይ ቢያተኩርም ማለት ነው። ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ ነው የተባለው የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ስለሚያረጋግጥ ነው። ይህ አሰራር በዘርፉ በዋናነት

የሚሰራበት ሲሆን ሥርዓተ-ፆታን ለማካተት የሚደረገውን ሰፋ ያለ አለማቀፍ እንቅስቃሴን የሚከተል ነው።

የሥርዓተ-ፆታ መመዘኛ መጠይቅ አንድን የጤና ፕሮግራም በጥልቀት የሚተነትን ዘዴ አይደለም። በጥልቀት ለመተንተን እያንዳንዱ ጥያቄ ጠለቅ ያለና ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚዳስስ መሆን አለበት። ለምሳሌ፦ በፆታ ተከፋፍሎ የተደራጀ መረጃ እምብዛም ስለሌለ "ከፕሮግራሜ የተሰበሰበው መረጃ ወይም ለፕሮግራሜ ግብአት የሆነው መረጃ በፆታ በተከፋፈለ መልኩ የተሰበሰበና ሪፖርት የተደረገ ነው?" ለሚለው ጥያቄ ብዙ ሰው "አይደለም" የሚል ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። ነገር ግን "በፆታ በተከፋፈለ መልኩ የተደራጀ መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለመተንተንና ሪፖርት ለማቅረብ በፕሮግራምህ ምን እየተደረገ ነው?" በማለት ተከታይ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል።

ጠቅለል ተደርጎ የቀረበው የአለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ መመዘኛ መጠይቅ "አዎን" እና "አይደለም" በማለት የሚመለሱ 23 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። በተራ-ቁጥር 1-18 ለሚገኙ ለአብዛኛው ጥያቄዎች "አዎን" የሚል ምላሽ ከተሰጠ የጤና ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ፣ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ የሚያመጣ ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። በተቃራኒው በተራ-ቁጥር 19-23 ውስጥ ለሚገኙ አብዛኛው ጥያቄዎች "አይደለም" የሚል ምላሽ ከተሰጠ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የሌለው ነው በማለት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭ አይደለም ተብሎ ሊታሰብ ይችላል።



ሥዕ1ሥ-ፆታ፡ የጤና አቅድና አና የጤና ፕሮግራም ቀረፃ ቺክ ሊስት (ዓለም ጤና ድርጅት የተወሰደ)

ፕሮግራምን ወይም ፖሊሲን በመቅረጽ ሂደት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች በተለያዩ እርከኖች ትኩረት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በአባሪ ሰነድ 6 ውስጥ የተካተተው ቼክ ሊስት፣ ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ በማተኮር የሥርዓተ-ፆታ በጤና እቅድና በጤና ፕሮግራሞች ተግባሮች ውስጥ እንዲቀራኝ ያግዛል (በሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴ መሰረት) ፡፡

## ክትትልና ምዘና

በፆታ የተከፋፈለ መረጃና ሥርዓተ-ፆታን ከግምት የሚያስገቡ ጠቋሚዎች ለጤና እቅድና ፕሮግራም ዝግጅት መሠረታዊ መስፈርቶች ናቸው፡፡ የጤና እቅድና ፖሊሲዎች የሥርዓተ-ፆታን ልማዳዊ ደንቦችን፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን መዳሰሳቸውን ለማረጋገጥ በዝግጅቱ ሂደት ውስጥ የምንጠቀማቸው መረጃዎች ቢያንስ በፆታ የተከፋፈሉ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የጤና መረጃዎች መሆን አለባቸው፡፡ የሚመረጡ ጠቋሚ መረጃዎች ምን አይነት እንደሆኑ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ቁልፍ የሥርዓተ-ፆታና የጤና ጉዳዮች በበቂ ደረጃ ለሁኔታዎች ትንተና፣ ለመረጃ አሰባሰብ ወይም ለክትትልና ምዘና ተግባሮች መዳሰሳቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

የጤና መረጃ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የጠቋሚ መረጃዎች አመራረጥ የጤና ጉዳዮችን ከግምት የሚያስገባና በፆታ የተከፋፈለ መረጃ መሆን አለበት፡፡ ሰፋ ያሉ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች መረጃ በጤናው ዘርፍ የጤና ትንተናን ለማካሄድ በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከሌሎች ዘርፎች የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መረጃዎችን ወይም ሌሎች መረጃዎችን መውሰድ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ከታች የተሰጡት ሁለት ምሳሌዎች በፆታ የተከፋፈለ መረጃ ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖርን ለመለየትና ለመከታተል እንዴት እንደሚያግዙ ያሳያሉ፡፡

**የጤና አገልግሎት ተደራሽነት በፆታ የተከፋፈለ መረጃ ከማግኘት በላይ ነው**

***ጠቋሚ መረጃ*** - በጤና መድን የታቀፉ የሰዎች ብዛት ወይም የቤተሰብ ብዙት (%) በፆታና በሕዝብ ቡድኖች የተከፋፈለ መረጃ፤ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ፡፡

የጤና መድን ሽፋን ለጤና አገልግሎት ተደራሽነት እንደ መለኪያ መሳሪያ ያገለግላል፡፡ ምክንያቱም ከፍሎ መገልገልንም ሆነ በድንገት ከሚያጋጥሙ ከፍተኛ የጤና ወጭዎች ለመከላከል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ይሁን እንጂ ብዙ አውዶች ውስጥ ህብረተሰቡ የጤና መድን ሽፋን ተደራሽነት የለውም፡፡ ይህም በተለያዩ ማህበረተሰብ ውስጥ በሚገኙ ወንዶችና ሴቶች መካከል በተለያየ መለኩ ይገለጣል፡፡

በፆታ የተከፋፈለ መረጃ ሲሆን ዬትኞቹ የሴቶችና የወንዶች ቡድኖች የጤና መድን ሽፋን እንዳላገኙ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረታዊ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የሆኑ ሴቶች ወይም ወንዶች ከሌሎች ይልቅ ለምን ተጋላጭ ሆኑ የሚል ወሳኝ ጥያቄን ለመጠየቅ ያስችላል፡፡

ለምሳሌ የጤና መድን ሽፋን ሰዎች ከሚሰሩት የስራ አይነት ጋር የተቆራኘ ከሆነ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እኩልነት አለመኖር እንዲባባስ ያደርጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ሴቶች ከቀጣሪ መስሪያ ቤት የሚገኝ የጤና መድን ሽፋን ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ ምክንያቱም ስራቸው ብዙ ጊዜ ኢመደበኛ ስራዎች ስለሆኑ ነው (ለምሳሌ የቤት ውስጥ ልጅ የማሳደግ ስራ፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ እና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የግብርና ስራ ናቸው)፡፡ በተጨማሪም የቤት ኃላፊነቶችን ለመወጣት ሲባል በተለያዩ የስራ ሰዓቶች መስራታቸው የሰራተኛ ጥቅማጥቅሞችን ሊያስቀርባቸው ይችላል፡፡ ወይም ሴቶች ሙሉ በሙሉ ከስራ ገበታ የተገለሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በደንብ የተከፋፈለ መረጃ ካልሆነ ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙና የጤና መድን ሽፋንን በተመለከተ ተጋላጭነትን የሚጨምር እንዲህ ያለ መረጃ ሊገኝ አይችልም (የመድን ሽፋኑ በመንግስት የሚሰጥ ሆነም አልሆነም)፡፡

## የጤና አገልግሎቶች ሽፋን፡ በፆታ የተከፋፈለ መረጃን በደንብ መጠቀም

***ጠቋሚ መረጃ*** የጤና ችግር ወይም አደጋ ካጋጠማቸው ሰዎች የጤና አገልግሎት ያገኙ የወንዶችና የሴቶች ብዛት በመቶኛ

የጤና አገልግሎት አቅርቦት በዩትኛውም የጤና አሰራር ውስጥ ወሳኝ አካል ነው። የጤና አገልግሎ አቅርቦት ከሚመለከታቸው ጉዳዮች መካከል የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና አጠቃቀም ይገኙበታል። በተለይ የጤና አገልግሎት ሲያስፈልጋቸው አገልግሎቱን የሚያገኙ የሰዎች ቁጥርን የሚመለከት የጤና አገልግሎት ሽፋን በከፍተኛ ሁኔታ በጤና አገልግሎ አቅርቦት ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው።

የጤና አገልግሎቶችን ማግኘት የመፈለግና የመጠቀም ውሳኔ በብዙ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። እነዚህም በተጠቃሚዎቹ እይታ የጤና እክሉ ወይም የአደጋው ክብደት (የበሽታ ስሜቶችን መለየት ጨምሮ)፣ የቤተሰቡ የሃብት ሁኔታ፣ የጤና አገልግሎቶቹ መኖር፣ የመክፈል አቅም ያገናዘበ መሆን፣ ሁሉን አቀፍና ተቀባይ መሆን ናቸው። *የሥርዓተ-ፆታ* አመለካከት ድምዳሜዎች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ በብዙ መንገድ ተጽህኖ ያሳድራሉ። በድህነት የሚኖሩ ሴቶች ለቤተሰቡ ገቢ አስተዋጽዎ የማያደርጉ ከሆነ ለጤናቸው የሚሰጠው ዋጋ ዝቅ ያለ ይሆናል። ይህ በምጣኔ ሃብት ላይ በመመስረት ለቤተሰቡ ገቢ ለሚያስገኙ ሰዎች ቅድሚያ መስጠት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሌሎች *ሥርዓተ-ፆታ* የጤና አገልግሎት የማግኘት ፍላጎት ባህሪንና የጤና አጠቃቀምን ሊወስን የሚችልባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

- የሴቶች አካላዊ እንቅስቃሴ መወሰን፡ ከቤት ውጭ ለሴቶች የደንገጡር ጥበቃ ይባላል።
- የሴቶች የመወሰን ስልጣን መገደብ ወይም የፈለጉትን ለማድረግ ፈቃድ የመጠየቅ አስፈላጊነት፣ እና
- የወንዶችና የሴቶች የየእለት ስራዎች (በክፍያም ሆነ ያለክፍያ የሚሰሩ) የጤና አገልግሎት የማግኘት አቅማቸውን የሚወስኑ ሊሆኑ። ለምሳሌ ሴቶች የቤተሰብ አባላትን ጤና እና ደህና መሆንን መንከባከብ ሲኖርባቸው የራሳቸውን ጤና ቸል ማለት

ይህ ጠቋሚ መረጃ እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች አይዳሰሱም። ነገር ግን በፆታ የተከፋፈለ መረጃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ቢያንስ የተለያዩ የጤና አገልግሎት አጠቃቀም ዘይቤዎችን ለመለየትና ልዩነቶች ለምን እንደኖሩ፣ ፍትሃዊ መሆን አለመሆናቸውን፣ ማስወገድ መቻል አለመቻሉን በበለጠ ጥልቀት ለመመርመር ያስችላል። እነዚህም ልዩነቶችና የጤና ፍላጎቶች አሁን ባሉት የጤና አገልግሎቶችና የጤና አገልግሎት ማግኘት የመፈለግ ባህሪያት ሊፈቱ መቻል አለመቻላቸውንም ለማጥናት ያስችላል።

የጤና አገልግሎት ሽፋን ጠቋሚ መረጃዎች በተመለከተ ልብ ሊባሉ የሚገቡ ነጥቦች፡

ሁሉም ባይሆኑ አብዛኛው የጤና አገልግሎት ሽፋን ጠቋሚ መረጃዎች በፆታ መከፋፈል ይችላሉ። በቀዶ ጥገና መውለድ ወይም ሌሎች የጤና አገልግሎት ሽፋን ጠቋሚ መረጃዎች በአንድ ፆታ ብቻ ላይ ያተኮሩ ናቸው። እንዲህ አይነቶቹ ጉዳዮች መረጃን በፆታ ማከፋፈሉን አላስፈላጊ ያደርጋሉ። ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን በፆታው ውስጥ ለመለየት እንደዚህ አይነቶቹ ጠቋሚ መረጃዎች በሌሎች መስፈርቶች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ እርጉዝ ሴቶች በሽታውን ከእናት ወደ ልጅ እንዳያስተላልፉ የፀረ-ኤች አ ቪ መድኃኒት መውሰድ አለመውሰዳቸው ላይ የተመሰረተ የመረጃ አደረጃጀት ሊሆን ይችላል። ሌሎች ክፍፍሎች ደግሞ እድሜ፣ የመኖሪያ አካባቢ (ከተማ ወይ ገጠር) እና የትምህርት ደረጃ ሊሆኑ ይችላሉ።

## *የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ጠቋሚ መረጃዎች*

የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ሲባል ሂደትን (ተቋማዊ አካታችነት) እና ውጤትን (የፕሮግራም አካታችነት) የሚመለከት መሆኑን ልብ በል፡፡ ይህ ማለት በሁለቱም ውስጥ የታዩ ልዩነቶችና እምርታዎችን ለመለየት ጠቋሚ መረጃዎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ የሂደት ጠቋሚ መረጃዎች ተራማጅ ተቋማዊ ለውጦችን ለመከታተል አስፈላጊ ናቸው፡፡

የጤና ሚኒስቴር አራቱን የሥርዓተ-ፆታ ማካተት መከታተያ የስትራቴጂ አቅጣጫዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

***የስትራቴጂ አቅጣጫ 1***፡ የጤና ሚኒስቴርን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና እና የእቅድ አዘገጃጀት አቅምን መገንባት

1. የሥርዓተ-ፆታ እና የጤና መሰረታዊ መረዳት ያላቸው የሁሉ የጤና ሚኒስቴር ሰራተኞች ቁጥር በመቶኛ (በፆታ፣ በዘርፍ፣ በደረጃና በክልሎች) ፡፡
2. የሥርዓተ-ፆታ ትንተናንና ተግባራትን በስራዎቻቸው ውሰጥ በመጠኑም ቢሆን የሚተገብሩ የሁሉ የጤና ሚኒስቴር ሰራተኞች ቁጥር በመቶኛ (በፆታ፣ በዘርፍ፣ በደረጃና በክልሎች) ፡፡
3. በመጠኑም ቢሆን የሥርዓተ-ፆታን በስራዎቻቸው ውስጥ የማቀናጀት ተቋማዊ ድጋፍ ሪፖርት የሚያቀርቡ የጤና ሚኒስቴር ሰራተኞች ቁጥር በመቶኛ (በፆታ፣ በዘርፍ፣ በደረጃና በክልሎች) ፡፡

***የስትራቴጂ አቅጣጫ 2*** ፡ የሥርዓተ-ፆታን በጤና ሚኒስቴር አመራር ውስጥ ማካተት

1. ምላሾቻቸው የሥርዓተ-ፆታ ቅንጅት የትግበራ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ጠንካራ መሆኑን የሚያንጸባርቁ የእቅድ ዝግጅት ትኩረት ቦታዎች በመቶኛ (በፆታ፣ በዘርፍ፣ በደረጃና በክልሎች የተከፋፈለና ከሥርዓተ-ፆታ፣ ከሴቶችና ከጤና ኔትወርክ ጋር ትብብር መኖሩን እና አለመኖሩን የሚያሳይ) ፡፡
2. የሥርዓተ-ፆታን በተጠናከረ መልኩ በጤና ፕሮግራሞቻቸው ውሰጥ ለማቀናጀት ሲባል የተከለሰውን የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻን የተገበሩ የጤና ፕሮግራሞች፣ ኤጀንሲዎች እና ቢሮዎች ቁጥር
3. የሁሉም ሙያዎችና የአስተዳደር የስራ ምድቦች በፆታና በትምህርት ደረጃ በመቶኛ

***የስትራቴጂ አቅጣጫ 3*** በፆታ የተከፋፈለ መረጃንና የሥርዓተ-ፆታ ትንተናን መጠቀምን ማስፋፋት

1. በቅርቡ ታትመው ከወጡ ከተወሰዱ ናሙናዎች በፆታ የተከፋፈለ መረጃን የሚያስፋፉ እና/ወይም የሚጠቀሙ የጤና ሚኒስቴር ህትመቶች ቁጥር

***የስትራቴጂ አቅጣጫ 4*** ፡ ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ

1. በጤና ሚኒስቴሩና በክልል የጤና ቢሮ ኃላፊዎች ከተደረጉት ንግግሮች ከተወሰዱ ናሙናዎች ሥርዓተ-ፆታን የነኩ የንግግሮች ቁጥር

ስለዚህ፣ በአጠቃላይ የጤናው ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት አሰራሮች ክትትልና ምዘና ከታች የተቀመጡ ነጥቦችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡

- ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ በዝርዝር (qualitative) እና በአሃዛዊ (quantitative) ጠቋሚ መረጃዎች ሊለዩ ይገባል፡፡
- በፆታ የተከፋፈለ መረጃን መጠቀምና መተንተኑን ማረጋገጥ
- የሥርዓተ-ፆታ-ነክ የሆኑ ዓላማዎችን ማሳካት፣ ፕሮጀክቱ በወንዶችና በሴቶች ላይ ያሳደረውን የተለያዩ ተጽህኖዎችና ውጤቶችን ማጤን፣ እና በሁለቱ መካከል ባለው የኃይል ግንኙነት ላይ ያሳደረው ተጽህኖ ሊታወቅ ይገባል፡፡
- በተለያዩ ዘርፎች የሚሰሩ ሰራተኞች የሥርዓተ-ፆታ ሚዛን ሊጠበቅ ይገባል፡፡

## አባሪ ሰነዶች

### አባሪ ሰነድ 1፡ የአለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎች

የሚከቱለት የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎች (GAQ) የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መጠይቅ ቅጾችን (GAM) ለመሙላት ይረዳል። የህን ሰነድ ከGAM እና ከሥርዓተ-ፆታ እቅድ አዘገጃጀት እና ፕሮግራም ዝግጅት ቼክሊስት ጋር በመጠቀም በስራህ ዙሪያ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ትኩረት እንዲያገኙ አድርግ።

| የዓለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎች | ተጓዳኝ ጤና-ነክ GAM እሳቤዎች |
|---|---|
| **ትኩረት የሚያስፈልገው ህመም፣ በሽታ ወይም የጤና ሁኔታ ምንድነው?** | |
| አጣዳፊ ነው ወይስ የቆየ ህመም ነው?<br>• ተላላፊ በሽታ ነው ወይስ ተላላፊ ያልሆነ በሽታ ነው?<br>• ይሄን በሽታ በተመለከተ አስጊ ጉዳዮች ምን ምንድናቸው?<br>• ለሴቶችና ለወንዶች፣ ለልጃገረዶችና ለወንዶች ልጆች ይለያያል? | ስለህመሙ ለመግቢያ የሚሆኑ መረጃዎች (በGAM ውስጥ ያልተጠቃለሉ)<br>የስጋት ምክንያቶችና ተጋላጭነት |
| **ይህ ሁኔታ መቼ መቼ ነው የሚከሰተው?** | |
| በማንኛውም ጊዜ ነው የሚከሰተው?<br>በዚህ ወቅት በህመሙ የተጠቃውን ሰው/ቡድን ተጋላጭነት በስነ-ህይወት-ነክ ምክንያቶች የሚብራራ ሰበብ አለ? ምን ምንድናቸው?<br>በዚህ ወቅት በህመሙ የተጠቃውን ሰው/ቡድን ተጋላጭነት በማህበራዊና ባህላዊ-ነክ ምክንያቶች የሚብራራ ሰበብ አለ? ምን ምንድናቸው?<br>በዚህ ወቅት ዬትኞቹ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የተጋላጭነት መጨመርን ሊያብራሩ ይችላሉ? | ስለህመሙ ለመግቢያ የሚሆኑ መረጃዎች (በGAM ውስጥ ያልተጠቃለሉ)<br>የስጋት ምክንያቶችና ተጋላጭነት<br>የጤና እና ማህበራዊ ውጤቶችና መዘዞች |
| ተጋላጭነት በአመቱ ውስጥ በተለየ የጨመረበት ጊዜ አለ?<br>- ከአየር ሁኔታ ጋር በተያየዘ መልኩ ተለይቶ በሚታወቅ ጊዜ ወይም በዚያ ጊዜ አካባቢ ነው? እህል ሲደርስ ነው?<br>- ተጋላጭነታቸውን የሚጨምር በዚህ ወቅት ወንዶች ወይም ሴቶች የሚሰሩ የተለዩ ስራዎች አሉ? | |
| **የህ የጤና ሁኔታ ዬት ነው የሚከሰተው?** | |
| • በገጠር ወይስ በከተማ አውድ?<br>• ለሴቶች፣ ለወንዶች፣ ለልጃገረዶች ወይም ለወንዶች ልጆች የተለያየ ተጽህኖ አለው? | ስለህመሙ ለመግቢያ የሚሆኑ መረጃዎች (በGAM ውስጥ ያልተጠቃለሉ)<br>የስጋት ምክንያቶችና ተጋላጭነት |
| • ከማህበራዊና ከባህላዊ ሁኔታ ጋር የሚያያዝበት ለየት ያለ ምክንያት አለ?<br>• ችግሩ የሚከሰተው በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት፣ በሜዳ ወይም በቤት ውስጥ ነው?<br>• ወንዶች ወይም ሴቶች በሚያዘወትሩበት ወይም በሚበዙበት ስፍራ ነው የሚከሰተው?<br>• እነዚህ ወንዶችና ሴቶች ከተለየ ማህበራዊና ባህላዊ ቡድን የመጡ ናቸው (የምጣኔ ሃብት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ)? | |

| ማነው የሚታመመው? | |
|---|---|
| • ለምን ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆች በሁኔታው በተለያየ መልኩ እንደሚጎዱ የስነ-ህይወት ምክንያቶች ሊያብራሩ ይችላሉ?<br>- የግለሰቡ ዕድ ለዚህ ህመም የተጋላጭነት ስጋቱን ይጨምራል? እንዴት?<br>- እድሜ ወይም ሌሎች እንደ የሆርሞን መጠን የመሳሰሉ አካላዊ ምክንያቶች ልዩነት ያመጣሉ? እንዴት? | የስጋት ምክንያቶችና ተጋላጭነት<br>የጤና እና ማህበራዊ ውጤቶችና መዘዞች |
| • ምን ምን የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች ለዚህ በሽታ የማህበረተሰቡን ስጋት ወይም ተጋላጭነት ይጨምራሉ?<br>• እነዚህ የአመለካከት ድምዳሜዎች ወንዶችና ሴቶች ላይ ተመሳሳይ ወይስ የተለያዩ ተጽህኖዎችን ያሳድራሉ?<br>• የተጎዳው ቡድን የተለየ የማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ፣ ብሄር ወይም የተገለለ ቡድን አካል ነው?<br>• የሴቶችና የወንዶች የየእለት ተግባሮች ለበሽታው ስጋት ተጋላጭነታቸው ላይ ለውጥ ያመጣሉ? ከሆነስ፣ ዩትኛቹ ስራዎች (በክፍያም ሆነ ያለ ክፍያ የሚሰሩ) ስጋትን ይጨምራሉ? እነዚህን ስራዎች የመስራት ኃላፊነት ያለበትማነው?<br>• የሃብቶች ተደራሽነትና የመቆጣጠር መብት በበሽታው ስጋት እና ተጋላጭነት ላይ ተጽህኖ አላቸው?<br>• የግለሰብ ወይም የማህበረተሰብ የብቃት ደረጃ በበሽታው ስጋት እና ተጋላጭነት ላይ ተጽህኖ አላቸው?<br>• በሽታው ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ለልጃገረዶችና ለወንዶች ልጆች የተለያየ ነው?<br>- የትምህርት እድሎች በበሽታው ስጋት እና ተጋላጭነት ላይ ተጽህኖ አላቸው?<br>• በሽታው በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ለሚገኙ ወንዶች ልጆችና ልጃገረዶች የተለያየ ነው? እንዴት?<br>• በደመወዝ የመቀጠር እድሎች በበሽታው ስጋት እና ተጋላጭነት ላይ ተጽህኖ አላቸው?<br>• በሽታው በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ለሚገኙ ወንዶችና ሴቶች የተለያየ ነው? እንዴት?<br>• የሴቶች የቤት ውስጥ፣ የማህበረተሰብ እና የስራ ቦታ ኃላፊነቶች በበሽታው ስጋት እና ተጋላጭነት ላይ ተጽህኖ አላቸው? | |
| **በጤናው ችግር የተጠቁ ሰዎች ስለጉደዩ ምን እያደረጉ ነው?** | |
| • ወንዶቹም ሴቶቹም ለበሽታው አግባብ ያለው ህክምና ይፈልጋሉ?<br>• ማናቸው ናቸው የህክምና አገልግሎትን እየተከታተሉ ያሉት? ሴቶች? ወንዶች? የተወሰነ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ቡድኖች? የተወሰነ ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ቡድን?<br>• ባህላዊ ሃኪሞችን የሚያማክሩ ወይም አማራጭ የህክምና ዘዴ የሚፈልጉ ማናቸው ናቸው? ሴቶች? ወንዶች? የተወሰነ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ቡድኖች? የተወሰነ ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ቡድን?<br>• ለምን እነዚህ ቡድኖች የሚያደርጉትን ያደርጋሉ? | የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀም<br>የጤና አገልግሎት ማግኘት የመፈለግ ባህሪ |
| • የስነ-ህይወት ምክንያቶች ከዚህ በሽታ ጋር በተገናኘ መልኩ የጤና አገልግሎት የመፈለግ ባህሪ ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ? እንዴት? ምክንያቶቹ ለሴቶችና ለወንዶች የተለያዩ ናቸው? እንዴት? | |
| • የማህበራዊና ባህላዊ ምክንያቶች ከዚህ በሽታ ጋር በተገናኘ መልኩ የጤና አገልግሎት የመፈለግ ባህሪ ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ? እንዴት? ምክንያቶቹ ለሴቶችና ለወንዶች የተለያዩ ናቸው? እንዴት? | |
| • የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሴቶች ወይም የወንዶች መታመማቸውን የመቀበልና እና/ወይም ህክምና የመፈለጋቸው ፈቃደኝነት ወይም አቅም ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ? እንዴት? | |

| | |
|---|---|
| • የሴቶችና የወንዶች ሃብት ማግኘት የመቻልና የመቆጣጠር እድል መታመማቸውን የመቀበልና እና/ወይም ህክምና የመፈለጋቸው ፈቃደኝነት ወይም አቅም ላይ በምን መልኩ ተጽህኖ ያሳድራሉ?<br>• ሴቶች የህክምና እርዳታ ለማግኘት በራሳቸው መወሰን ይችላሉ? | |
| **ሃብት ማግኘት የመቻልና የመቆጣጠር እድል የጤና እንክብካቤ አሰጣጥ ላይ በምን መልኩ ተጽህኖ ማሳዳር ይችላል?** | |
| • የጤና አገልግሎቶች ተቋማት የተመሰረቱት ወይም አገልግሎቶቹ የሚሰጡት ማህበረተሰቡ ባለበት አካባቢ ነው? ወይስ ሁለቱም?<br>• የጤና አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ የሚያገለው ቡድን አለ? ዬትኛው? ለምን? | የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀም በጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚያጋጥሙ ልምምዶች |
| ሃብት ማግኘት የመቻልና የመቆጣጠር እድል ለዚህ ህመም የሚሰጠው አገልግሎት አይነት ላይ የሚያሳድረው ተጽህኖ አለ? እንዴት? | |
| ወንዶችና ሴቶች ለዚህ ህመም የሚሆን የጤና አገልግሎቶችን ለመፈለግና ለመጠቀም የሚያስችል ሃብት አላቸው?<br>- የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት እነዚህን ሃብቶች ማግኘት ይችላሉ? ማግኘቱ ለወንዶችና ለሴቶች የተለያየ ነው?<br>- የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት እነዚህን ሃብቶች ለመጠቀም ወሳኔ መወሰን ወይም በውሳኔ አሰጣጡ ላይ ተጽህኖ ማሳደር ይችላሉ? ውሳኔ አሰጣጡ ለወንዶችና ለሴቶች የተለያየ ነው?<br>- ሴቶችና ወንዶች ሃብት ማግኘት የመቻልና የመቆጣጠር እድላቸው የተለያየ ከሆነ ከጤና አገልግሎት ጋር በሚኖራቸው ልምምድ ላይ ምን አይነት ተጽህኖ ያሳድራል? እንዲህ አይነቱ ልዩነት በሚሰጠው የአገልግሎት ጥራት ላይ ተጽህኖ ያሳድራል?<br>- ሃብት ማግኘት የመቻልና የመቆጣጠር እድል የህክምና አማራጮች ላይ ተጽህኖ ያሳድራል? በምን መልኩ? ልዩነቱስ ለወንዶችና ለሴቶች ይለያያል? | |
| በህመሙ በተጠቁት ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘትና ለመጠቀም የሚያስችል አቅማቸው ላይ ተጽህኖ የሚያሳድሩ የተለዩ የፋይናነስና ማህበራዊ ተጋላጭነት አላቸው?<br>- ይህ ተጋላጭነት በእድሜ፣ በብሔር ወይም በሚከተሉት ሃይማኖት፣ በፆታ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ይባባሳል? | |
| በህመሙ የተጠቃው ማህበረሰብ አስፈላጊውን ሃብት የሌለው ከሆነ ምን አይነት የግንኙነት መረቦች ወይም ተቋማት ሊደግፏቸው ይችላሉ?<br>- እነዚህስ ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ ናቸው? | |
| ይህን ህመም ለማከም የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል አቅምን ያገናዘበ ነው?<br>- ለተለያዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድኖች ይለያያሉ? እንዴት? | |
| የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት ግለሰቡ የሚያወጣቸው እንደ መጓጓዣ የመሳሰሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች አሉ? ወይም የልጆች እንክብካቤ የመሳሰሉ በወንዶችና በሴቶች ላይ የተለያየ ተጽህኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች አሉ? | |
| የጤና መድን ሽፋን እቅዶች ውስጥ ለመካተት ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ መስፈርቶች አሏቸው?<br>-የጤና መድን እቅዶቹ ለዚህ ህመም የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን | |

| | |
|---|---|
| ይሸፍናሉ? በስራ ቅጥር ሁኔታ ላይ፣ በጋብቻ ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶች አሉ? ከሆነስ፣ ይህ በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽህኖ ምን ይመስላል?<br>-የጤና መድን እቅዶቹ ለመድኃኒት መግዣና እንደ ጡት ምርመራ ወይም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኤች አይ ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎቶችን ይሸፍናሉ? ከዚህ በሽታ ጋር የተያያዙና የጤና መድኑ የማይሸፍናቸው ወሳኝ አገልግሎቶች አሉ?<br>- የጤና መድን እቅዶች ከሌሉና የህክምና አገልግሎቶች በነጻ የማይሰጡ ከሆነ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሴቶችና ወንዶች እንዴት አድርገው የጤና አገልግሎቶቹን ማግኘት ይችላሉ?<br>• ምን የግል ወይም የማህበረሰብ ስልቶችን ይጠቀማሉ?<br>• እነዚህ በሽተኛው ወንድ ወይም ሴት ስለሆነ ይለያያል? እንዴት? | |
| የጤና አገልግሎትን ማግኘት ከመፈለግ እና እንክብካቤ ከማግኘት የተነሳ የሚታጡ እድሎች ምን ምንድናቸው (ለምሳሌ ገቢ የማግኘት እድል የሚያስመልጡ)?<br>- እነዚህ ለወንዶችና ለሴቶች ይለያያሉ? | |
| | |

| የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ጥያቄዎች | ተጓዳኝ ጤና-ነክ GAM እሳቤዎች |
|---|---|
| ***የጤና አገልግሎቶች በዚህ በሽታ የተጠቁትን ወንዶችና ሴቶች ፍላጎት እንዴት ያሟላሉ?*** | |
| የስነ-ህይወት ምክንያቶች የህክና አማራጮች ላይ፣ አቀባበልና ክትትል ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ?<br>- እነዚህ ከተለያዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድን (እድሜን ጭምር) ለመጡ ሰዎች ልዩነት አላቸው? እንዴት? | የህክምና አማራጮች በጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚያጋጥሙ ልምምዶች |
| የማህበራዊና ባህላዊ ምክንያቶች የህክና አማራጮች ላይ፣ አቀባበልና ክትትል ላይ ተጽህኖ ያሳድራሉ?<br>- እነዚህ ከተለያዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድን (እድሜን ጭምር) ለመጡ ሰዎች ልዩነት አላቸው? እንዴት? | |
| በዚህ በሽታ ህክምና አማራጮች ውስጥ የወንዶችና የሴቶች የተለያዩ ሚናዎች ከግምት ገብተዋል?<br>- የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች እና ግንኙነቶች ከግምት ገብተዋል? እንዴት?<br>- የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች፣ ልማዳዊ ደንቦች እና ግንኙነቶች ከግምት ውስጥ ሳይገቡ ይህን በሽታ ማከም መዘዙ ምን ሊሆን ይችላል? | |
| የጤና ሠራተኞች በአጠቃላይ በተለያዩ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች በዚህ በሽታ ሲሰቃዩ የሚሰማቸውን የህመም ስሜት የሚገልጹት በተለያየ መንገድ እንደሆነ ያውቃሉ? | |
| ይህን በሽታ (የጤና ሁኔታ) ሲታከሙ ወንዶችና ሴቶች በጤና አገልግሎቶቹ የተለያዩ ልምምድ አላቸው? ምን አይነት? ለምን ምክንያት?<br>- በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የሚያጋጥሟቸው ልምምዶች በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታ፣ በብሔር ወይም በሚከተሉት ሃይማኖት፣ በማህበራዊና ምጣኔ-ሃብታዊ ደረጃዎች ወይም በሌሎች ምክንያቶች ይለያያሉ? እንዴትና ለየትኛው ቡድን? | |
| ***የዚህ በሽታ (የጤና ሁኔታ) በዋናነት ጎልተው የሚታዩ የጤና እና ማህበራዊ ወጤቶች ምን ምንድናቸው?*** | |
| ከዚህ በሽታ (የጤና ሁኔታ) የተነሳ ከበሽታው በማገገም ላይ፣ አካል ጉዳት ወይም ስነ- | የጤና እና የማህበራዊ |

| | |
|---|---|
| ምግባር ላይ ልዩነት አለ (በወንዶች፣ በሴቶች፣ በልጃገረዶችና በወንዶች ልጆች መካከል)?<br>-እነዚህ ውጤቶች በያታና በእድሜ ተጽህኖ ስር ናቸው?<br>-ውጤቶቹ በሥርዓተ-ያታ ሚናዎች፣ ልማዳዊ ድምዳሜዎች እና ግንኙነቶች ተጽህኖ ስር ናቸው? ተጽህኖዎቹ ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ ናቸው?<br>-የእነዚህ ውጤቶች ሰፋ ያሉ ማህበራዊ ተጽህኖዎች ምን ምን ናቸው? | ውጤቶችና መዘዞች |
| በሽታው (ከታማሚው በተጨማሪ) በእነማን ላይ ተጽህኖ አሳድሯል? በልጆች? በወላጆች? በቤተሰቦች? በማህበረሰቦች? በምን በምን መንገዶች?<br>- በተጽህኖው የተጎዳው ሰው ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ተጽህኖዎቹ እንዴት ሊለያዩ ይችላሉ? | |
| በቤት ውስጥ የኃላፊነት ክፍፍል፣ የመቀጠር እድል፣ መድሎ ወይም ፍቺ የመሳሰሉ የበሽታው ማህበራዊ ባህሪዎች እና መዘዞች ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ ናቸው? | |
| ከመደበኛው የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ውጭ ለዚህ ህመምተኛ (እንክብካቤ ፈላጊ) እንክብካቤ የሚያደርጉት ሌሎች ሰዎች አነማን ናቸው?<br>- ይህ የእንክብካቤ ስራ የሚያሳጣው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?<br>- ለወንዶችና ለሴቶች ይለያያል? | |
| ወንዶችና ሴቶች የበሽታውን (የጤና ሁኔታውን) ተጽህኖ እንዴት እየተቋቋሙ?<br>- ያታ ወይም ሌሎች የስነ-ህይወት ምክንያቶች በሽታውን በመቋቋም ስልት ላይ በምን መልኩ ተጽህኖ ያሳድራሉ?<br>- የሥርዓተ-ያታ ሚናዎች፣ የአመለካከት ድምዳሜዎች እና ግንኙነቶች በሽታውን በመቋቋም ስልት ላይ በምን መልኩ ተጽህኖ ያሳድራሉ?<br>- ይህን በሽታ (የጤና ሁኔታ) በመቋቋም ረገድ ሃብት ማግኘትና መቆጣጠር መቻል ሌዩነት ያመጣል?<br>- ይህ ለሴቶችና ለወንዶች የተለያየ ነው? በምን መልኩ? | |

## አባሪ ሰነድ 2: የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥ

**የዓለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥ (GAM)**

| ***በጤና ውጤቶች ላይ ተጽህኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች፡ ጤና-ነክ እሳቤዎች*** | ***በጤና ውጤቶች ላይ ተጽህኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች፡ ሥርዓተ-ፆታ-ነክ እሳቤዎች*** | | |
|---|---|---|---|
| | ስነ-ህይወታዊ ምክንያቶች | ማህበራዊና ባህላዊ ምክንያቶች | ሃብትን ማግኘትና መቆጣጠር መቻል |
| የስጋት ምክንያቶችና ተጋላጭነት | | | |
| የጤና አገልግሎቶችን ማግኘትና መጠቀም | | | |
| ጤናን የመፈለግ ባህሪ | | | |
| የህክምና አባራጮች | | | |
| በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የገጠመ ልምምዶች | | | |
| የጤና እና የማህበራዊ ውጤቶች እና መዘዞቻቸው | | | |

## አባሪ ሰነድ 3፡ የዓለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭነት የምዘና ስኬል፡ የጤና ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች መመዘኛ መስፈርት

***ደረጃ 1፡ ሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የለም***

- ያልተመጣጠኑ ልማዳዊ ደንቦችን፣ ሚናዎችና ግንኙነቶችን በማጠናከር ***የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን ያስፋፋል***
- ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች ልዩ ጥቅም ይሰጣል (ወይም በተቃራኒው)
- በአብዛኛው አንደኛው ፆታ ከሌላኛው ይልቅ የበለጡ መብቶችን ወይም እድሎችን እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

***ደረጃ 2፡ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የለውም***

- ***የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን ችላ ይላል***
- በጣም ብዙ ጊዜ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ መድሎን ያጠናክራል
- በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የእድሎችና የሃብት ክፍፍል ልዩነቶችን ችላ ይላል
- በአብዛኛው **ሁሉንም እኩል ማስተናገድ** በሚል ፈሊጥ “ፍትሃዊ” መሆን የሚል መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

***ደረጃ 3፡ ሥርዓተ-ፆታን የሚያገናዝብ***

- ***የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን*** ከግምት ያስገባል
- እኩል ባልሆኑ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሚፈጠሩትን የእኩልነት ማጣት በመፍታት ላይ ትኩረት አያደርግም
- በአብዛኛው ***የመፍትሔ እርምጃዎች ባይዘጋጁም*** የሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤ እንዳለ ያመላክታል

***ደረጃ 3፡ ሥርዓተ-ፆታ ተኮር***

- ***የሥርዓተ-ፆታ፣ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን*** ለወንዶችና ለሴቶች ከግምት ያስገባል፡፡ እነዚህ እንዴት ሃብት በማግኘትና በመቆጣጠር ላይ ተፅህኖ እንደሚያሳድሩም ጭምር ከግምት ያስገባል፡፡
- የወንዶችንና የሴቶችን ለየት ያሉ ፍላጎቶችን ከግምት ያስገባል
- ***አንዳንድ የፖሊሲና የጤና ፕሮግራሞችን ግብ ወይም የተለዩ ፍላጎቶችን ለማሳካት ሲል*** ሆን ብሎ ***የተለዩ የሴቶች ወይም የወንዶችን ቡድን ለይቶ ትኩረት በማስጠት ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋል***፡፡
- በሥርዓተ-ፆታቸው ሚና ላይ በመመርኮዝ የተመደበባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለወንዶች ለሴቶች ሁኔታዎችን ያቀላል፡፡

***ደረጃ 5፡ ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ***

- ***የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን*** ለወንዶችና ለሴቶች ከግምት ያስገባል፡፡ እነዚህ እንዴት ሃብት በማግኘትና በመቆጣጠር ላይ ተፅህኖ እንደሚያሳድሩም ጭምር ከግምት ያስገባል፡፡
- የወንዶችንና የሴቶችን ለየት ያሉ ፍላጎቶችን ከግምት ያስገባል
- ***ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖር መንስኤዎችን ይፈታል***
- ***ጎጂ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦችን፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን ለመለወጥ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ያካትታል***
- ***ዓላማው በአብዛኛው የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፋፋት ነው***
- ***በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የሃይል ግንኙነት በተመለከተ ተራማጅ ለውጦችን*** ማምጣት የሚያስችሉ ስልቶች ማጎልበትን ያካትታል፡፡

## አባሪ ሰነድ 4፡ የሴቶችን መብቃት ለመመዘን የሚያገለግሉ የጠቋሚ መረጃዎች ምሳሌዎች

| የሚገመገሙ መለያ ባህሪያት | አዎን | አይደለም | በከፊል |
|---|---|---|---|
| **በግለሰብ ደረጃ** | | | |
| በቤተሰብ ደረጃ በውሳኔ ሰጭነት ውስጥ የመሳተፍ አቅም | | | |
| የጤና መረጃን የማግኘት እድል | | | |
| በማንኛውም ማህበር ውስጥ አባል መሆን/አለመሆን | | | |
| ሴቶችን ለማብቃት በሚዘጋጁ ወርክሾፖችና ሰብሰባዎች ላይ የመሳተፍ ወይም የመካፈል እድል | | | |
| ከቤተሰብ ውጭ በህብረተሰቡ ውስጥ መንቀሳቀስ መቻል/አለመቻል | | | |
| **በማህበረተሰብ ደረጃ** | | | |
| ማህበረተሰቡ የሴቶችን አመራር መቀበልና መደገፍ | | | |
| ሴቶች በአካባቢያቸው ማህበረተሰብ ውሰጥ ውሳኔ መስጠት መቻል | | | |
| የሴቶችን ጉዳዮች የሚያገናዝቡ የማህበረተሰብ መሪዎች መኖር | | | |
| **በብሔራዊ ደረጃ** | | | |
| የሴቶችን ጤና፣ መብቃትና ተሳትፎ የሚያፋጥኑ ህጎች እና ድንጋጌዎች መኖር | | | |
| ንቁ የሴቶች ንቅናቄዎችና ተቋማት መኖር | | | |
| የሥርዓተ-ፆታ ፖሊሲ መኖር | | | |

## አባሪ ሰነድ 5፡ የዓለም ጤና ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ ሚዘና መጠይቅ (GAT)

| ጥቃቄ | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. ራዕይ፣ ግብ ወይም መርሆዎች በግልጽ የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማስፋፋት ወይም ለማረጋገጥ የታለሙ ናቸው?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - የሚለው መልስ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |
| 2. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ ትኩረት የተሰጠውን ማህበረተሰብ ለመምረጥ ፆታን እንደ መስፈርት አካቷል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |
| 3. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ በፆታና በሥርዓተ-ፆታ መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ይረዳል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |
| 4. ትኩረት የተሰጠው ማህበረተሰብ ሆን ተብሎ ሴቶችንም ወንዶችንም ያካትታል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል<br>አይደለም - በተጨማሪም የጤና ፕሮግራሙ ሰፋ ካለው የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች አኳያ ከሁለቱ ፆታዎች አንዱ ላይ ያተኮረ ከሆነ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ሊሆን ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |
| 5. ወንዶችም ሴቶችም በሚከተሉት የሂደት ደረጃዎች ውስጥ ተሳትፈዋል?<br>• በፕሮግራሙ ቀረጻ (ዲዛይን)<br>• በትግበራ<br>• በክትትልና ምዘና<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ወይም የተለየው የፕሮግራሙ የሂደት ደረጃ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ማለት ፕሮግራሙ ወይም የተለየው የፕሮግራሙ የሂደት ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |
| 6. የወንዶችና የሴቶችን እኩል ተሳትፎ ለማረጋገጥ እርምጃዎች ተወስደዋል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ወይም ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል<br>አይደለም - በተጨማሪም የጤና ፕሮግራሙ ሰፋ ካለው የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች አኳያ ከሁለቱ ፆታዎች አንዱ ላይ ያተኮረ ከሆነ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ሊሆን ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል | | |

| | | |
|---|---|---|
| 7. ሁለቱም ወንድና ሴት የቡድን አባላት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እኩል ሚና አላቸው?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ወይም ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ያመላክታል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል** | | |
| 8. ፓሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የሴቶችንና የወንዶችን የኑሮ ሁኔታዎችንና እድሎችን ከግምት ያስገባል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመስጠቱን ሊያመላክት ይችላል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል** | | |
| 9. ፓሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የሴቶችን ተጨባጭና ስልታዊ ፍላጎቶችን ከግምት በማስገባት ያካትታቸዋል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ያመላክታል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ያመላክታል** | | |
| 10. የአሰራር ዘዴዎቹ በሁለቱም ፆታዎች ላይ ተሞክረዋል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን፣ ወይም ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር መሆኑን ያመላክታል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል** | | |
| 11. ፓሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ በቤተሰብ መካካል ያለውን መስተጋብር ከግምት ያስገባል? ማለትም ለቤተሰቡ አባላት በግል እንደ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ወይም የመወሰን መብት የመሳሰሉ የተለያዩ ውጤቶችና እድሎችን በቤተሰቡ ውስጥ ከግምት ያስገባል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል** | | |
| 12. ፓሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የተለያዩ የሥርዓተ-ፆታ ጥልቅ እውቀት ያላቸውን የባላድርሻ አካላትን ያካትታል? ማለትም ከመንግስት ጋር የሚሰሩ አካላትን፣ ሃገር-በቀልና አለማቀፋዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የማህበረሰብ ድርጅቶችን ያካትታል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ሊያመላክት ይችላል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል** | | |
| 13. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ ማስረጃዎችን በፆታ ከፋፍሎ በመሰብሰብ ሪፖርት ያደርጋል?<br>**የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡**<br>**አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል**<br>**አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል** | | |

| | | |
|---|---|---|
| 14. በፖሊሲው ወይም በጤና ፕሮግራሙ የተሰበሰቡ ማስረጃዎች እንደዚሁም ለፖሊሲው ወይም ለጤና ፕሮግራሙ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች በሥርዓተ-ፆታ ትንተና ላይ የተመሰረቱ ናቸው?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 15. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የሴቶችንና የወንዶችን የተለያዩ የጤና ፍላጎቶችን ከግምት ያስገባል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ አለመሰጠቱን፣የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ወይም ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር መሆኑን (አንድ ፆታ ብቻ ላይ ትኩረት ከተደረገ) ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 16. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የሴቶችንና የወንዶችን ተሳትፎ ለመከታተል የሚያስችል ኳልቴቲቭ እና ኳንትቴቲቭ ጠቋሚ መረጃዎቸን ያካተተ ነው?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 17. ፖሊሲው ወይም ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ የስራ ክፍፍልን (በክፍያ እና ያለክፍያ የሚሰራ፤ ምርታማ እና ስነ-ተዋልዷዊ ብሎ በማነጻጸር) ከግምት ያስገባል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 18. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ የሥርዓተ-ፆታ የተለምዶ ደንቦችን፣ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን ይዳስሳል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 19. ፖሊሲው ወይም ፕሮግራሙ (ሆን ብሎም ሆነ ሳያውቅ) አንዱን ፆታ እያገለለ ነገር ግን ድምዳሜው ለሁሉቱም ፆታ እንደሚውል አድርጎ ይገምታል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 20. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ በተለምዶ ሌላኛውን ፆታ የሚመለከቱ ናቸው ተብለው ከሚታሰቡት እንደ የእናቶች ጤና ወይም ሙያ-ነክ ጤና ጉዳዮች አንዱን ፆታ ያገላል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል | | |

| | | |
|---|---|---|
| 21. ፖሊሲው ወይም የጤና ፕሮግራሙ በግልፅ የሚታወቁ የተለያዩ የንዑስ ቡድኖች ውጤት የሚጠበቁ ሆነው ሳሉ ወንዶችንና ሴቶችን እንደ አንድ ተመሳሳይ ቡድን ይመለከታል? ለምሳሌ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ እና ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ሴቶችን እንደዚሁም የተቀጠሩና ያልተቀጠሩ ወንዶችን እንደ አንድ ተመሳሳይ ቡድን ይመለከታል?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 22. ቁሳቁሶችና የህትመት ውጤቶች ወንዶችንና ሴቶችን ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ባደረገ የተዛባ አመለካከት ያቀርባሉ?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል | | |
| 23. የቋንቋ አጠቃቀሙ አንዱን ፆታ የሚያገል ወይም ለአንዱ ፆታ የሚያደላ ነው?<br>የማርክ አሰጣጥ ፍንጮች፡<br>አይደለም - ማለት የጤና ፕሮግራሙ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ፣ ሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል<br>አዎን - ደግሞ ፕሮግራሙ ለሥርዓተ-ፆታ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ወይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖሩን ሊያመላክት ይችላል | | |

# አባሪ ሰነድ 6፡ የሥርዓተ-ፆታና የጤና እቅድና ፕሮግራም አዘገጃጀት ቼክሊስት

| **የሁኔታ ትንተና** |
|---|
| የሁኔታ ትንተና ሲካሄድ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል?<br>✓ ትኩረት ለሚሹ ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረጉ የጤና እኩልነት አለመኖር ላይ ለማተኮር የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መጠይቆችን (GAQ) እና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥን (GAM) ይጠቀሙ |
| ስለሥርዓተ-ፆታና ስለጤና የሚያወሱ ከጤና ጠቋሚ መረጃዎች እና/ወይም ሪፖርቶች ውጭ ከሆኑ ምንጮች የተገኙ አውቀቶችና መረጃዎች እንደ ማስረጃነት ሥራ ላይ ውለዋል?<br>✓ በፆታና በእድሜ የተከፋፈሉ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን እንደዚሁም ስለሞት፣ በሽታ፣ ስለአኗኗር፣ ስለአካል ጉዳት እና ስለጤና ወሳኝ ጉዳዮች የሚያወሱ መረጃዎችን ይጠቀሙ<br>✓ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ድምዳሜዎች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶችን በተመለከተ በወቅቱ የሚገኙ መረጃዎችን ለመረጃ ትንተና እንደግብአት ይጠቀሙ |
| ሃገሪቱ በሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና የሴቶች ጤና ላይ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፍ አላት?<br>✓ እንደ እነ ቤጂንግ ፕላትፎርም ፎር አክሽን፣ ብሔራዊ የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች እቅዶች፣ እንደ እነ ወሳኝ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተፈረሙበት/የፀደቁበትን ሰነዶች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች (ለምሳሌ CEDAW) ያሉትን አለማቀፋዊ ስምምነቶችና ግዴታዎችን ይከልሱ<br>✓ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ለሴቶች የጤና ጉዳዮች ትኩረት መስጠት አለመስጠታቸውን ለማረጋገጥ ብሔራዊ እና/ወይም የወረዳ የጤና ዘርፍ ፖሊሲዎችን ይገምግሙ<br>✓ በተነሳው ጉዳይ ላይ የፕሮግራሞችና የፖሊሲ መረጃዎችን ሰብስበው ያደራጁ - ከዚያም የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጭነት ግምገማ ዘዴን (GRAS3) በመጠቀም ይገምግሟቸው |
| ብሔራዊና የጤናው ዘርፍ ሂደቶች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና የሰብአዊ መብቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሠራሮችን ያካትታሉ? ለምሳሌ የሥርዓተ-ፆታ ዴስክ/ክፍል፣ የፕሮግራም ተጠሪ (የፎካል ፖይንት) አሰራር ወይም መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች ትስስር አለ?<br>✓ የፕሮግራም ውጤቶችን የሚያፋጥኑ አጋሮችን ለመለየት የሚያስችል በጤና ላይ የሚሰሩ የባለድርሻ አካላት ዝርዝር የያዘን ሰነድ ያዘጋጁ<br>✓ መንግስታዊ ያልሆኑ የሴቶች ድርጅቶችን ያካትቱ - ለምሳሌ lesbian, gay, bisexual and transgender organizations; የሰብአዊ መብቶች ቡድኖችን፣ የሴቶች ጉዳዮች የሚኒስቴር መስሪያቤቶችን፣ የማህበረሰብ መሪዎችን፣ የጤና ባለሙያዎችንና የመሳሰሉትን ያካትቱ |
| **የፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ቀረፃ፡ የስራ አድማሳቸውን፣ ራዕያቸውንና ትኩረት ያደረጉበትን ማህበረተሰብ ግልጽ ያድርጉ** |
| በስራ አድማሱና በራዕዩ ውስጥ በዚህ ዙሪያ ያሉ ወሳኝ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ተንፀባርቀዋል?<br>✓ የፆታና/ወይም የየሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶች በተነሳው የጤና ጉዳይ ላይ በምን መልኩ ተጽህኖ እንደሚያሳድሩ ያጥኑ<br>✓ ሥርዓተ-ፆታንና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን እንደ የጤና ወሳኝ ጉዳዮች ይዳስሱ<br>✓ የሥርዓተ-ፆታ ቁልፍ ጉዳዮችን ለይተው በስራ አድማሱና በራዕዩ ውስጥ ተንተን በማድረግ ያስገቡ<br>✓ በፕሮግራምና ፖሊሲ ቀረፃ ወቅት፣ እንደ ተጠቃሚዎችና እንደ ፕሮግራሙ ሰራተኞች ወንዶችንም ሴቶችንም እኩል ያሳትፉ |
| ትኩረት የተሰጠው ማህበረተሰብ ሆን ብሎ ወንዶችንም ሴቶችንም ያካትታል? ካልሆነስ ለምን?<br>✓ ትኩረት የሚደረግባቸው ማህበረተሰብ ሲመረጡ በሴቶች መካከልና በወንዶች መካከል ለሚኖሩት ብዝሃነት ትኩረት ይስጡ<br>✓ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ለየት ያለ ትኩረት የሚሹትን ቁልፍ የማህበረተሰብ ክፍሎችን ይለዩ<br>በተቀመጡት ዓላማዎችና ትኩረት በተደረገባቸው ማህበረተሰብ ላይ በመመስረት የሥርዓተ-ፆታ-ተኮር ወይም ሥርዓተ-ፆታን የሚለውጥ አሰራርን ይከተሉ |

## ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን መቅረጽ፡ ግቦችንና ዓላማዎችን ማስቀመጥ

ቢያንስ አንድ ግብ ወይም ዓላማ በግልጽ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ወይም የሥርዓተ-ፆታን እንደ ወሳኝ የጤና ጉዳይ ይዳስሳል?

- ✓ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መጠይቆች (GAQ) እና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥ (GAM) ላይ በመመስረት በግቦችና በዓላማዎች ውስጥ የሴቶችንና የወንዶችን የተለያዩ የጤና ፍላጎቶች ያነጸባርቁ
- ✓ ግቦችና ዓላማዎች ሲወሰኑ በሴቶች መካከልና በወንዶች መካከል ለሚኖሩት ብዝሃነት ትኩረት ይስጡ
- ✓ ግቦችንና ዓላማዎችን ሲያስቀምጡ ሌሎች የባለድርሻ አካላትንና አጋሮችን ያሳትፉ
- ✓ በጤናው ዘርፍ የሚታዩ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርን ለመዳሰስ ትክክለኛ ክህሎትና ችሎታ ያላቸውን አጋሮች ይምረጡ

እነዚህ አጋሮች በሁኔታ ትንተና ጊዜ ከተደራጀው የባለድርሻ አካላት ዝርዝር ውስጥ ሊመረጡ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ፡፡ በሁኔታ ትንተናው ወቅት ይህ ያልተደረገ ከሆነ ተገቢ የባለድርሻ አካላት መካተታቸውን ለማረጋገጥ በማንኛውም ጊዜ ሊደረግ ይችላል፡፡

- ✓ ግብ በማስቀመጥ ስራዎች ውስጥ ወንዶችንና ሴቶችን እኩል ማሳተፍን ያስታውሱ

## ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን መቅረጽ፡ የሚሰሩ ተግባሮችን ማዘጋጀት

የወንዶችና/ ወይም የሴቶች የኑሮ አውድና የተለያዩ የጤና ፍላጎቶቻቸው ከግምት ውስጥ ገብተዋል?

- ✓ ተግባሮቹ ትኩረት በተሰጣቸው ማህበረተሰብ ውስጥ በሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽህኖና እንድምታቸውን ከግምት ያስገቡ
- ✓ የተመረጡት ተግባሮች አስፈላጊነታቸው ወይም ተገቢነታቸው ሲወሰን ሴቶችን፣ ወንዶችን፣ ልጃገረዶችንና ወንዶች ልጆችን ያካትቱ
    - የምክክር ዘዴዎችን ሲወስኑ ከወንዶች፣ ከሴቶች፣ ከልጃገረዶችና ከወንዶች ልጆች የተለያዩ ግብአቶችን ለማግኘት አዳዲስ የፈጠራ አስተሳሰቦችን ይጠቀሙ
    - ፕሮግራሙ ከየአለት ተግባሮቻቸው ጋር አለመጋጨቱን ያረጋግጡ (ከተጋጨ ተሳትፎና ጥቅማጥቅም ማግኘት ላይ ተጽህኖ ያሳድራል)
    - የማህበራዊና ባህላዊ የተለምዶ ደንቦች የሴቶችና የወንዶች ተሳትፎ እና ጥቅማጥቅም ማግኘታቸው ላይ በምን መልኩ ገደብ እንደሚያደርጉ ከግምት ያስገቡ - ከዚያም ተገቢውን መፍትሔ ይስጡት

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖር ችግሮችን ለመፍታት ከአንድ ቡድን ለመጡ ወንዶችና ሴቶች ለየት ያሉ የአሰራር ተግባሮች ያስፈልጋሉ?

- ✓ የወንዶችን፣ የሴቶችን፣ የልጃገረዶችና የወንዶች ልጆችን ተመሳሳይና የተለያዩ ፍላጎቶችን ይለዩና በቡድኑ የተለዩ ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ ተግባሮችን ያዘጋጁ፡፡ የተለዩ ቡድኖቹ ከሌሎች የበለጠ የበሽታ ጫና ያለባቸው ወይም ጤናቸው የበለጠ ተጋላጭ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ ወንዶችና ሴቶች አንድ ወጥ (ተመሳሳይ) ቡድኖች አይደሉም፡፡ የአሰራር ተግባሮቹን ሲያዘጋጁ በእርስ በራሳቸው (በወንዶችና በወንዶች ወይም በሴቶችና በሴቶች) መካከል ሰፋ ያለ ብዝሃነት እንዳለ ከግምት ያስገቡ፡፡

የአሰራር ዘዴዎችና ተግባሮች ለጤና ጎጂ የሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦችን፣ ሚናዎችን እና ግንኙነቶችን ለመለየት ወይም ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ያካትታሉ?

- ✓ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ሰንጠረዥ (GAM)ን እና የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መጠይቆች (GAQ)ን በመጠቀም ጤናማ ውጤቶች እንዳይገኙ እንቅፋት የሚሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ልማዳዊ ደንቦችን፣ ሚናዎችን እና ግንኙነቶችን ለይተው መፍትሔ ይስጡ፡፡
- ✓ የአሰራር ተግባሮች በዘዴዎቻቸውና መሰረት በሚያደርጉት ግምቶቻቸው፣ ትኩረት በተደረገባቸው ማህበረተሰብ ውስጥ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን አለማጠናከራቸውን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

የአሰራር ተግባሮችን በተመለከተ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሌሎች የባለድርሻ አካላትና አጋሮች ተሳትፈዋል?

- ✓ እንደየሁኔታው አመችነት፣ ዘላቂ የመፍትሔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የግለሰብ ቡድኖችንም ሆኑ ሰፋ ያሉ ማህበረተሰቦችን ይዳስሱ
- ✓ በተዘጋጁ ተግባሮች አስፈላጊነትና አግባብነት ላይ የባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለው ግብአት ለማቅረብ እድል ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እንደ ተጠቃሚዎችም ሆነ እንደ የፕሮግራሙ ሰራተኞች ወንዶችና ሴቶች በተግባር ዝግጅቱ ላይ እኩል ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን መቅረጽ፡ በጀት ማዘጋጀት

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ስራን ወይም የሴቶች ጤና ስራዎችን ለማስፈጸም የሚረዱ በጀቶች ተመድድበዋል?

- ✓ የተለያዩ ተግባሮችን ለማስፈፀምና በጤናው ዘርፍ የሚታየውን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የአለመኖር ችግርን ለመፍታት የሚያስችሉ የተለዩ ፈንዶችን ይመድቡ
- ✓ ይህ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ያሉ ዓላማዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በግልጽ ለእያንዳንዱ የሥራ ተግባሮች ወጭውን ለይቶ በጀት መመደብን ይጠይቃል፡፡
- ✓ ሙሉ ጊዜያቸውን በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ እና በሴቶች ጤና ላይ የሚሰሩ ሰራተኞችን ይቅጠሩ ወይም ይመድቡ፡፡ የሥራ ተግባሮችን ለመተግበርና ለመከታተል ሰራተኞቹ በቂ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ወንዶችና ሴቶች ሠራተኞች እኩል ጥቅማጥቅም ያገኛሉ?

- ✓ እኩል ያልሆኑ ማበረታቻዎችና ጥቅማጥሞችን በመክፈል በተለያዩ የወንዶችና የሴቶች ቡድኖች መካከል (በእርስ በራሳቸው መካከል) ያሉትን መበላለጦች በማያጠናክሩ ወይም በማይደግፉ መልኩ የሥራ ተግባሮች መተግበራቸውን ያረጋግጡ፡፡

የታቀዱ ወጭዎችን በመለየት ሂደት ውስጥ ከማህበረተሰቡ እና ከአጋር ድርጅቶች የተውጣጡ ሴቶችና ወንዶች ተማክረዋል?

- ✓ በበጀት አመዳደብ ላይ የባለድርሻ አካላት ምክርና ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጡ፡፡ እዚህም ሀገር-በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንደዚሁም ሴቶችና ወንዶችን፣ ወንዶች ልጆችንና ልጃገረዶችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
- ✓ ይህ ለሰራተኛው የትርፍ ጊዜ ስራ፣ የትራንስፖርት ወጭ፣ የልጅ እንክብካቤ ወጭዎችን ለማካካስ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ ለሥርዓተ-ፆታ እና ለጤና ተግባሮች ሃብት ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ግልጽ የሆኑ ስልቶችን ይጠቀሙ

## ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን መቅረጽ፡ የሥራ ቡድን ስብጥር

የስራ ቡድኑ በሁሉም የውሳኔ አሰጣጥ እርከኖች ወንዶችንም ሴቶችንም ያካተተ ነው?

- ✓ የፆታ መመጣጠንን ግልጽ የምልመላ መስፈረት ያድርጉ
- ✓ እንደ ፕሮጀክት ሰራተኞች የወንዶችንና የሴቶችን እኩልና ትርጉም ያለው ተሳትፎን ያደፋፍሩ
- ✓ በፕሮጀክቱ ውስጥ የውሳኔ ሰጭ የስራ ምድቦች በወንዶችና በሴቶች መካከል ምዛኑን የጠበቀ ለማድረግ ይጣሩ
- ✓ በስራ ቡድኑ ስብጥር ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ የስራ ልምድን (ትንተና ወይም እኩልነት) ወይም በሴቶች ጤና ዙሪያ የስራ ልምድን እንደ ቁልፍ ብቃት ያካትቱ
- ✓ ከአማካሪዎች፣ ከፕሮጀክት ሠራተኞች፣ እና ከሌሎች የኮንትራት ፈራሚዎች ጋር በሚደረጉ የስራ ስምምነት የውል ማጣቀሻዎች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታና የጤና ልምድን ያካትቱ፡፡
- ✓ በጤናው ዘርፍ የሚታዩትን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እጦትን ለመፍታት የሚያስችሉ ክህሎቶችን፣ እውቀቶችንና ልምዶችን ከተለዩ ተግባሮችና ዓላማዎች ጋር ያጣምሩ፡፡
- ✓ ከፍ ባሉ የስራ ምድቦችና በትግበራ ሚናዎች ላይ የሚመደቡ ሰዎች የሥርዓተ-ፆታና የጤና ክህሎት ያላቸው መሆናቸውን ያረጋግጡ
- ✓ በፕሮጀክቱ አድማስ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ወይም የሥርዓተ-ፆታና የጤና ግንዛቤን በማሳደግ ረገድ በስራ ቡድኑ ውስጥ የሚታዩትን የአቅም ግንባታ ፍላጎቶችን ለይተው ምላሽ ይስጡት፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ስልጠና ይስጡ፡፡
- ✓ ስልጠናው ክህሎትን የሚያደብር እና ሰራተኛው በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ ያለውን እምነቶችና አመለካከቶችን የሚዳስስና ወደ ጋራ መረዳትና አሰራር የሚያመጣ መሆን አለበት፡፡

የሥራ ቡድኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትንና የሴቶች ጤና እንቅስቃሴን በተመለከተ ሪፖርት የሚያቀርቡበት እና ያላቸውን መረጃ የሚያካፍሉበት የተደራጀ አሰራር አላቸው?

- ✓ የሥርዓተ-ፆታ-ነክ የሆኑ የፕሮግራሙ ገጽታዎችን በተመለከተ ግልጽ የሆኑ የተጠያቂነት መስፈርቶችን ያስቀምጡ

የስራ ቡድኑ አባላት በክፍያ እርከን ወይም በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ይበላለጣሉ? እነማን ይበልጣሉ? ለምን?

- ✓ ተመሳሳይ ስራ ለሚሰሩ ወንዶችና ሴቶች እኩል የአከፋፈል ሥርዓትን ይዘርጉ
- ✓ ለሠራተኞች የሚሰጡ ማበረታቻዎች ለወንዶችና ለሴቶች እኩል መሆናቸውን ያረጋግጡ
- ✓ ከሰራተኞችና ከኮንትራት ፈራሚዎች ጋር የሚደረጉ የሥራ ስምምነቶችና ሁኔታዎች ከአወቃቀርና ከቤተሰብ ከሚመነጩ ገዳቢ ሆኔታዎች የተነሳ ለማሟላት ከአንዱ ፆታ ይልቅ ለሌላኛው ፆታ የሚከብድ አለመሆኑን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ የስራ ምደብ በገጠር ወይም ከፍተኛ የደህንነት ጥበቃ የሚያስፈለገው አካባቢ ከሆነ ስራው ለሁሉም እኩል ተደራሽ እንዲሆን እነዚህ የወንዶችም ሆኑ የሴቶች እንቅፋቶች መፍትሔ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡

## የትግበራ እንቅስቃሴዎች

የፕሮግራሙ ትግበራ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና የጤና ፍትሃዊነት መርሆዎችን የሚደግፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምን የተዘረጉ አሰራሮች አሉ?

- ✓ በፕሮግረሙ ውስጥና በመስክ ስራዎች ከሚሰሩ ሰራተኞች የሚጠበቁ የሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ የሥራ የስነ-ምግባር መስፈርቶችን ያዘጋጁ

የፕሮግራሙ ቁሳቁሶችና የህትመት ውጤቶች የሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ያጠናክራሉ?

- ✓ ለፕሮግራም ትግበራ የሚውሉ ዘዴዎችና ስለቶች፣ ተግባቦትን ጨምሮ፣ ስለተለየዩ የሴቶችና የወንዶች ቡድኖች የሚንጸባረቁ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የማያጠናክሩ ወይም የማይደግፉ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ የፕሮግራሙ የቋንቋ አጠቃቀም አንደኛውን ፆታ የሚያገልና ለሌላኛው ፆታ የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ አለመሆኑን ያረጋግጡ፡፡

የፕሮግራሙ የትግበራ ቦታዎች ወንዶችም ሴቶችም መድረስ የሚችሉባቸው ቦታዎች ናቸው?

- ✓ ወንዶችና ሴቶች አንዳንድ የፕሮግራሙ ትግበራ ቦታዎች ጋር ለመድረስ ሊያጋጥማቸው የሚችሉ ግድድሮሾችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ፡፡ ለሁሉም ተደራሽ የሆኑ ቦታዎችን ይምረጡ፡፡ ብዙ የፕሮግራም ትግበራ ቦታዎችን ማዘጋጀት ቢያስፈልግም ማለት ነው፡፡

ወንዶችና ሴቶች በትግበራው ደረጃ እኩል ተሳትፈዋል - እንደ ተጠቃሚዎችም ሆነ እንደ ፕሮግራሙ ሰራተኞች?

- ✓ ስለ ፕሮግራሙ፣ ስለ ወጤቶች እና ስላሳደረው ተጽህኖ ባለ ሁለት መስመር የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓትን ይዘርጉ፡፡ ከእናንተ ወደ ማህበረተሰቡ እና ከማህበረተሰቡ ወደ እናንተ ማለት ነው፡፡
  - ስለ ፕሮግራሙ፣ ስለ ሂደቱና ስለውጤቱ መረጃን ለማካፈል የሚያስችሉ ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ ስልቶችን ይዘርጉ
  - የማህበረተሰቡ አባላትን (ወንዶችንና ሴቶችን) እና ሌሎች የአካባቢ ባለድርሻ አካላትን/አጋሮችን መረጃን በመተንተንና ውጤቶችን በመተርጎም ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አግባብነቱ ያካትቱ፡፡
  - በሃገር ደረጃና በዓለማቀፍ ደረጃ ውሳኔ ከሚሰጡ አካላት ጋር፣ ከአካዳሚው ማህበረተሰብ ወይም የህትመት መገናኛ ብዙሃን ጋር የሚደረጉ ተግባቦቶችን አይወስኑ፡፡
  - በፖሊሲው ወይም በፕሮግራሙ የትግበራ ሂደት ሁሉ ውስጥ የባለድርሻ አካላት መሳተፍ የሚችሉበትን አሰራሮች ይፍጠሩ፡፡

## ክትትልና ምዘና

የሂደትና የውጤት ጠቋሚ መረጃዎች በክትትልና ምዘና ማዕቀፎችና ተግባሮች ውስጥ ተካተዋል?

- ✓ ጠቋሚ መረጃዎች ሲመረጡ ወይም ሲዘጋጁ በፆታና በእድሜ የተከፋፈሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ (እንደ አነስተኛ መስፈርትና እንደ ተገቢነታቸው) ::
- ✓ በክትትልና ምዘና እንደዚሁም በሁኔታ ትንተና ዝግጅት ወቅት የጤና ሁኔታ ጠቋሚ መረጃዎች የበሽታና የሞት መረጃን፣ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ በፆታና በዕድሜ የተከፋፈሉ ሆነው መካተታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለክትትልና ምዘና የሚረዱ መረጃዎች ምንጫቸው ዩት ነው?

- ✓ ማህበራዊ፣ የምጣኔ ሃብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች በጤና ላይ የሚያሳድሩ ተጽህኖዎችን ለመተንተን ከተለያዩ ምንጮች በሚወሰዱ መረጃዎች ላይ ይመርኮዙ

ፕሮግራሙ በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና በጤና ፍትሃዊነት ላይ የሚታየውን እምርታ ይከታተላል?

- ✓ ሴቶችንና ማህበረተሰቡን ለማብቃት እርምጃዎች መካተታቸውንና መተንተናቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ✓ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና የጤና ፍትሃዊነትን ለመመዘን ተራማጅ እርምጃዎችን ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ለሥርዓተ-ፆታ ማካተት የሂደትም ሆነ የውጤት ጠቋሚ መረጃዎችን ያካትቱ
- ✓ ማህበራዊ እርምጃዎች ምርታማውንም ሆነ ስነ-ተዋልዶአዊውን የሴቶችን ሚና ማካተት አለበት፡፡
- ✓ የፕሮግራሙ ወይም የፖሊሲው ውጤቶች በተለያዩ የእድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ እና በሌሎች ማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ እንደዚሁም ማህበራዊና ማህላዊ እርከኖች ላይ በሚገኙ ሴቶችና ወንዶች ላይ ያሳደረውን የተጽህኖ ልዩነትን እንደ አመችነቱ ይፈትሹ፡፡
- ✓ ለማሻሻያዎች፣ ለማስተካከያ እርምጃዎች ወይም ለሚቀጥሉ የፕሮግራሞችና የፖሊሲዎች ዑደት ግብአት እንዲሆኑ ከክትትልና ምዘና የተሰበሰቡትን መረጃዎች ይጠቀሙ፡፡

እንደ ተጠቃሚም ሆነ እንደ ፕሮግራሙ ሰራተኝነት ወንዶችና ሴቶች በክትትልና በምዘና ደረጃዎች እኩል ተሳታፊ ሆነዋል?

- ✓ የማህበረተሰብ አካላትን (ወንዶችና ሴቶችን) እና ሌሎች የባለድርሻ አካላትን በክትትልና ምዘና ስትራቴጂ እና በተግባሮች ቀረጻ ውስጥ ያካትቷቸው፡፡

## ዋቢ መጻህፍትና ማጣቀሻ ሰነዶች


1. የጤና ሚኒስቴር፣ የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ 2020-2025፣ 2020

2. Gender mainstreaming manual for health managers: A practical approach. Geneva, World Health Organization, 2011.

3. Gender, health and tobacco. Geneva, World Health Organization, 2003. (http://www.who.int/gender/documents/Gender_Tobacco_2.pdf,

4. Integrating poverty and gender into health programmes: A sourcebook for health professionals. Geneva, World Health Organization, 2008. (http://www.wpro.who.int/NR/rdonlyres/C93DEB19-91A0-4EA5-

5. Online gender learning and information module. Unit 1: A conceptual framework for gender analysis. Geneva, International Labor Organization, 1998

6. UN gender equality score card, performance indicators for gender equality and the empowerment of women for UN country teams, 2018 framework and technical guidance V2.0

7. Beijing Declaration and Platform for Action, 4th conference for women, 1995

8. Gender mainstreaming in WHO: what is next? Report of the midterm review of WHO gender strategy, WHO, 2011

9. Gender mainstreaming research services, APLAP conference, Canberra, 2015

10. የኢትዮጵያ የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ጤና ሚኒስቴር፣ አገር አቀፋዊ የጤናው ሴክተር የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል፣ 2006 ዓ. ም.